# ዐፄ ቴዎድሮስ እና ልዑል ዓለማየሁ ቴዎድሮስ

ከተደለ ብጡል ክብረት



ዐፄ ቴዎድሮስ

እና



ልዑል ዓለማየሁ

## ልዩ ምስጋና

1. ለአማራ ክልል ሺሕኛ ዓመት ጽሕፈት ቤት (የአማራ ክልል ሚሊኒየም ሴክሬታሪያት)

2. ለኢት-ሜዲክስ (ET-MEDIX) የመድኀኒት አቅራቢ ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ምናሴ ክፍሌ

3. ለአቢሲኒያ ባንክ

እነዚህ ስማቸው ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ድርጅቶች፣ለመጽሐፉ የመጀመሪያ እትም ላደረጉልኝ የገንዘብ ድጎማ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

የዚህን መጽሐፍ የመጀመሪያው ህትመት ገቢ በሙሉ ጎንደር ለሚሠራው የዐፄ ቴዎድሮስና የልዑል ዓለማየሁ ሐውልት ማሠሪያ እንዲውል በደስታ አበረክታለሁ።

ሽፋን ዲዛይን በታደለ ብጡል ክብረት
የቴዎድሮስ የሽፋን ሥዕል በኤልያስ አረዳ
ኅዳር ፪ ሺሕ ዓ.ም.
2007




## አስተያየት

ዐፄ ቴዎድሮስ እና ልዑል ዓለማየሁ ቴዎድሮስ የተሰኘውን በታደለ ብጡል ክብረት የተጻፈውን መጽሐፍ አንብቤ የሚከተለውን አስተያየት አስፍሬአለሁ።

አለቃ ዘነበ፣ሄንሪ ብላንክ፣ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት፣ብርሃኑ ዘሪሁን፣ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ፣አሁን ደግሞ ታደለ ብጡል ክብረት ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ መጽሐፍ ጽፈው ለአንባብያን አቅርበዋል።

የደራሲ ታደለ ብጡል ክብረትን መጽሐፍ በጉጉት አነበብኩት።

1ኛ. እስካሁን ካነበብኋቸው የዐፄ ቴዎድሮስ የትውልድ ሐረግ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በበለጠ በዝርዝር ተገልጿል።
2ኛ. የዐፄ ቴዎድሮስ ሁለት ጋብቻዎችም በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ በጥሩ ሁኔታ ተብራርቷል።
3ኛ. ሁለት ወንድሞቻቸው እና አባታቸው ራስ ውቤ ከታሰሩ በኋላ እቴጌ ጥሩ ወርቅን ማግባታቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ያነበብሁት ከዚህ መጽሐፍ ነው።
4ኛ. ዐፄ ቴዎድሮስ ለልጃቸው ለልዑል ዓለማየሁ የነበራቸውን ፍቅር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ልብ በሚነካ አጻጻፍ ቀርቧል።
5ኛ. ዐፄ ቴዎድሮስ ለማዳ እንስሳት እንደነበሯቸውና ከአንበሶች ጋር ውሎ ያደርጉ እንደነበረ ይኸው መጽሐፉ ያስረዳል።

የትልልቅ ሰዎች የሕይወት ጉዞ እንደውቅያኖስ ውሀ ተቀድቶ የማያልቅ መሆኑን ለማመላከት በመጽሐፉ ውስጥ ጀግንነት፣ ቆራጥነት፣ ደግነት፣ አመዛዛኝነት፣ ሩኅሩኅነት፣ ታጋሽነት ቁልጭ ባለ መልኩ ተጽፏል።

ታሪኩ ሚዛናዊነት እንዲኖረው የዐፄ ቴዎድሮስን ትብጥብነት፣ ጭፍንነት፣ ችኩልነት እና ጨካኝነት ወ.ዘ.ተ. የሚንፀባርቅባቸው ባህርያትን ቀልብ በሚስብ መልኩ በዚህ መጽሐፍ መቅረቡ የደራሲውን ሥራ ያስመሰግናል። የዐፄ ቴዎድሮስ የአንድነት ትግል፣ለአፍሪካ ሕዝቦች የነጻነት ትግል የመጀመሪያዊ ኢትዮጵያዊ ነፀብራቅ መሆኑ አይካድም። መጽሐፉ ከዚህ አኳያ ሲዳሰስ ተገቢነት ያለው አቀራረብ ነው ማለት ይቻላል።

ዓለማየሁን በተመለከተ፣የወጣቱን ልዑል ሕይወት የሸረሸረውን ብቸኝነት፣ ባይተዋርነትእንዲሁም ለእንግሊዝ አገር ባዳ በመሆኑ፣አገሩ እና ወገኖቹ እንደናፈቁት፣ በለጋ ዕድሜው ማለፉን ቁልጭ ባለ መልኩ ደራሲ ታደለ ብጡል ክብረት ማቅረባቸው፣ልዑል ዓለማየሁ በሕይወት ቢኖሩ ኖሮ የእንግሊዝ መንግሥት የፖለቲካ መሣሪያ ሊያደርጋቸው ያስብ እንደነበረ መጽሐፉን የሚያነብ ሁሉ መገንዘብ አያዳግተውም።

ደራሲ ታደለ ብጡል ክብረት እሳይ በተጠቀሰው ርእስ የጻፉት መጽሐፍ፣ቀደም ሲል በተለያየ ወሬ ሲተረክ የነበረውን የዐፄ ቴዎድሮስን እና የልዑል ዓለማየሁን የሕይወት ታሪክ በዚህ መጽሐፍ አሁን ዕውነታውን እንድንገዘነብ ማድረጉ በጣም አስደስቶኛል::

ከሁሉም በላይ ደግሞ፣አዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው ቸርቸል ጎዳና መሐል በዐፄ ቴዎድሮስ ስም ስለተሰየመው አደባባይና በስፍራው ሊቆም ስለታሰበው ሐውልት አጠር ያለ ዘገባ ማቅረባቸው፣መጽሐፉን የተሟላና ተወዳጅ ያደርገዋል::

የዐፄ ቴዎድሮስን ሐውልት ለማቆም የታሰበው በኢትዮጵያ ደራሲያን አባላት ጥያቄ ነው:: በዚያን ዘመን ክቡር ደጃዝማች ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት የማኅበሩ ፕሬዚደንት ሲሆኑ እኔ ደግሞ ዐቃቤ ንዋይ ነበርኩ:: አዲስ አበባ ቸርቸል ጎዳና ላይ የቴዎድሮስ ሐውልት እንዲሠራ የተፈቀደው ደጃዝማች ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት ጽፈውት የነበረውን ቴአትር በማሳየት የሚገኘውን ገቢ ለደራሲያን ማኅበር ሰጥተው ስለነበረ፣በቴዎድሮስ መቶኛ (፻ኛ) ሙት ዓመት ቴአትሩን ለማሳየት የደራሲያን ማኅበር ብሄራዊ ቴአትር ቤትን ለተከራየ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቴአትሩን እንዲያዩ ተጋብዘው የእሺታ መልስ ሰጡ:: አጋጣሚውን በመጠቀም፣በሕዝብ ዘንድ ለሚወደዱት እና ለሚታወሱት ዐፄ ቴዎድሮስ፣ በስማቸው አደባባይ እንዲሰየም ቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወት ባቀረቡት ጥያቄ፣የመሠረት ድንጋይ በተቀመጠበት ምሽት፣ንጉሠ ነገሥቱ ቴአትሩን ለማየት መጥተው ነበር:: ቴአትሩ ከመታየቱ በፊት ደጃዝማች ግርማቸው ያደረጉት ንግግር አጠር ብሎ ከዚህ በታች ቀርቧል::

> ግርማዊ ሆይ!
>
> በዛሬው ቀን ደስታዬ እጥፍ ድርብ ነው:: በአንድ በኩል ግርማዊነትዎ ለታላቁ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ቴዎድሮስ በመናገሻ ከተማዎ አዲስ አበባ መሐል ሐውልታቸው እንዲቆም ፈቅደው ዛሬ የመሠረት ድንጋይ በማኖርዎ ሲሆን፣በሌላ በኩል ደግሞ መጽሐፉን ጽፌ ቴአትሩ መታየት ከጀመረ በ፲፱ኛው ዓመቱ የግርማዊነትዎ መልካም ፈቃድ ሆኖ ቴአትሩን ለማየት ስለተገኙልን ነው::
>
> ግርማዊ ሆይ!
>
> ቴዎድሮስን የምንጠላውና የምንወደው በሁለት የተለያዩ ምክንያቶች ነው:: በአንድ በኩል የሰዎች እጅ ቆርጧል፣ሰዎችን ገደል አስገብቷል እየተባለ የሚናፈሰውን ወሬ ስንሰማ ሲሆን፣በሌላው በኩል ደግሞ በመሳፍንቶች ተከፋፍላ የነበረችውን ኢትዮጵያ አንድ ለማድረግ ሌት ተቀን ደክመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የወሰዷቸውን እርምጃዎች፣ ኢትዮጵያ ዘመናዊ አስተዳደር እንዲኖራት፣ ገበሬው በእርሻው፣ወታደር በደመወዝ እንዲተዳደር፣የቤተ ክህነት አገልጋዮች ቁጥር ከአምስት እንዳይበልጥ የሰጧቸው ውሳኔዎች እና በመጨረሻም ለኢትዮጵያ ክብር በራሳቸው እጅ ሕይወታቸውን ማጥፋታቸው፣ዐፄ ቴዎድሮስ በኢትዮጵያ ነገሥታቶች ታሪክ ቀዳሚውን እና ዋናው ሆኖ ለዘለዓለም ይኖራል::

በመጨረሻም፣ደራሲ ታደለ ብጡል ክብረት የመጽሐፉን የመጀመሪያ ህትመት የሽያጭ ገቢ በሙሉ፣ለዐፄ ቴዎድሮስና ለልጃቸው ለልዑል ዓለማየሁ ለሚቆመው ሐውልት ማሠሪያ እንዲውል ለመለገስ መወሰናቸው ደግሞ እጅግ ያስመሰግናቸዋል::

ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ
የኢፌዴሪ ፕሬዚደንት



## መቅድም

ጌታው ኃይሉ አባታቸው ደጃዝማች ወልደ ጊዮርጊስ ከሚገዙት አገር በአንዱ አውራጃ በምክትልነት ሹመዋቸው ሳለ፣ከበላይ አለቃቸው ጋር ባለመስማማት ግዛታቸውን ለቅቀው ወደ ጎንደር ሄዱ:: ለሁለት ዓመት ያህል ያለ ትዳርና አጋር ከኖሩ በኋላ የእንፍራንዝ ባላባት የሆኑትን ወይዘሮ አትጠገብ ወንድ በወሰንን አግብተው ወንድ ልጅ አፈሩ:: በ፲፱፻፲፩ ዓ.ም. በደቡብ ምሥራቅ ጎንደር ለተወለደው ለዚህ ሕፃን "ካሣ" የሚል ስም አወጡለት:: ይህን ስም ሲሰጡት ቀደም ሲል ለደረሰባቸው ስደትና ብቸኝነት ማካካሻ ሆነኝ ለማለት እንጂ፣ሕፃን "ካሣ" አድጎና ተመንድጎ አንድ ቀን ይነግሣል ብለው ያሰቡ አይመስልም:: ለዚያውም ካሣ በተወለዱ በዓመቱ አባቱ ጌታው ኃይሉ ወልደ ጊዮርጊስ፣፲፱፻፲፪ ዓ.ም. ጎንደር ውስጥ ዐርፈው ሰቀልት ወረዳ ጋና ዮሐንስ ከተባለው ትልቅ ገዳም ውስጥ ተቀበሩ::

የካሣ ዕድሜ ለትምህርት ሲደርስ አጎታቸው ደጃዝማች ማሩ ኃይለ ጊዮርጊስ ቄስ ትምህርት ቤት አስገቧቸው:: ትምህርታቸውን በሚገባ በመከታተል ላይ እያሉ፣በአገር አገዛዝ ጠብ ምክንያት ደጃዝማች ማሩ በመሸፈታቸው ካሣ ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ተገደዱ:: ከዚያም ወደ ታላቅ ወንድማቸው ደጃዝማች ክንፉ ኃይሉ ዘንድ ሄደው ለጥቂት ጊዜ ተቀመጡ:: ቀጥሎም አመቺ ሁኔታ ጠብቀው የራሳቸውን ዕድል ፍለጋ ሸፈቱ:: በሂደት ጉልበታቸው እየበረታ፣ኃይላቸው እየጨመረ መጣ:: ከዚህ በኋላ ባላንጣዎቻቸውን እያሸነፉ ሲሄዱ፣የ፲፪ ዓመት ኮረዳ የነበሩትን የደጃዝማች ውቤን ልጅ አገቡ:: የወይዘሮ ጥሩወርቅ አባት ደጃዝማች ውቤ፣ወንድሞቻቸው ደጃዝማች ወንድ ወሰን እና ደጃዝማች ጓንጉል የካሣ እስረኞች ስለነበሩ ወይዘሮ ጥሩወርቅ በትዳራቸው ደስተኛ አልነበሩም:: ካሣ ከባለቤታቸው ፍቅርና አክብሮት ሳያገኙ በመቅረታቸው ከፍተኛ ቅሬታ ነበራቸው:: ይሁን እንጂ የእግዚአብሄር ፈቃድ ሆነና ባልና ሚስቶቹ አንድ ወንድ ልጅ ለማፍራት በቁ:: ወይዘሮ ጥሩወርቅ የወለዱላቸውን ሕፃን ሲያዩ፣ካሣ እጅግ ከመደሰታቸው የተነሳ ዓለማየሁ የሚል ስም አወጡለት:: ትርጉሙ ደስታን አገኘሁ እንደማለት ነው::

## ልዩ ምስጋና

1. ለአማራ ክልል ሺሕኛ ዓመት ጽሕፈት ቤት
   (የአማራ ክልል ሚሊኒየም ሴክሬታሪያት)

2. ለኢት-ሜዲክስ (ET-MEDIX) የመድኀኒት አቅራቢ ድርጅት
   ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ምናሴ ክፍሌ

3. ለአቢሲኒያ ባንክ

እነዚህ ስማቸው ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ድርጅቶች፣ለመጽሐፉ የመጀመሪያ እትም ላደረጉልኝ የገንዘብ ድጎማ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

የዚህን መጽሐፍ የመጀመሪያው ህትመት ገቢ በሙሉ ጎንደር ለሚሠራው የዐፄ ቴዎድሮስና የልዑል ዓለማየሁ ሐውልት ማሠሪያ እንዲውል በደስታ አበረክታለሁ።

ሽፋን ዲዛይን በታደለ ብጡል ክብረት
የቴዎድሮስ የሽፋን ሥዕል በኤልያስ አረዳ
ኅዳር ፪ ሺሕ ዓ.ም.
2007



# ምዕራፍ ፩


## ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ



መይሳው ካሣ፣የቋራው አንበሳ

በበጌምድር በተለይም በቋራ ታዋቂ መሳፍንት ከነበሩት አንዱ ደጃዝማች ወልደ ጊዮርጊስ ነበሩ። ደጃዝማች ወልደ ጊዮርጊስ የባላባት ወገን የሆኑ እመቤት ነጭትን አግብተው ጌታው ማሩ እና ጌታው ኃይሉ የሚባሉ ሁለት ልጆች አፍርተዋል። ጌታው ማሩ ዕድሜያቸው ከፍ ሲል በደጃዝማችነት ማዕረግ የደምቢያ ገዥ ሆኑ። ጌታው አቶ ኃይሉ፣በአባታቸው ግዛት ቋራ በምክትል ሹምነት ሲሠሩ ከእንፍራንዝ መሳፍንት የሚወለዱትን እመቤት ወልደ ተክሌን አግብተው ልጅ ክንፉን ወልደዋል።

# ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ



መይሳው ካሣ፣የቋራው አንበሳ

ልጅ ክንፉ ለዐቅመ አዳም ሲደርሱ በውትድርና ሙያ ሠልጥነው የደጃዝማችነት ማዕረግ ለማግኘት በቁ:: ደጃዝማች ክንፉ ኃይሉ ትዳር መሥርተው፣ልጅ መኮንን፣ልጅ ይልማ እና ልጅ ጋረድ የሚባሉ ሦስት ወንዶች እና ሁለት ሴቶች ልጆች ወልደዋል::

ጌታው ኃይሉ በበኩላቸው አባታቸው ደጃዝማች ወልደ ጊዮርጊስ ከሚገዙት አገር በአንዱ አውራጃ በምክትልነት ሹመዋቸው ሳለ፣ከበላይ አለቃቸው ጋር መስማማት ስላለቻሉ፣ ግዛታቸውን ለቅቀው ወደ ጎንደር ሄዱ:: ጎንደር ውስጥ ሁለት ዓመት እንደ ተቀመጡ ብቸኝነት ስለ ተሰማቸው ሚስት ለማግባት ወሰኑ:: የትዳር ጓደኛ የምትሆን ሚስት ሲያፈላልጉ፣ከእንፍራዝ መሳፍንት ከሚወለዱ ከእመቤት አትጠገብ ጋር በ፲፰፻፲ ዓ.ም. ትዳር መሠረቱ:: ጋብቻ በፈፀሙ በዓመቱ ጥር ፮ ቀን ፲፰፻፲፩ ዓ.ም. ከጎንደር በስተደቡብ በሚገኝ ገጠር ውስጥ ባልና ሚስቶቹ አንድ ወንድ ልጅ ዐፈሩ::

ከአገራቸው ከቋራ ስለወጡ ይበሳጩ የነበሩት ጌታው አቶ ኃይሉ፣ወንድ ልጅ በመወለዱ ተደስተው ለልጃቸው "ካሣ"* የሚል ስም አወጡለት:: ይህን ስም ሲሰጡት ቀደም ሲል ለደረሰባቸው ስደትና ብቸኝነት ማካካሻ ሆነኝ ለማለት እንጂ፣ሕፃን ካሣ አድጎና ተመንድጎ አንድ ቀን ይነግሣል ብለው ያሰቡ አይመስልም::

ካሣ በጎንደር ከተማ ዐቢየ እግዚ ቤተ ክርስቲያን ሲጠመቁ፣ገብረ ኪዳን የሚል የክርስትና ስም ተሰጣቸው:: ካሣ በተወለዱ በዓመቱ፣ጌታው ኃይሉ ወልደ ጊዮርጊስ፣በድንገት ታምመው በ፲፱፻፲፪ ዓ.ም. ጎንደር ውስጥ ዐርፈው ሰቀልት ወረዳ ጋና ዮሐንስ ከተባለው ትልቅ ገዳም ውስጥ ተቀበሩ:: በጌታው ኃይሉ ሞት ምክንያት ካሣን የማሳደግ ኃላፊነት የእመቤት አትጠገብ ሆነ:: ካሣ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ፣አጎታቸው ደጃዝማች ማሩ ዘንድ እየኖሩ እንዲማሩ በአደራ ተሰጡ:: ደጃዝማች ማሩ አደራውን ተቀብለው ካሣን ቸንክር ተክለ ሃይማኖት ከተባለው ደብር አስገብተው መንፈሳዊ ትምህርት እንዲማሩ አደረጉ:: እሳቸው ትምህርታቸውን በጥሩ ሁኔታ ሲከታተሉ ደጃዝማች ማሩ የደንቢያ ገዥ ነበሩ:: ደጃዝማች ማሩ የበጌምድር ገዥ ለመሆን ከነበራቸው ምኞት የተነሳ ለራስ ይማም አልገዛም ብለው ሸፈቱ::



በዚህ ምክንያት፣ ራስ ይማም ከደጃዝማች ማሩ ጋር ለመዋጋት ወደ ደንቢያ ዘመቱ:: የራስ ይማም ጦር አይሎ፣ደንቢያን ዘርፎ መንደሮችንም አቃጠለ:: በዚህ ብቻ ሳይወሰን ቸንክር ተክለ ሃይማኖት ደብር ይማሩ ከነበሩት ወጣቶች መሐል በእሳቸው ትእዛዝ ሃምሳ ያህል ተማሪዎች እንዲሰለቡ አደረገ:: ካሣ ከአደጋው ለመትረፍ የቻሉት፣በዚያን ዕለት ከመምህራቸው ጋር ወደ ሌላ ስፍራ ሄደው ስለነበረ ነው:: ወጣቱ ካሣ ከዚህ አደጋ ካመለጡ በኋላ ትምህርታቸውን አቋርጠው ወደ ታላቅ ወንድማቸው ደጃዝማች ክንፉ ዘንድ ሄዱ:: ካሣ ከታላቅ ወንድማቸው ደጃዝማች ክንፉና ከእሳቸው ልጆች ጋር ጥቂት ወራት አብረው ከሰነበቱ በኋላ ደጃዝማች ክንፉ ዐረፉ::

ወንድማማቾቹ መኮንን ክንፉ እና ይልማ ክንፉ፣የአባታቸውን ግዛት እኔ ልያዝ፣እኔ ልግዛ በመባባል በመጣላታቸው፣በመሐከላቸው ጦርነት ተካሄደ:: ከዚያም ወንድማማቾች ዘንጊ ከሚባል ስፍራ ውጊያ ገጠሙ:: ካሣ ለመኮንን ወግነው የውጊያው ተሳታፊ ነበሩ:: ድሉ የይልማ ሆኖ፣ልጅ መኮንን ክንፉ በጦርነቱ ሲሸነፉ ካሣ ተማረኩ:: ነገር ግን ካሣ የልጅ ይልማ አጎት ከመሆናቸውም በላይ በመሐከላቸውም የግል ጠብ ስላልነበረ በነፃ ተለቀቁ::

ከዚያ በኋላ ካሣ ከአንዱ መስፍን ወደ ሌላ መስፍን ግቢ እየተዘዋወሩ በመሥራት እና በመዋጋት የጦርነት ልምድ አካበቱ:: ከዚያም የራሳቸውን ዕድል ለመሞከር በሽፍትነት ሥራ ተሰማሩ:: ጫካ ገብተው በሸፈቱበት ወቅት ጉልበታቸው እየጠነከረና ስማቸው እየገነነ ስለ መጣ ከተራ ሽፍትነት ይልቅ ሥልጣን ለመያዝ ተነሳሱ:: ይህን ምኞታቸውን ለማሳካት አስበው የራሳቸውን ሠራዊት አቋቁመው የመሪነት ዳዬ «ሀ» ብለው ጀመሩ:: በዚህም በየጊዜው በሚያደርጓቸው መቆራቆዝ የበላይነት ስለሚያገኙ ለተቀናቃኞቻቸው መቅሰፍት ሆኑ:: ዝናቸው እየገነነ ስለመጣ የሠራዊታቸውም ቁጥርም በብዙ እጥፍ ጨመረ:: በዚህን ጊዜ ነበር አቶ እንግዳ ወርቅ የሚባሉትን የታወቁ ታላቅ ሽፍታ ተወዳጅተው፣ገሰሰች እንግዳ የሚባሉትን ልጃቸውን አግብተው፣መሸሻ እና አልጣሽ የሚባሉ አንድ ወንድና አንድ ሴት ልጅ ያፈሩት:: ከዚያ በኋላ፣ወሀኒ የሚባለውን አምባ ወርረው ብዙ ሀብት ዘረፉ:: የወሀኒን መዘረፍ የሰሙት የአገረ ገዢው የራስ ዓሊ እናት በጣም ተናደዱ::

መናደድ ብቻ ሳይሆን ካሣን አሳድዶ የሚይዝ ጦርም ላኩ:: የተላከው ጦር የካሣን ሠራዊት ተሰልፎ ሲያይ ሕዝቡ የሚበገር ስላልመሰለው ምንም ሳይዋጋ ወደ መጣበት ሠፈር ተመልሶ፣የካሣ ጦር የተደራጀና የማይበገር መሆኑን ተናገረ:: ይህን አስደንጋጭ ዜና እቴጌ መነን ሲሰሙ፣ካሣን በወዳጅነት መያዙን መርጠው ሰላም ፈጠሩና ካሣን የቋራ ምስሌኔ አድርገው ሾሟቸው::

ካሣ ሹመቱን ተቀብለው ወደ ግዛታቸው ለመሄድ ተዘጋጅተው እቴጌ መነንን ሊሰናበቱ ሲሄዱ "ቋራ በባለነጋሪት ደጃዝማች እንዲስተዳደር እቴጌዪቱ ስለወሰኑ፣ካሣ የበላያቸው ሆኖ አዲስ የተሾመውን አለቃቸውን አጅበው እንዲሄዱ ታዘዙ:: ካሣ ከበላያቸው ሰው መሾሙን ባይወዱም ትእዛዙን ተቀብለው ለመሄድ ሲዘጋጁ "ከእኔ ጋር የሚሄደው ማነው?" ብለው ሲጠይቁ ደጃዝማች በለው መሆናቸው ተነገራቸው:: የበላይ ሹማቸው ተማርረው ወደ ግዛታቸው እዳይሄዱ ካሣ ዕቅድ አወጡ::

ያሰቡትን በሆዳቸው ይዘው ለደጃዝማች በለው መንገድ መሪ ሆነው ቅርቡን መንገድ እየተው፣ገደልማና ሩቅ በሆነ መንገድ ስለ ወሰዷቸው የደጃዝማቹ ሠራዊት ከመዳከሙና ከመሰላቸቱም በላይ ፈረስና በቅሎውም ገደል እየገባ አለቀ:: ደጃዝማች በለው ይህን ሁሉ ችግር ሲያዩ "ደህና የተሻለ መንገድ የለም ወይ?" ብለው ካሣን ጠየቁ:: ካሣም "ደርሰናል" እያሉ ተጨማሪ ብዙ መንገድ ካስጓዟቸው በኋላ ቋራ ደረሱ::

ደጃዝማች በለው ከሠራዊታቸው ጋር ቋራ እንደገቡ "ጦር ሲመጣብህ ቤትህን እያቃጠልክና እየጮህክ ሽሽ" ብለው ካሣ ወደ ሕዝቡ መሐል ገብተው መከሯቸው:: የደጃዝማች በለው ሠራዊት በበኩሉ አገሬውን መውጋት ጀመረ:: በዚህን ጊዜ ከካሣ በተሰጠው ምክር መሠረት ሕዝቡ ቤቱን እያቃጠለ እና እየጮኸ ይሸሽ ጀመር:: ከዚያ በኋላ ካሣ ወደ ደጃዝማች በለው ቀርበው "እዩልኝ ይህን እርጉም አገር፣ዘላለም እንዲሁ በጦርነት ነው የምንኖረው:: አመለኛ ስለሆነ ምንም ቢደረግለት እሺ ብሎ አይገዛም" አሏቸው::

*ገሪማ ታፈረ፡- መሪሳው ካሳ፡ የቋራው አንበሳ



የደጃዝማች በለው ሠራዊትም "እዚህ የከፋ አገር እንዳመጡን ወደ ደህናው አገራችን ይመልሱን" እያሉ አጉረመረሙ:: ደጃዝማች በለው የሠራዊታቸውን መበሳጨት ተገንዝበው "አገሩ የከፋ ነው" ብለው ወደ ጎንደር ሲመለሱ "ካሣ ወዴት ቀረ?"* ብለው እቴጌ መነን ሲጠይቋቸው "ደንቢያ ድረስ ሸኝቶኝ ወደ ቋራ ተመለሰ" አሉ:: እቴጌ መነን ግን ካሣ ቋራ ገብተው መሸፈታቸውንም ጭምር ሲሰሙ በጣም ተናደዱ:: በካሣ መሸፈት እናታቸው መናደዳቸውን የተረዱት ራስ ዓሊ "እናቴ እቴጌ መነን በድለውሃል እና እኔ አስታርቅሃለሁ" ብለው ታላላቅ ሽማግሌዎች ልከው ካስታረቋቸው በኋላ የቋራን ገዥነት ከደጃዝማችነት ማዕረግ ጭምር ሰጧቸው::

በዚያን ዘመን በሱዳን ወሰን በኩል ወደ ኢትዮጵያ እየገባ ያስቸግር የነበረውን የግብፅ ሠራዊት፣ ቀደም ብሎ ካሣ እየደጋገሙ አሸንፈው ስለ ነበረ በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር ታላቅ ዝና ለማግኘት በቅተው ነበር:: አሁን በአዲስ የተሾሙበት ግዛታቸውን በሰላም ለማስተዳደር ሲነሱ፣በወሰን አካባቢ ያሉት ግንጃሮች (ሻንቅሎች) በመተማ በኩል ድንበር እየጣሱ በመግባት ዘረፋ ያካሂዱ ጀመር:: ካሣ እነዚህን ወራሪ ግንጃሮች ለመዋጋት ምርጥ የሆኑ ሰዎች ይዘው ወደ መተማ ዘመቱ:: ጦርነት ለመዋጋት ያዘጋጁትን ዘጠና የሚያህል ሰው ሰብስበው "ግንጃር ብዙ ሆኖ ተሰልፎ ለማስፈራራት ይመጣባችኋል እና አትፍሩት፣ዝም በሉት" ብለው መከሯቸው::

ካሣ እንዳሉትም ግንጃሮች በፈረስ ሆነው በብዛት መጡ:: የካሣ ሠራዊትም እንደታዘዘው ግንጃሮቹ አጠገቡ እስኪደርሱ ድረስ ዝም ብሎ ቆሞ ጠበቃቸው:: ግራ የገባው የግንጃር ሠራዊትም ከፈረሱ እየወረደ በእግሩ ወደ ካሣ ሠራዊት ተጠጋ:: ካሣም ከሠራዊቱ መሐል ወጥተው በሰላም ከግንጃሮቹ ጋር ተገናኙ:: ከዚያም ወደ መተማ ከተማ አብረው ተጉዘው በሰላም ገቡ:: መተማ ሲደርሱ ግንጃሮቹ የዝሆን ጥርስ፣ስን እና ብርት፣ገንዘብ እና ሌላም ዕቃዎች ለካሣ ሰጥተው በሰላም ተለያዩ:: ካሣም ከግንጃሮች የተቀበሉትን ዕቃዎች ለእቴጌ በስጦታ ላኩላቸው::*

* ጳውሎስ ኞኞ:- አጤ ቴዎድሮስ

ቀደም ሲል እንደተገለጠው ካሣ በሱዳን በኩል የሚመጣውን የውጭ ወራሪ ደጋግመው በማሸነፍ የበርካታ ድሎች ባለቤት ሆነዋል። እንዲህ ዓይነቱን ጀግና በጦርነት ሳይሆን በወዳጅነት ለመያዝ አስበው፣እቴጌ መነን የልጃቸውን የራስ ዓሊን ልጅ፣ወይዘሪት ተዋበችን ለካሣ ሊድሩላቸው ፈለጉ። ቀጥሎም "የአቶ እንግዳ ወርቅን ልጅ ትተህ የኔን ልጅ አግባ" ብለው ላኩባቸው። ካሣም በተነገሩት ተደስተው በ፲፰፻፵፱ ዓ.ም. የራስ ዓሊን ልጅ፣ የእቴጌ መነንን የጅ ልጅ ወይዘሮ ተዋበችን በሕግ አገቡ።

ጋብቻውን በተመለከተ «አጤ ቴዎድሮስ» በሚባለው መጽሐፍ ውስጥ ጳውሎስ ኞኞ እደሚከተለው ጽፈል።

> ምንም እንኳን ካሣ የመስፍኑ የራስ ዓሊ እና የአጤ ዮሐንስ ፫ኛ ባለቤት የእቴጌ መነን አማች ቢሆኑም፣ሦስቱ ታላላቅ መሪዎች የካሣ ጋብቻ የእኩዮች ጋብቻ አይደለም በማለት ካሣን ይንቋቸው ነበር። ወይዘሮ ተዋበች ዓሊን አግብተው ለመሪዎቹ ቤተኛ ከሆኑ በኋላ ካሣ ብዙ ችግር ደረሰባቸው። ከችግሩ አንዱ፣መሪዎቹ ንቀታቸውን ለማሳየት ሲሉ ካሣ የሚያስተዳድሯቸውን ግዛቶች መቀነስ እና የሚሰጡትንም ፍርድ እስከ መቀልበስ መድረሳቸው ነበር።

ካሣ ግዛታቸው ሲቀነስ፣ለሠራዊታቸው የሚሆን ስንቅ አጥተው በጣም ተቸገሩ። ዐቅማቸው ተዳክሞና ሠራዊታቸው የተጉላላ መሆኑን ስለ ዐወቁ፣ራስ ዓሊ፣ካሣን እስከ ጭራሹ ለማስወገድ ፈለጉ። ዕቅዳቸው እንዲሳካም ዘዴ ፈጠሩ። ዘዴውም ካሣን ወደ ኢትዮጵያ ወሰን ልከው በጦር ሜዳ እንዲሞቱ ማመቻቸት ነበር።

በዚያ ዘመን ግብፆች በሱዳን በኩል እያለፉ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ገብተው ቤት ያቃጥሉ፣ንብረት ይዘርፉ ስለ ነበረ፣ካሣ ስለ አገራቸው መደፈር ተቆጭተው ትዕዛዙን በፀጋ ተቀብለው የግብፅን ጦር ለመግጠም በፈቃደኛነት ዘመቱ። የግብፅ ጦር የዘመኑን አዳዲስ መሣሪያ ታጥቆ ነበር። በአንፃሩ፣የካሣ ሠራዊት ትጥቅ በአብዛኛው የአረጀ ጠመንጃ፣ጋሻ፣ጦርና ጎራዴ ብቻ ነበር።



የሁለቱ ሠራዊት አሰላለፍ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ ነበር ጦርነቱ የተጀመረው። በጎራዴ በመቅላት፣በጦር በመውጋት ችሎታና በከፍተኛ ወኔ ገጥሞ፣የካሣ ሠራዊት የግብፁን ጦር ድል አድርጎ ምሽጋቸውን ያዘ። የኢትዮጵያን ድንበር ጥሶ ገብቶ የነበረው የግብፅ ጦር ሸሽቶ ለማምለጥ ሲሞክር፣የካሣ ሠራዊት ራሂል ከተባለ ወንዝ ላይ ደርሶባቸው፣ብዙዎቹን የግብፅ ወታደሮች ሲፈጅ ጥቂቶች ብቻ አመለጡ። በጦርነቱ ድል የተቀዳጁት ካሣና ሠራዊታቸው እንደጥንቱ ልምድ ከበላዮቻቸው ፊት ቀርበው ግዳይ ጥለው ለመፎከርና ለመሸለም አልበቁም። ለዚህ ምክንያት የሆነው ካሣ ሲዋጉ ቆስለው ነበረና ሕመሙ ጠንቶባቸው ጨንከር ከተባለው መንደር ከአንድ የባህል መድኀኒት ዐዋቂ ሰው ቤት ተኝተው ይታከሙ ስለነበረ ነው። መድኀኒት ዐዋቂው ካሣን ሲያክም ከቆየ በኋላ "ቁስሉ በቶሎ እንዲድን በሚገባ መቀለብ አለብዎ" አላቸው።

ካሣም ምክሩን ሰምተው ለማገገሚያ የሚሆን ስንቅ እንዲልኩላቸው፣ወደ ዐፄ ዮሐንስ ፫ኛ እና እቴጌ መነን ዘንድ መልዕክተኛ ላኩ። ዐፄ ዮሐንስ ፫ኛ መልዕክቱን ሲሰሙ አንድ ሰንጋ፣ብዙ እንጀራ እና ጠጅ ላኩላቸው። እቴጌ መነን ግን አንድ ብልት ሥጋ፣ሠላሳ እንጀራ እና አንድ ገንቦ ጠጅ ብቻ ይላክለት ብለው አዘዙ። ይህን ትዕዛዝ የሰሙ ሰዎች "ምነው እቴጌ? ካሣ ኩሩ ጠባይ እንዳለው የታወቀ ነው። ምናለ? ሲሆን አንድ ፍሪዳ አለበለዚያ አንድ የበግ ሙክት ቢላክ አይሻልም ነበር?"* አሏቸው።

እቴጌ መነን ሲመልሱ "ለአንድ ፍየል ጠባቂ ቆለኛ አንድ ብልት ሥጋ አንሶት ነው እንዴ?"* ማለታቸው ይነገራል። ይህን የእቴጌ መነን ዘለፋ ካሣ ቢሰሙም፣ስጦታውን አመስግነው ተቀበሉ። ከዚያም ከንጉሡ ዘንድ የተላከው ሰንጋ ታርዶ ተበላ። እቴጌይቱ የላኩት አንድ ብልት ሥጋ ግን፣በአገልግል ተቀምጦ ከበሰበሰ በኋላ ተጣለ። እቴጌ መነን፣በካሣ ላይ ያሳዩት የንቀት ተግባር፣ካሣን እጅግ ይወዷቸው የነበሩትን ባለቤታቸውን ወይዘሮ ተዋበችን አናደዳቸው። እቴጌ ተዋበች ከንዴታቸው ብዛት ቴዎድሮስ ከተኙበት ድንኳን ገብተው የሚከተለውን ቃል ተናገሩ። "ሲሆን በቤተ መንግሥቱ አዳራሽ፣ፍሪዳ ታርዶ፣ማቶቱ በጠጅ ርሶ፣ምጥኑ ተለውሶ በተቀበሉን ነበር።

* ጳውሎስ ኞኞ፡- አጤ ቴዎድሮስ

ሌላ ቢቀር እንኳን ድልብ ፍሪዳ ቀሚስ ለብሶ፣ሥጋው በመልከኛ ጠጁ በገንቦኛ በተሳከልን ነበር። እንዴት እና እንደምን ብንናቅ ነው አንድ ብልት ሥጋ የተሳከልን? እኔ ጀግና እወዳለሁ፣ፈሪ ወንድ እንቃለሁ። ከፈሪ ሰው ጋርም አብሬ መኖር አልፈቅድም። ይህን በደል ለመበቀል ከእንግዲህ ታጥቀው ይነሱ"* አሉ። ይህን መሰል አነጋገር ከሚስታቸው የሰሙት ካሣ፣ጥቅምት ፳ ቀን ፲፰፻፵፪ ዓ.ም. በራስ ዓሊና በእቴጌ መነን ላይ ሸፈቱ። የካሣ መሸፈት ሲሰማ በቤተ መንግሥቱ ታላቅ ድንጋጤ ሆነ። ወዲያውኑ፣ካሣ ሳይደራጁ እና ኃይል ሳያበጁ ቀድመው ለማስመታት አሰቡና ካሣን የሚወጋ ጦር ጥቅምት ፲፪ ቀን ወደ ጫቆ ላኩ።

አራት መቶ (፬፻) ጦር እና ጋሻ፣፭፻ ጠመንጃ የያዙ ተከታዮች የነበሯቸው ካሣ፣ እቴጌ ጦር እንደላኩባቸው ሲያውቁ የራሳቸውን ዕቅድ አወጡ። ከዚያም ሠራዊቱን ሰብስበው "ጦርነት የምንገጥምበት ጊዜ ተቃርቧል። ቢሆንም እኔ የእምቢልታና የመለከት ድምፅ ሳላሰማህ ምንም እንዳትንቀሳቀስ። የእምቢልታ ድምፅ በሰማህ ጊዜ ግን ወደ ኋላ እንዳትል። መሐል ገብተህ ካላጨድኸው ወዮልህ" ብለው ማስጠንቀቂያ ከሰጡ በኋላ ከድንኳን ውስጥ ገብተው ተኙ። እንቅልፍ ትንሽ ሸለብ ሲያደርጋቸው የጠላት ጦር መምጣቱን ወይዘሮ ተዋበች ሰምተው ስለነበረ ካሣን ቀሰቀሰው "ጠሩ መጥቷል እና ተነሱ"* ብለው ቀሰቀሷቸው። ካሣ ከመኝታቸው ተነስተው ትጥቃቸውን አሳምረው ከድንኳናቸው ወጡና በፊት እንደ ተናገሩት፣የጠላት ጦር ከእራሳቸው ሠራዊት አቅራቢያ እስኪጠጋ ድረስ በጸጥታ ቆመው ጠበቁ። የሁለቱም ሠራዊቶች ከተጠጋጉ በኋላ እሳቸው ቀደም ሲል በሰጡት መመሪያ መሠረት መለከት አስነፍተው "በለው እንግዲህ" አሉ።

የእቴጌ ሠራዊት ያልጠበቀው የጦር ስልት ስለ አጋጠመው ተሸነፈ። በዚህ ውጊያ አንድ መቶ ያህል ጠመንጃ ስለ ማረኩ፣ተዳክሞ የነበረው የካሣ ሠራዊት እንደገና አንሰራራ። የእቴጌ መነን ሠራዊት ወደ ጫቆ ሄዶ ከካሣ ጋር ጦርነት ከመግጠሙ በፊት፣ደጃዝማች ወንድይራድ የሚባል የጦር አለቃ "ይህን የኮሶ ሻጭ ልጅ እንደ ሙጭጭላ አንገቱን አንቄ አመጣልሻለሁ፣አይዞሽ"* ብሎ ፎክሮ ነበር። ቀደም ሲል ካሣ ፉከራውን ሰምተው ነበር እና ደጃዝማች ወንድይራድ ተማርኮ መያዙን ሲሰሙ በጣም ደስ አላቸው።



ሠራዊቱን ሰብስበው "ዛሬ አንድ ትልቅ እንግዳ መጥቶብኛል እና በርከት ያለ ኮሶ ከያለበት ቦታ ፈልጋችሁ አምጡልኝ" ብለው አዘዙ። ኮሶው መጥቶ ከተደቆሰ በኋላ ተበጥብጦ ቀረበ። ካሣ ጦራቸውን ጭናቸው ላይ አጋድመው ሕዝብ በተሰበሰበት አዳራሽ ውስጥ ደጃዝማች ወንድይራድ ተጠርተው ሲቀርቡ "እናቴ ገበያ ላይ ሳይሸጥላት የቀረ ኮሶ አለ። አሁን እህል ታጥቷልና ይህን ኮሶ ተመገብ" ብለው በትልቅ አንኮላ እንዲቀርብላቸው አዘዙ። ከዚያ በኋላ ደጃዝማች ወንድይራድ ኮሶ እየጠጣ እንዲታሰር ተደርጎ ምግቡ ኮሶ ብቻ በመሆኑ ተሰቃይቶ ሞተ።

ደጃዝማች ወንድይራድን ለሞት ያበቃው፣የካሣ እናት ኮሶ ሻጭ ናቸው ተብሎ ሲወራ ሰምቶ፣ወሬውን በማዛመቱ ነው። እና የሚወራውን ያውሩ እንጂ፣ካሣ በራሳቸውም ይሁን በባለቤታቸው በኩል ያለው የዘር ግንድ አመጣጥ እንደተረጋገጠው፣ኮሶ እስከ መሸጥ የሚያደርስ ችግር አልነበረባቸውም።

ይህንንም ለማሳየት የባል እና ሚስቱን የዘር ግንድ ከዚህ በታች አቀርባለሁ።*

## የካሣ የዘር ግንድ

ከአፄ ልብነ ድንግል ጀምሮ በተዋረድ እስከ ካሣ አያት ደጃዝማች ወልደጊዮርጊስ ድረስ የሚወርደው የልጅ ልጆች ሰልፍ ከዚህ እንደሚከተለው ነው። ዐፄ ልብነ ድንግል፣አቤቶ ያዕቆብ፣ገራም ፋሲል፣ዐፄ ሱስንዮስ፣ዐፄ ፋሲል፣እመቤት ሰብለ ወንጌል፣ደጃዝማች አንስጤ፣ደጃዝማች ኤልፍዮስ፣ደጃዝማች ወልደ ጊዮርጊስ፣ጌታው አቶ ኃይሉ፣ዐጼ ቴዎድሮስ።*

## የእመቤት አትጠገብ የዘር ግንድ

ራስ ወዳጆ ሌንጮን ይወልዳሉ። ሌንጮ ወንድ በወሰንን ይወልዳሉ። ወንድ በወሰን ትሳልን አግብተው አትጠገብን ይወልዳሉ። እሳቸው (አትጠገብ) ካሣ ኃይሉን ይወልዳሉ።*

*ገሪማ ታፈረ፡- መሪሳው ካሳ፡ የቋ ራው አንበሳ

የዐፄ ቴዎድሮስ የእናት እና አባት የዘር ግንድ አመጣጥ ከዚህ ከፍ ብሎ የተጻፈው ነው። ይሁን እንጂ ዐፄ ቴዎድሮስ የሚመኩት ከነገሥታት በመወለዳቸው ሳይሆን "በጦራቸው ላንቃ፣በሰይፋቸው ግርማ" እንደነበረ ይታመናል። ይህንንም እሳቸው በተደጋጋሚ ተናግረውታል። ስለዚህ ካሣ በዘር ቆጠራ የማያምኑ መሆናቸው ቢታወቅም፣ለወግ አጥባቂዎች እና የእሳቸውን ንግሥና ላለመቀበል በሐሰት ስማቸውን ለማጥፋት ተሞክሯል። ዐፄ ቴዎድሮስ የሚመኩት ከነገሥታት በመወለዳቸው ሳይሆን "ከትብያ ተነስቼ ኢትዮጵያን እንዳስተዳድር በትረ ኃይል የሆነኝ እግዚአብሄር ነው" እያሉ አጥብቀው ይናገሩ ነበር። ሆኖም አንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች የካሣ እናት ኮሶ ይሸጡ ነበረ እያሉ የጻፉት ሁሉ በኩሸት ላይ የተመሠረተ ለመሆኑ መነሾው እንደሚከተለው ነው።

ወይዘሮ አትጠገብ በውይ ደጋ ወረዳ፣ በአውሊድ ማርያም ሰባን ከአሉት ተወላጆቻቸው ጋር በመሬት ጉዳይ ሲከራከሩ ነበር። እሳቸው ይከራከሩበት የነበረው ቦታ "ኮሶ ሽሻየ" ወይም "ኮሳየ" በመባል ይጠራ የነበረው መሬት ድርሻቸው ሆነ። አንድ ቀን በውርስ የደረሳቸውን ይህን መሬት ሲያስመነጥሩ፣በመሬቱ መሐከል ትልቅ የኮሶ ዛፍ አዩ። እሳቸው ኮሰውን እንደ አበባ ቆጥረው ሳያስመነጥሩ ተውት። በዓመቱ መሬታቸውን ለማየት ሲሄዱ ዛፉ አብቦና ፍሬ አፍርቶ አገኙት። ወደ ጎንደር ሲመለሱ አብራቸው የነበረችው ገረዳቸው የኮሰው ፍሬ ደስ ስላላት፣ጥቂት የኮሶ እሸት ሰብስባ በጨርቅ ቋጥራ ወደ ጎንደር ይዛ መጣች።

ከወይዘሮ አትጠገብ ጋር የመሬት ክርክር የነበራቸው ባላንጣዎቻቸው፣ገረዳቸው ኮሶ መያዟን ሲያዩ፣ወይዘሮ አትጠገብ ኮሶ ትሸጣለች የሚል ወሬ ማናፈስ ጀመሩ። ደጃዝማች ወንድራድ ለሞት የበቁት ይህን ወሬ እንደ እውነት ቆጥረው በፈጸሙት ስህተት ነው። ቀደም ሲል ከገሪማ ታፈረ ጽሑፍ ካነበብነው እንደተረዳነው፣የወይዘሮ አትጠገብ የዘር ግንድ ከመሳፍንት ወገን መሆኑን እና የተደላደለ ኑሮ እንደነበራቸው ነው። ከዚህ የታሪክ ማስረጃ አኳያ ሲታይ፣የካሣ እናት ኮሶ እየሸጡ ልጃቸውን አሳደጉ መባሉ ተቀባይነት አይኖረውም።



ምክንያቱም፣ የካሣና የወይዘሮ አትጠገብ ቤተሰቦች ሀብት ብዙ ነበር ባይባል እንኳን፣አንድ ልጃቸውን (ካሣን) ለማሳደግ ወረት አልባ ነበሩ ማለት ስለማይቻል ነው። ሌላውና ዋናው የአሉባልታው ምንጭ፣ከነገሥታት እንወለዳለን፣የታላላቅ መሳፍንት ልጆች ነን፣ወይም መኳንንቶች እና ወይዛዝርት ነን የሚሉትን ተሽንቀዳሪዎች ካሣ ስላማይወዷቸው፣ በዓል ሲደረግ እንኳን የደስታቸው ተካፋይ እንዲሆኑ አለ መፍቀዳቸው ነበር*። ይልቁንም ወታደሮቻቸውንና ከዝቅተኛ ቦታ ተነስተው ለማዕረግ የበቁትን ባልደረቦቻቸውን ይበልጥ ያከብሩ ነበር።

በዚህ ላይ ደግሞ እሳቸው ለትኅትና ብለው "እግዚአብሄር ከትብያ አንስቶ የኢትዮጵያ መሪ አደረገኝ" ያሉትን እውነት የመሰላቸው ነበሩ። ይህ ሁሉ ተዳምሮ፣የካሣ እናት ኮሶ እየሸጡ አንድ እና ብቸኛ ልጃቸውን አሳደጉ የሚለው አሉባልታ በመፋፋሙ፣ሐቁን ለመቀበል በተቸገሩ ታሪክ ጸሐፊዎች ነው። ዛሬም ይህንኑ እውነት መስሏቸው የሚጽፉ አልጠፉም።

ከዚህ ከፍ ብሎ እንዳነበብነው ለደጃዝማች ወንድ ይራድ ሞት ምክንያት በሆነው ጦርነት ሠራዊታቸው መሸነፉን እቴጌ መነን እንደሰሙ እንደገና ኅዳር ፲፪ ቀን ከፍተኛ ቁጥር ያለው ጦር ላኩባቸው። የካሣ ጦር ቀደም ብሎ በማረከው መሣሪያ ተጠናክሮ ነበር እና ከእቴጌ የተላከውን ጦር፣ሰቀላ ወርካ ከተባለ ቦታ ገጥሞ በቀላሉ ድል አድርጎ በታተነው።

ለሁለተኛ ጊዜ ሠራዊታቸው በካሣ ጦር መሸነፉን የሰሙት እቴጌ መነን ሃያ ሺሕ ጦር አስከትለው እና ራሳቸው የጦር መሪ ሆነው በካሣ ላይ ዘመቱ። ለጊዜው የእቴጌይቱ ጦር በማየሉ፣የካሣ ሠራዊት ወደ መሸነፍ ሲቃረብ፣በካሣ ቀስቃሽነት ሠራዊቱ በርትቶ ስለ ተዋጋ እቴጌ መነን ጭናቸው ላይ በጦር ተወግተው ወደቁ። ከዚያም የካሣ ሠራዊት በጦሩ መሐል እየተዘዋወረ እቴጌ መነን ቆስለው መማረካቸውን ለፈፈ። ለፈፋውን የሰማው የእቴጌ ሠራዊት፣ተደናግጦ ስለሸሸ ድሉ የካሣ ሆነ። የእናታቸውን መማረክ የሰሙት ራስ ዓሊ እቴጌዪቱ እንዲፈቱላቸው ከጎጃም አድባራት ፴ ቀሳውስት መርጠው ወደ ካሣ በአማላጅነት ላኩ።

ካሣ መልክቱን ሲሰሙ በበኩላቸው "የወንድሜ የደጃዝማች ክንፉ ግዛት የነበረውን አገር ሁሉ ይልቀቁልኝ እና እኔም እቴጌ መነንን ከእስር ፈትቼ እልካለሁ"* የሚል መልስ ሰጡ። የካሣን መልክት ራስ ዓሊ ሲሰሙ ስል አልተደሰቱ ምንም ድርድር ለማድረግ አልፈለጉም ነበር። እቴጌ መነን የልጃቸውን የራስ ዓሊን ውሳኔ ሲሰሙ በእጅጉ አዘኑ። በዚህም የተነሳ " ከዚህ መጥፎ ቦታ በሰላም እንጂ በጦርነት ልታገኘኝ አትችልም" ብለው ለራስ ዓሊ መልክት ላኩ። ራስ ዓሊም፣ሌላ አማራጭ ስላልነበራቸው የእቴጌ መነንን ጥያቄ ተቀብለው፣ካሣ በጠየቁት የእርቅ ድርድር ተስማምተው፣የሙሉ ደንቢያ፣የቋራ እና ከፍርቃ በር እስከ አርማ ጨሆ ድረስ የሚገኘው አገር ሁሉ ገዢ ብለው ሾሟቸው። ካሣ ሹመቱን ካገኙ በኋላ እቴጌ መነን ከእስር ቤት ተለቀቁ*። ካሣም ከራስ ዓሊ ጋር ታረቁ።

ካሣ፣ ግዛታቸውን እሳቸው በሚፈልጉት አካሄድ ማስተዳደር የጀመሩት፣ሌባ እና ሽፍታ ለማጥፋት አቀድው በመነሳት ነበር። በግዛታቸው ላይ የበላይ ሹም ባለመኖሩ ፈላጭ፣ቆራጭ ሆኑ። እልገዛም ያለ ተቃዋሚ ሲገኝ አሳድደው በመያዝ እግሩን እና እጁን እያስቆረጡ ገደል ይከቱት ጀመር። ይህን አድራጎት የሰሙት ራስ ዓሊ ተናድደው ካሣ ወደ እሳቸው ዘንድ እንዲመጡ መልዕክተኛ ላኩ። ካሣ ግን ጊዜው ክረምት ነውና በበጋው እመጣለሁ የሚል መልስ ሰጡ።

በዚህ መልሳቸው ተናድደው፣ራስ ዓሊ ደጃዝማች ካሣን ሽረው ግዛቱን ለጎጃሙ ገዥ ለደጃዝማች ጎሹ መስጠታቸውን በኅዳር ወር ፲፰፻፴፰ ዓ.ም. በአዋጅ አስነገሩ። ቀጥሎም ራስ ዓሊና ደጃዝማች ጎሹ በአንድነት ሁነው፣ደጃዝማች ካሣን ለመውጋት አብረው ዘመቱ። ካሣም እነዚህ ሁለቱን ታላቅ መኳንንት በአንድነት ለመዋጋት ስለአልፈለጉ ወደ ትውልድ ቦታቸው ወደ ቋራ ሄዱ። ራስ ዓሊ የካሣን አለ መኖር ሲሰሙ ጦራቸውን ይዘው ወደ መጡበት ተመለሱ። በእሳቸው ላይ ለመዝመት የተላከው ጦር መመለሱን ደጃዝማች ካሣ ሲያውቁ፣ከሄዱበት ቦታ ተመልሰው ወደ ጉር አምባ ወጡ። የደጃዝማች ካሣን እንደገና መነቃነቅ የሰሙት ደጃዝማች ጎሹ ጦር አሰባስበው እንደገና መጡና ኅዳር ፲፱ ቀን ጉርጉም ላይ ጦርነት ገጠሙ።



የደጃዝማች ጎሹ ጦር አይሎ የካሣ ጦር ማፈግፈግ ሲጀምር፣ካሣ ከጥቂት ወታደሮቻቸው ጋር ከጦሩ መሐል ገብተው ሲዋጉ ደጃዝማቹ ጎሹ በጥይት ተመትተው ሲወድቁ፣ድሉ የደጃዝማችነት ጎሹ መሆኑ ቀርቶ በደጃዝማች ካሣ አሸናፊነት ተቋጨ። በዚህ ጦርነት ላይ ደጃዝማች ካሣ ብዙ ሀብት እና መሣሪያ ማረኩ።

ከዚህ ድል በኋላ አባ ታጠቅ ካሣ ከጎንደር እስከ ወሎ እና ሸዋ ያሉትን መሳፍንት በየተራ እየወጉ ማስገበር ጀመሩ። አልፎ አልፎ አልገብርም ያለ መስፍን ሲነሳ አገሩን ወርረው መንደር አቃጥለው የወጋቸውን አገሬ እጅና እግር እየቆረጡ ገደል ይጥሉ ጀመር። ይህ ድርጊት በርካታ ተቃሚዎች በፍርሃት እንዲርዱ አደረገ። ያም ሆኖ የራስ ዓሊና የእቴጌ ጦር ወደ አይሻ መጥቶ ከካሣ ጋር ጦርነት መግጠሙ አልቀረም ነበር።

አይሻ ላይ በተደረገው ጦርነት የራስ ዓሊ ሠራዊት ድል ተመትቶ እቴጌዪቱ ለሁለተኛ ጊዜ የአባ ታጠቅ ካሣ ምርኮኛ ሆኑ። የየመሳፍንቱ ጦር ሊመክታቸው ያልቻለው የድሉች ሁሉ ባለቤት አባ ታጠቅ ካሣ፣የካቲት ፬ ቀን ፲፰፻፵፯ ዓ.ም. ዳግማዊ ቴዎድሮስ ተብለው ከአቡነ ሰላማ እጅ ቅብዓተ መንግሥት ተቀብለው በደረስጌ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ ተቀዳጁ*። (ገሪማ ታፈረ በጻፉት መይሳው ካሣ፡ የቋራው አንበሳ በሚባለው መጽሐፍ ዐፄ ቴዎድሮስ በ፲፰፻፵፯ ነገሡ ብለው መዝግበዋል።)

ኢትዮጵያን ከመሳፍንት አገዛዝ አላቅቀው ማዕከላዊ መንግሥት መሠረቱ። በቴዎድሮስ መንገሥ ፲፫* ዓመት ሙሉ ሰፍኖ የነበረው የመሳፍንት ዘመን በአይሻ ጦርነት ተደመደመ። በሃይማኖት፣በጎሳና በባህል ሰበብ፣ሕዝቡን ሲያራርቅ የነበረው የመሳፍንት ሥርዓት አከርካሪው ስለተሰበረ፣ዐፄ ቴዎድሮስ፣የመንግሥታቸው አስተዳደር ዘመናዊ ፈር እንዲይዝ በማሰባቸው የሚከተለውን ሕግ በአዋጅ አስነገሩ*።

መጀመሪያ:-"እናት አባት ያለህ፣በየግዛትህና በየአባትህ ግባ፣ አባትና ግዛት የሌለህ ግን እኔ አባት እሆንሀለሁ፣ ግዛትም እሰጥሀለሁ" አሉ።

---

* ያሬድ ግርማ ኃይሌ:- የጎንደር ታሪክ

ቀጥለውም:-

1. ከአሁን በፊት የነበረ ሃይማኖት ክርስትያን በክርስትያንነቱ፣እስላምም በእስላምነቱ ፀንቶ እንዲቀመጥ:: ነገር ግን ክርስትያን ከአንድ ሐይማኖት ወጥቶ ሌላ ሃይማኖት ተከትሎ፣ እስላሙም ከእስልምናው ሌላ አዲስ የእስልምና ሃይማኖት ይዞ ቢገኝ፣ አስተማሪውም ተማሪውም አንገቱን በሰይፍ ይቆረጣል፣ደረቱም በጦር ይወጋል፣
2. ክርስትያን የሆነ ሁሉ ከአንዲት ሴት በቀር ሌላ አግብቶ ቢገኝ ሀብቱን ሁሉ እንዳለ ለመጀመሪየያ ሚስቱ ጥሎ እንዲወጣ እና ርስትም ሆነ ሹመት እንዳይሰጠው፣
3. ከጥንት የቆየው የቄስና የደብተራ የመሬት ግብር እንደነበረ ሆኖ ይቆያል፣
4. የቤተ መንግሥት ባለሥልጣኖች በዕለት ተግባራቸው በደሞዝ እንዲሠሩ እንጅ ባሪያ መግዛትና መሸጥ እንዳይፈፅሙ፣ሲሸጡና ሲገዙ ቢገኙ እንደ ነፍሰ ጌዳይ በአደባባይ እንዲሰቀሉ ወይም በግዞት እንዲኖሩ፣
5. የቤት, ሠራተኞች፣ገረድና አሽከሮች ወድደው በነጻም ሆነ በደሞዝ ቢያገለግሉ እና ከአሠሪያቸው ጋር ተጣልተው ቢወጡ በውላቸው መሠረት ይጸድቃል፣
6. ማንኛውም የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙያው እንዲሰለፍ፣ ገበሬም በግብርናው፣ ነጋዴም በንግዱ እንዲተዳደር፣
7. ገበሬው ከጥንድ በሬ በላይ የሚያርስና ነጋዴ ከአጋሰስ ጭነት በላይ የሚነግድ ግብር እንዲከፍል፣ ነገር ግን በትከሻው ተሸክሞ የሚነግድና ቆፍሮ የሚዘራ ገበሬ ግብር ክፈል፣ መዋጮ አዋጣ ተብሎ እንዳይገደድና እንዳይከፍል፣

ከዚህ ከፍ ብሎ ከአወጡት አዋጅ በተጨማሪ ለኢትዮጵያ አንድነት፣ ዕድገት እና ከነበራቸው የማያወላውል ዓላማ የሚከተሉትን ተግባራት ፈፅመዋል::

* የፊውዳል ባላባቶችን እና የመሳፍንት ኃይልና ሥልጣን ገደቡ፣
* የጦር ኃይላቸውን አደረጃጀትና ትጥቅና ሥርዓት አስያዙ፣
* ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ተጣጣሩ፣
* የቱርኮችን የመስፋፋት ፖሊሲ ለመግታት ከእንግሊዝና ከፈረንሳይ መንግሥታት ጋር የወዳጅነት መረብ ዘረጉ፣
* ለሠራዊታቸው መሪዎች የሹመት እርከን አወጡ፣ (አሥር አለቃ፣ሃምሳ አለቃ፣መቶ አለቃና ሻለቃ)



ዐፄ ቴዎድሮስ ለአገራቸው በጎ በመመኘት የሚፈጽሙትን ተግባራት ለማደናቀፍ፣ በየጎጡ ተቃዋሚዎች እየተነሱ ስላስቸገሯቸው፣መንፈሳቸው ተረብሾ የጭካኔ ተግባር ለመፈፀም ተገፋፉ:: በዚህ ምክንያት እንገዛም እያሉ በየጊዜው እየተዋጓቸው ተሸንፈው በእስር ከነበሩት መሐከል የሚከተሉትን መኳንንት መቀጣጫ እንዲሆኑ በማለት በመጀመሪያ እግራቸውን ከአስቆረጡ በኋላ በስቅላት ቀጧቸው:: በግንቦት ወር ፲፰፻፶፱ ዓ.ም. ቅጣቱ የተፈፀመባቸው መኳንንት ስም ዝርዝር የሚከተለው ነው:: ዋግ ሹም ገብረ መድኅን፣ቢትወደድ ብሩ አባ ጫጉ፣አሰኔ ድረስ፣ገልሞ ወልደ ሚካኤል እና ማሩ ሰለሞን:: ይህን ቅጣት ባስፈፀሙ በሦስተኛው ወር ዐፄ ቴዎድሮስ መሪር ኀዘን እንደ ደረሰባቸው ገሪማ ታፈረ፡ መይሳው ካሣ፣የቋራው አንበሳ በሚለው መጽሐፍ እንደሚከተለው ገልጠውታል::

"የመከራ ጓደኛቸው፣የሐሳብ ረዳታቸው፣የድል ማዕረግ በር የከፈቱላቸው እጅግ በጣም የሚያፈቅሯቸው እቴጌ ተዋበችን ነሐሴ ፲፫ ቀን ፲፰፻፶፱ ዓ.ም. ሞት ነጠቃቸው::" በወቅቱ ዐፄ ቴዎድሮስ፣የሥልጣን ተቀናቃኛቸውን **ዓመዴ** በሽርን በማሳደድ ላይ ነበሩ:: በዚህ ምክንያት፣የእቴጌዪቱ አስከሬን በጉዞ ላይ ስለ ነበረ በሞቱ በሁለተኛው ወር ፲፰፻፶፩ ዓ.ም. በጥቅምት ፲፩ ቀን በግሸን ማርያም አምባ አሳረፉት:: የዐፄ ቴዎድሮስ ጠባይ እየተለወጠና እየከበደ **መሄድ የጀመረው** የቃል ኪዳን ሚስታቸው እቴጌ ተዋበች ከዚህ ዓለም በሞት **ከተለዩበት ዘመን** ጀምሮ ነው ይባላል:: ምክንያቱም እቴጌ ተዋበች ለካሣ **መንገሥ የድካሙ** ተካፋይ በመሆናቸውና በእቴጌነታቸው የማይኰሩና የማይመኩ ስለ ነበሩ ነው:: ይልቁንም እንደ እናት በርኅራኄ፣እንደ እህት በመምከር፣እንደ ገረድ በባልትና የሚረዷቸው እና የሚያገለግሏቸው እሳቸው ብቻ ነበሩ:: ከሽፍትነት እስከ ዘውድ መጫን (መቀዳጀት) በተደረገው ትግል በማደፋፈር እና በማበረታታት ብርቱ መከታ እና ጋሻ የሆኗቸው እቴጌ ተዋበች ነበሩ:: ከዚህም አልፎ በጣም ይፈቃቀሩ እና ይከባበሩ ነበር::

ለባለቤታቸው የነበራቸው ከፍተኛ ፍቅርና አክብሮት የነበራቸው መሆኑን ዐፄ ቴዎድሮስ የጻፉት የኀዘን እንጉርጉሮ ገላጭ ነው::

ብዙ ሥራ ዐዋቂ ትናንት ተቀበረች
መድኀኒትን ምሳ ታበላኝ ነበረች
እስቲ ጠይቁልኝ ርቃ ሳትሄድ
እቴጌ ተዋበች ሚስት ናት ገረድ?

ዐፄ ቴዎድሮስ ሥልጣኔ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ አልመው ስለነበረ ጎዘናቸውን አምቀው የቴክኒክ ሙያ ያላቸው ፈረንጆች ወደ አገሪቱ እንዲገቡ በእጅጉ ሞከሩ:: በዚህ በኩል የእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶሪያ እንዲረዷቸው በማሰብ፣በእንግሊዙ ቆንሲል ካፒቴን ካሜሮን በኩል ደብዳቤ ጽፈው ላኩ:: በተጓዳኝም በሚስዮናዊነት ስም ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ለነበሩት ፈረንጆች ጋፋት ከሚባል መንደር ሰፊ መሬት በነፃ ሰጧቸው:: በተጓዳኝም በሚስዮናዊነት ስም ወደ ኢትዮጵያ ገብተው የነበሩ ፈረንጆቹ የራሳቸውን ቤት ሠርተው መኖር ጀመሩ::

አብዛኛዎቹ ፈረንጆች ሚስዮናዊያን ስለ ነበሩ ሃይማኖት መስበክ ያዘወትሩ ነበር:: ከፈረንጆቹ መሐከል ብረት የማቅለጥ፣የመቀጥቀጥ እንዲሁም የመንገድ ሥራ ሙያ ያላቸውም ነበሩ:: ቀደም ሲል ዐፄ ቴዎድሮስ የፈረንጆቹን የሥራ ችሎታ አይተው ነበርና አንድ ቀን ሁሉንም ጠርተው "ለአገሬ የሚያስፈልጋት ጠርቅ ማንጠር፣ብረት ማቅለጥ የሚችል ባለ ሙያ እንጂ ወንጌል የሚሰብክ አይደለም:: ሃይማኖት ለመስበክ ከሆነማ በአገሬ ውስጥ በርካታ ሊቃውንት አሉ:: ስለዚህ እናንተ በእጅ ሥራ በኩል አገሬን እንድታገለግሉ እፈልጋለሁ::

ለዚህም ፈቃደኛነታችሁን ግለጡልኝ"* አሉ:: ፈረንጆቹ ሥራውን ለመሞከር ፈቃደኞች ስለሆኑ ስለሥራቸው አመቺ የሆነ ሰፊ ቤት ጋፋት ላይ ሠርተው የብረት ማቅለጥና የመቀጥቀጥ ሥራ ጀመሩ:: ከዚያም በአጭር ጊዜ ውስጥ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች ሠሩ:: ዐፄ ቴዎድሮስ ሚስዮናውያኑ የሠሩትን ሲያዩ በእጅጉ ተደሰቱ:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ፈረንጆቹ ልዩ ልዩ ምክንያት በመፍጠር ወደ አገራችን ደርሰን እንመለስ የሚል ጥያቄ በማቅረብ ያስቸግሩ ጀመር:: ከዚህም የተነሳ የተጀመረው ሥራ እንዳይቋረጥ ዐፄ ቴዎድሮስ በጣም ሰጉ:: ምክንያቱም ፈረንጆቹን ፈቃድ ቢከለክሏቸው ሥራውን በሙሉ ልብ የማይሠሩ መሆናቸውን ተረድተዋል እና ነው::



ሚስዮናውያኑ ወደ አገራቸው ለመሄድ ጥያቄ ያቀረቡት ከዘመድ ናፍቆት የተነሳ መሆኑንም ገመቱ:: ለዚህ መፍትሄው ሚስት የሌላቸውን ሁሉ፣ከኢትዮጵያ ሴቶች ጋር ትዳር እንዲመሠርቱ ቢያደርጉ የሚሻል መሆኑን አምነው፣ሐሳባቸውን ወደ ተግባር ለመለወጥ ወሰኑ::

ሐሳባቸው ተቀባይነት እንዲያገኝ፣የወንድማቸውን የደጃዝማች ክንፉን ሴት ልጅ ለካፒቴን ቤል ዳሩለት:: ሌሎቹ ፈረንጆችም ልባቸው የፈቀዳትን ኢትዮጵያዊ ሴት እየመረጡ ትዳር መሠረቱ:: ፈረንጆቹ ትዳር ከመሠረቱ በኋላ ደስተኛ ስለሆኑ፣ቀስ በቀስ ጋፋት፣የአውሮፓ የገጠር ከተማ መልክ እንዲኖራት ሆና ተከተመች:: ፈረንጆቹ ጋፋት ውስጥ የሠሯቸውን ቤቶችና ቁሳቁስ ቴዎድሮስ ሲጎበኙ፣በአዩት ሁሉ በጣም በመደሰታቸው፣ለያንዳንዱ ባለትዳር ቤተሰብ መቋቋሚያ የሚሆን የገንዘብ እና የቁሳቁስ የማበረታቻ ስጦታ አበረከቱ:: እንደዚህ አድርገው ካስደሰቷቸው በኋላ፣አንድ ቀን ፈረንጆቹን ሰብስበው መድፍ እንዲሠሩላቸው ጠየቋቸው::

ፈረንጆቹ መድፍ ለመሥራት የሚያስችል ዕውቀት የለንም በማለት በጥሞና ነገሯቸው:: ፈረንጆቹ የነገሯቸው እውነት ነው ብለው ስላልተቀበሏቸው መድፍ ለመሥራት እንዲሞክሩ አጥብቀው ጠየቋቸው::

ፈረንጆቹ በበኩላቸው ንጉሠ ነገሥቱ የጠየቋቸውን አንሠራም ቢሉ፣ሊጣሏቸው እንደሚችሉ ገምተው ሥራውን ለመሞከር ፈቃደኞች ሆኑ:: ወዲያው ደግሞ ብረት የማቅለጥ ሥራ ጀመሩ:: ከዚያም በቅርጽ ላይ በማፍሰስ በመጀመሪያ የመድፉ አካል፣ቀጥሎም፣ማስፈንጠሪያው እና እርሳስ (ጥይት) ተሠራ:: መድፉ ተገጣጥሞና እርሳሱም አብሮ መዘጋጀቱን ካሣ ሲያዩ በጣም ተደሰቱ:: እሳቸው የአገራቸው ልጆች የቴክኒክ ሙያ በመማር፣ለአገር እድገት እንዲሠሩ ምኞት ነበራቸውና የመድፍ ሥራ ዘዴን ቶሎ ለመቅሰም ብቁ እና ንቁ ናቸው የተባሉትን ወጣቶች መልምለው አዘጋጁ:: እነዚያ ልጆች ከፈረንጆቹ ጋር ሆነው የመድፍ አሠራሩን ዘዴ እንዲመለከቱና ልምምድ እንዲያደርጉ አደረጉ::

ፈረንጆቹም በእነዚህ ኢትዮጵያውን በመታገዝ ብረት በማቅለጥ እና ቅርጽ ላይ በማፍሰስ አሥራ አምስት ትልልቅ እና ትንንሽ መድፎች ለመሥራት በቁ። ትልቁ መድፍ ተሠርቶ ከአለቀ በኋላ የምረቃ በዓል ተዘጋጅቶ ስለ ነበረ ቴዎድሮስ በቦታው እንዲገኙ ለመኗቸው። በበዓሉ ቀን ከቦታው ሲደርሱ የመድፉ አፍ ሰው ወደሌለበት አቅጣጫ ዞሮና ተደግኖ ቆያቸው። መድፍ ተኳሾቹ ቀርበው ለመተኮስ ሲሞክሩ መድፉ ሳይተኩስ ቀረ። የመድፍ ተኩሱ በመክሸፉ ፈረንጆቹ ደንግጠው ሲንቀጠቀጡ ስለ ነበረ፣ አይዟችሁ አትስጉ፣ አሁን ቢበላሽ ነገ መልሳችሁ ትሠሩታላችሁ በማለት ምክር ሰጥተው አጽናኗቸው።

ቀጥሎም ወደ ምስል ማፍሰሻ ቦታው ቀርበው ሲመለከቱ፣ቅርፅ ማውጫው ውስጥ ውሀ ገብቶበት አዩ። መሐንዲሱን ጠሩና ጉድለቱ ይህ ብቻ መሆኑን አስረድተው ውሀው ተጠርጎ እንደገና እንዲሠራ አዘዙት። እሳቸው እንዳሉትም ውሀው ተጠርጎ አዲስ መድፍ ተሠርቶ ሙከራ ሲደረግ ልክ እንደተፈለገው ተተኮሰ።

በዚህ ምክንያት የጋፋት ሰዎች በዐፄ ቴዎድሮስ ብልህነት አጥብቀው ተደነቁ። የመድፍ ሥራው በዚህ መልኩ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ለመድፉና ለሌላም ዕቃ መጫኛ የሚሆን ጋሪ እንዲሠሩ አደረጉ።

ፈረንጆቹም ተረባርበው ፲፱ ጋሪዎችን ሠሩ። በዓሉም ዐፄ ቴዎድሮስ በአሉበት በሌላ ቀን እንዲከበር ተወሰነ። ዐፄ ቴዎድሮስ የመድፉ እና የጋሪዎቹ ሥራ መሳካቱን ከአዩ በኋላ፣ይህን የመሰለ የቴክኒክ ሙያ እና ሌላም ዕውቀት ወደ አገራቸው ለማስገባት ከፈረንሳይ እና ከእንግሊዝ መንግሥት እርዳታ ጠየቁ። ይሁን እንጂ ከእነዚህ መንግሥታት አጥጋቢ መልስ ሳያገኙ ቀሩ። በዚህ ላይ ደግሞ፣ቆንሲል ፕላውዴንና ስተርንን የመሰሉ የእንግሊዝ ዜጎች የቴዎድሮስን ክብር የሚነካ መጽሐፍ ጽፈዋል የሚል ወሬ ሰሙ።



የእሳቸውን ስም የሚያጎድፍ ዘገባ በመጽሐፍ አሳትመው ማውጣታቸው ዐፄ ቴዎድሮስን በእጅጉ አናደዳቸው። ስተርን ጻፈ የተባለው የተሰመደው እናታቸው ኮሶ ሻጭ ናቸው ማለቱ ብቻ አልነበረም። "ከነገሥታት ዘር የሌለው፣መጥፎና ሾካካ፣ደም የጠማው የዱር አውሬ ነው*" የሚል ሐረግ አክሎበታል።

ዐፄ ቴዎድሮስ ይህን የመሰለ የስድብ ቃል ጽፏል መባሉን በሰሙ ሰሞን እነስተርን ወደ አገር መግባት በሰሙ ጊዜ፣ወደ ደብረ ታቦር አስጠሯቸው እና መጡ። "እዚያ የነበሩትን አውሮፓውያን ከሜዳ ላይ እንዲሰበሰቡ አድርገው እሳቸውም ከአንድ ድንጋይ ላይ ቁጭ አሉ። በያዙት የጦር ጅንፎ ድንጋዩን እየደበደቡና እየሰባበሩ ወደ ስተርን እየተመለከቱ፣

«የክርስቲያን ነው የአረመኔ ወይስ የይሁዲ ባህል ነው እንድትሰድበኝ የሚፈቅድልህ? ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሆነ በየትኛው ሥፍራ ላይ ነው ሰውን እንድታዋርድ የሚፈቅድልህ? እንዲያው ለመሆኑ መጽሐፉን ስትጽፍ ፈቃድ የሰጠህ ማነው? ኧረ እንደው ማነው! ይህን እኔን የሚያንቋሽሽ ታሪክ የነገረህ? በል ንገረኝ" አሉ። "ስተርን ለመመለስ ሲዘጋጅ፣ቴዎድሮስ ወደ ራሳም ዞር አሉና «አንተም ብትሆን በድለኸኛል» ብለው ሊነግሩት ሲጀምሩ፣ራሳም ከፉኛ ደንግጦ ከንግግራቸው መሐል ገባና «እኔ? ጃንሆይ እኔ?» አላቸው።

አጤ ቴዎድሮስም «አዎ አንተ፣አንተ ራስህ። ያውም የበደልከኝ አራት ጊዜ ነው። አንደኛ ኮከቤ እኔን ሰድቦና አዋርዶ የጻፈውን መጽሐፍ አነበብከው። ሁለተኛ ነገር፣ከእስረኞቹ ጋር ሳታስታርቀኝ ከአገር እንዲወጡ አድርገህ ልታስወጣቸው ነበር። ሦስተኛው በደል፣ያንተ አገር መንግሥት፣ኢየሩሳሌም በቱርኮች እንደተያዘች እንድትቆይ ፈቃዱ ሆነ። አራተኛው ምን ነበር? ይሁን ብቻ አሁን ረስቼዋለሁ። ግን የምልህ! ኢየሩሳሌም የእኔ መሆኗን ታውቃለህ? በዚያም ያለው ጽላት በቱርኮች መያዙንም ታውቃለህ? ወይስ አላውቅም ልትል ነው?" ብለው ለጥቂት ጊዜ ዝም አሉ*። ወዲያው ዐፄ ቴዎድሮስ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም የሁለቱ ሰዎች ጉዳይ በችሎት እንዲታይ አዘዙ። ችሎቱ፣ጎንደር ከተማ ውስጥ ከሰፊ ሜዳ ላይ እንዲካሄድ ተደረገ።

---

* ጳውሎስ ኞኞ፡- «አጤ ምኒልክ

በችሎቱ ቀን፣በሺሕ የሚቆጠሩ ተመልካቾችና በኢትዮጵያ የሚኖሩ ፈረንጆች በተገኙበት ዐፄ ቴዎድሮስ ከዚህ በታች ያለውን ቃል ተናገሩ፡፡

> እናንት የአውሮፓ ሰዎች፣ወደ አገሬ ስትመጡ በታላቅ ፍቅር እና ክብር ተቀብዬ አኖራችኋለሁ፡፡ ይህንንም የማደርገው የአውሮፓ ሰዎች ሁሉ እንደ ወዳጄ ዮሐንስ ቤል እየመሰለኝ ነው፡፡ ዮሐንስ እውነት ተናጋሪ ነበር፡፡ እናንተ ግን ውሸታሞች ናችሁ፡፡ መልካም ሳደርግላችሁ እናንተ በመጥፎ ተግባር መለሳችሁልኝ፡፡ ወደ አገራችሁ መልክት ስትልኩ እኔን የሚያጥላላ ነገር ትጽፋላችሁ፡፡ በዚህም በዓለም ላይ መጥፎ ስም አሳጣችሁኝ፡፡ በእኔ እና በእናንተ መሐል ስለ አለው ጉዳይ እግዚአብሔር ፍርዱን ይስጥ፡፡

ችሎቱ ተጀምሮ ተከራካሪዎቹ የየራሳቸውን ሃሳብ አቅርበው ሲጨርሱ ከፍትሀ ነገሥቱ ውስጥ ችሎታን በተመለከቶ ውሳኔ ሊያሰጥ የሚያስችል አንቀጽ ተመርጦ ተነበበ፡፡

ቀጥሎም ብይን እንዲሰጥ ሲጠየቅ፣ችሎቱ ስተርን እና ሮዘንታል በስቅላት እንዲቀጡ በአንድ ድምፅ ፈረደ፡፡ ወዲያው ፈረንጆቹ ቀርበው እየተመለከቱ የመስቀያ እንጨት ይዘጋጅ ጀመር፡፡ በዚህን ጊዜ፣ዐፄ ቴዎድሮስ የሚወዱት እና የሚያከብሩት ሚስዮናዊው ዎልድሜየር በኀዘን እና በትካዜ ወደ ንጉሡ ዘንድ ቀርቦ፣ተንበርክኮ እያለቀሰ ለሁለቱ ሰዎች ምሕረት ጠየቀላቸው፡፡ እሳቸውም የዎልድሜየርን እጅ ይዘው ብድግ አደረጉትና "አይዞህ፣ለአንተ እና ለዮሐንስ ቤል ስል አልገድላቸውም" በማለት ሮዜንታል እና ስተርን በእግር ብረት እንዲታሰሩ አዘዙ*፡፡ ፈረንጆቹ በሚነዙት አሉባልታ ምክንያት፣ዐፄ ቴዎድሮስ ለአውሮፓውያን ያላቸው ፍቅር እና አክብሮት ስለ ተሟጠጠ፣ቂም የያዙባቸውን ፈረንጆቹን ሁሉ አሰሯቸው፡፡ የንግሥት ቪክቶሪያን ደብዳቤ ይዘው መልክተኞች ሲመጡ፣እሳቸው ሰዎቹን ለመፍታት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ፡፡ ይሁን እንጂ እስረኞቹ በየጊዜው እየተፈቱና ተመልሰው እየታሰሩ ከቆዩ በኋላ በመጨረሻ፣ፈረንጆችና አምስት መቶ የሚሆኑ ጎንደሬዎች አስረው፣ሐምሌ ፳ ቀን ፲፰፻፶፰ ዓ.ም. ወደ መቅደላ አፋፍ ላይ ይዘዋቸው ሄዱ፡፡



ለፈረንጆቹ መታሰር ምክንያት የሆነው ዐፄ ቴዎድሮስ ለንግሥት ቪክቶሪያ ለጻፉት ደብዳቤ እስከ እዚያን ጊዜ ድረስ ምንም መልስ ባለ መምጣቱ ነው፡፡ ቀስ በቀስ የፈረንጅ እስረኞቹ ቁጥር ወደ ፳፩ አሻቀበ፡፡

በእንግሊዞች በኩል ደግሞ አሁንም ተጨማሪ ሰዎች በመታሰራቸው እስረኞቹ በሙሉ ይፈቱ የሚል ውትወታው አየለ፡፡ የእስረኞቹ ጉዳይ እንደዚህ እየከረረ በመሄዱ በእንግሊዝ አገር ከፍተኛ ክርክር አስነሳ፡፡ በአንድ በኩል፣ኮለኔል ሜርዌዘር ሲናገር "የሚሻለው ጦር ማወጁ እንጂ ከእንግዲህ ወዲያ ቴዎድሮስን መለማመጥ የእንግሊዝን መንግሥት ክብር ማዋረድ ነው"* የሚል ሃሳብ አቀረበ፡፡ በሌላ በኩል፣በእንግሊዝ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ተጠንቶ የቀረበው ሃሳብ ደግሞ "ቴዎድሮስ ለጻፉት ደብዳቤ እና ጥያቄ መልስ ሰጥቶ መሞከር ይሻላል" የሚል ሆነ፡፡ ይህን መሰል ክርክር ከተካሄደ በኋላ፣የመጨረሻው ሐሳብ ተቀባይነት ስለ አገኘ፣ታልቦት የሚባል ሲቪል ኢንጂኔርና ስድስት የእጅ ጥበብ ሥራ ሙያተኞች እና ሚስተር ፍላድ ወደ ዐፄ ቴዎድሮስ ዘንድ ተላኩ፡፡ ፍላድ ከእንግሊዝ አገር ከመነሳቱ በፊት የተሰጠው ትዕዛዝ "ምፅዋ መድረሱን ለቴዎድሮስ አሳውቆ፣ እስረኞቹን ሳይረከብ፣እነዚያን ባለሙያዎች ወደ መቅደላ እንዳይልክ ወይም እሱ ራሱ ይዟቸው ወደ መቅደላ እንዳይሄድ" የሚል ነበር*፡፡ እስረኞቹ በቅድሚያ ካልተፈቱ በስተቀር ባለሙያዎቹን እንዳይልክ ወይም እሱ ይዟቸው እንዳይሄድ መከልከሉን የሚገልጽ ወረቀት ጽፎ ከእንግሊዝ መንግሥት የተላከውን ደብዳቤ በአባሪነት ላከላቸው፡፡ ከእንግሊዝ ንግሥት የተላከላቸው ደብዳቤ ሲተረጎም እንዲህ ይላል፡፡

> ግርማዊነትዎ እንደ ጠየቁት ሁሉ የሚፈልጓቸውን ባለ ሙያዎች ስለላክንልዎ ፍላድ ይዞልዎት ሊመጣ ሲል ለአሽከራችን ለራሳም ያደረጉለትን መልካም ድርጊት ትተው አሽከራችንን ካሜሮንን ከሌሎቹ አውሮፓውያን ጋር እንደገና ማሰርዎን ሰማን፡፡ ይህ የሆነበትን ምክንያት የሚያስረዳ ከግርማዊነትዎ በኩል ምንም ነገር አላገኘንም፡፡

* ጳውሎስ ኞኞ፡- አጤ ምኒልክ

> ይህም ቢሆን ፍላድን እንዲያው በከንቱ በማቆየት ጊዜ አናጠፋም ብለን ለግርማዊነትዎ የጻፍነውን ደብዳቤ ሰጥተን ላክነው። ግርማዊነትዎ የገቡትን የተስፋ ቃል እንደሚፈጽሙ እንተማመናለን። የታሰሩትን እስረኞች እና አሽከሮቻችንን ልቀቁልን። ይህን ካደረጉ አሁን በወዳጅነታችን ላይ የተጋረደው ጥቁር ደመና ተገፍፎ እንደሚጠፋ ሙሉ እምነት አለን።

ለዚህ ደብዳቤው መልስ ከዐፄ ቴዎድሮስ ባለ ማግኘቱ ሌላ ደብዳቤ እንደገና ጽፎ፣ ከበፊቱ ደብዳቤ ግልባጭ ጭምር ፍላድ ላከላቸው። በደብዳቤው የገሸሸው፣በፊት የላከው ደብዳቤ መልስ በመዘግየቱ ለሁለተኛ ጊዜ ይህን ደብዳቤ ለመጻፍ መገደዱን ነበር። የቴዎድሮስ ሐሳብ፣ፍላድ እስረኞቹ ከመልቀቃቸው በፊት ጥበበኞቹን እንዲያመጣላቸው ነበር። ፍላድ ምፅዋ እስካለ ድረስ-የቴዎድሮስ እጅ እንደማይደርስበት ቢያውቅም፣ባለቤቱ መቅደላ ከታሰሩት አንዷ በመሆኗ ሃሳብ አብከንክኖታል። በሌላ በኩል ደግሞ እስረኞቹን ሳይረከብ ጥበበኞቹን እንዳይልክ ተነግሮታል።

ፍላድ በእነዚህ ሁለት አጣብቂኝ ውስጥ በመሆኑ እጅግ ተጨንቋል። ሆኖም ትእዛዙን መፈጸም ግዴታው ስለ ሆነ ዐፄ ቴዎድሮስ እስረኞቹን ስለ አልፈቱ፣ከአገሩ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ከእሱ ጋር የመጡትን የጥበብ ሰዎች መልሶ ወደ እንግሊዝ አገር ላካቸው። ይህ ሁኔታ፣ከቴዎድሮስ ጋር ያለው ግንኙነት በሰላም የማያልቅ መሆኑን አመላከተ። ከዚያ በኋላ የእንግሊዝ መንግሥት የጦር አዋጅ አወጀ። አዋጁ ከተነገረ በኋላ "እስረኞቹን እንዴት በደህና ለማስለቀቅ ይቻላል?" የሚለው ጥያቄ ሌላ ክርክር አስነሳ።

የእንግሊዝ ምክር ቤት አባል የሆነው ሳሙኤል ቤከር "ከግብፆች ጋር ተስማምተን ቴዎድሮስን በጋራ እናጥቃ" አለ። ኢትዮጵያ ውስጥ ጉብኝት ስላካሄድ የነበረው ሜርዌዘር በበኩሉ "የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር በንጉሡ ላይ ሸፍቷል። በዚህ ምክንያት አገሪቷ ብትወረር ሕዝቡ በደስታ ይቀበላል" ብሎ አሳመነ። ሜርዌዘር ያለው እውነት ነው። ዋግሹም ገብረ መድኅን ሸፍተው ላስታ ገብተው ነፃነታቸውን አውጀዋል። ዋግሹም ጎበዜም ሸፍተው ብዙ ተከታይ በማግኘታቸው የቴዎድሮስ ኃይል በእጅጉ ለመቀነሱ ምክንያት ሁኗል።



ዘለለው እሸቱ የሚባለው የፈረሰኞች አለቃ ቴዎድሮስን ከድቶ፣ሁለት መቶ ያህል ፈረሶች ይዞ አገሩ ጋይንት ገብቷል። ዘለለው ከሌሎች አበጋዞች ጋር መቅደላ ላይ የነበሩት የአባኘር እሸቱ የበህር ልጅ ነው ይባላል*።

ከዐፄ ቴዎድሮስ ጋር የነበሩ ሌሎች ትናንሽ ሹማምንት እና ሠራዊቱም በየፊናቸው ቴዎድሮስን ከድተዋል። ይህ ሁሉ ተዳምሮ ከመቶ ሺሕ ሠራዊት በላይ የነበራቸው ቴዎድሮስ በ፲፰፻፶፱ ዓ.ም. በድምሩ ከአሥር እስከ አሥራ አምስት ሺሕ የሚሆን ጦር በላይ ተከታይ አልነበራቸውም። ይህ ክስተት ያበሳጫቸው ዐፄ ቴዎድሮስ ከሠራዊታቸው መሐል ሆነው ሁላችሁም እኔን ለመክዳት ማሰባችሁን አውቃለሁ። ከዚህ ሁሉ ለምን አትገድሉኝም?* ብለው የምር አለቀሱ ይባላል።

ሜርዌዘር አጥንቶ ለእንግሊዝ መንግሥት ያቀረበው ቀጥሎ ያለውን ሐሳብ ነው። እኛ ከቴዎድሮስ ጋር ብንዋጋ ሹማምንቶች እና ሠራዊታቸው እየከዳ በመሄዱ ምክንያት፣ጦርነቱን ለማሸነፍ እንችላለን" የሚል መረጃ በመስጠቱ እንግሊዞች ተበረታቱ። ከዚያም በእንግሊዞች የሚመራ የሕንድ ሠራዊት ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ ተወሰነ። ወዲያው እንግሊዛዊው ጀነራል ናፒር የጦሩ መሪ ሁኖ ተሾመ። እሱ ወደ ኢትዮጵያ እንዲዘምት ሲታዘዝ፣አብረውት እንዲዘምቱ የመረጣቸው መኮንኖች እና መሐንዲሶች ስለ ኢትዮጵያ ሁኔታ እንዲያውቁ ለማድረግ ከጄምስ ብሩስ ጊዜ ጀምሮ ስለ ኢትዮጵያ ተጽፎ ያገኙትን ሁሉ እንዲያነቡ አደረገ። ናፒር በቂ መረጃ ከአገኘ በኋላ፣በነሐሴ ወር ፲፰፻፶፱ ዓ.ም. መግቢያ ላይ ለጦርነት ተዘጋጀ። ጦርነቱን በድል ለመወጣት የቁሳቁስና የገንዘብ መጠን ጨምሮ ዝርዝሩን ጽፎ ለእንግሊዝ መንግሥት ሲያቀርብ የጠየቀው ሁሉ ተፈቀደለት። የእንግሊዝ ሠራዊት ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት መዘጋጀቱን የሰሙት ቴዎድሮስ ደብረ ታቦር እያሉ ነበር። ስለዚህ ለመከላከል ያመቻል ብለው በማሰብ መቅደላ አፋፍ ላይ ሆነው ለመዋጋት በመወሰናቸው ጉዟቸውን ወደዚያ ለማድረግ ወሰኑ። ወደ መቅደላ የሚሄዱበት ዋናው ምክንያት ዙርያውን ሙጥጥ ያለ ገደል በመሆኑ፣ጠላት እዚያ ቦታ በቀላሉ ለመድረስ ያዳግተዋል ተብሎ ነበር።

---

* መርስዔ ኀዘን፦ ከሐኪም ወርቀን ጋር ያደረጉት ያልታተመ ቃለ ምልልስ

ሌላው ምክንያት ደግሞ ወደ ተራራው ለመውጣት ያለው መንገድ በተራራው አንድ ጎን በኩል ብቻ በመሆኑ ጠላትን ለማጥቃት አመቺ ነው ከሚል እሳቤ ነው። ከጋፋት እስከ መቅደላ ያለው መንገድ ርቀት ፻፶፭ ኪሎ ሜትር ሲሆን ሴባስቶፖል ብለው የሰየሙት የትልቁ መድፍ ክብደት ፯ ሺሕ ኪሎ ግራም ነው። የቀሩት ፲፬ መድፎች እና የማጓጓዣ ጋሪዎች ክብደትም ቀላል የሚባል አልነበረም።


ወደ መቅደላ አፋፍ ሊያደርስ የሚያስችለው ብቸኛ መንገድ ጠመዝማዛና የድንጋይ ክምር የበዛበት በመሆኑ፣እንኳን እነዚያን ከባድ መድፎች የተሸከሙ ጋሪዎች ይቅርና ሌጣ ሰውም በቀላሉ ሊሄድበት የሚችልበት ሁኔታ አልነበረም። ስለዚህ ቴዎድሮስ የነበራቸው አማራጭ በቅድሚያ መንገዱን ማሠራት ነበር። እሳቸው እየቀየሱ፣ከሺህ ሰዎች በላይ በሥራው አሳትፈውና እራሳቸውም ዶማ ይዘው እየቆፈሩ ለጋሪዎቹ መሄጃ እንዲሆን መች መንገዱን አስተካከሉ።

መንገዱ ለጋሪ ማስኬጃ ብቁ ሆኖ ቢሠራም እጅግ ዳገትማና ጠመዝማዛ በመሆኑ ጋሪዎቹ እየተነዱ አቀበቱን ለመውጣት አስቸጋሪ ነበር። ዐፄ ቴዎድሮስ ችግሩን ለመወጣት የነበራቸው አማራጭ፣ከፊት እያስጎተቱ እና ከኋላ እያስገፉ ቀስ እያሉ መጓዝ ነበር። ለዚህም ሲባል ለመጎተቻ የሚሆን ወፍራም ገመድ ከጭራና ከበግ ፀጉር እያስገመዱ እንዲዘጋጅ አደረጉ።* ከዚያም ከፊት ሆነው የሚጎትቱና ከኋላ የሚገፉ ከ፰፻ ሰዎች በላይ መደቡ። በተጨማሪም ጋሪው ተንሸራትቶ ወደ ኋላ እንዳያፈገፍግ ሰዎች ተመርጠው እግሩ ስር ድንጋይ እንዲያስደግፉ ተመደቡ። ዐፄ ቴዎድሮስ ራሳቸው በመቅደላ መንገድ ሥራ ሲሳተፉ በዚህ መልኩ መንገዱ ከፊት፣ከፊት እየተሠራ መድፉን የተሸከሙት ጋሪዎች ከኋላ እየተከተሉ አስቸጋሪውን መንገድ እንደ ምንም ብለው አለፉና መድፎቹ ከስድስት ወር ጉዞ በኋላ ሰላምጌ ደረሱ። ስለ መንገድ ሥራ ከተነሳ አይቀር፣ጳውሎስ ኞኞ አጤ ቴዎድሮስ በሚለው መጽሐፉ ውስጥ ስለ እሳቸው ሌሎች ሥራዎች የጻፉትን ከዚህ በታች አጠር አድርጌ አቀርባለሁ። ዐፄ ቴዎድሮስ ሴባስቶፖል የሚባለውን ትልቅ መድፍ ያሠሩት በአገራቸው እንኳን መኪናና ሠረገላ መንገድም ባልነበረበት ዘመን ነው።



ዐፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን በዘመናዊ ሥልጣኔ ለማራመድ የተነሳሱት ለዚህ ነው።ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን በሙሉ በመንገድ ለማገናኘት ከፍተኛ ምኞትና ሐሳብ ነበራቸው። በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ሚስዮናውያን መንገድ እንዲሠሩላቸው ጠይቀው ስለ ነበረ፣እነሱን የሚረዱ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ መንገድ ሠሪዎች ሰጥተዋቸዋል።የመንገዱን ሥራ በተመለከተ ኸንሪ ዱፍተን የጻፈውን ከዚህ በታች እጠቅሳለሁ።

> አንድ ቀን ሚስዮናውያን ከንጉሡ ጋር በአጀብ ሲሔዱ ብዙ ድንጋይና ቋጥኝ ካለበት ቦታ ደረሱ። በዚያ መንገድ ሲሄዱ ያየውን አስመልክቶ "በኤሮፓ መንገድ ላይ እንዲህ ያለ መሰናክል ያለመኖሩንና መንግሥት መንገድ ማሠራቱን ነገሯቸው። ቴዎድሮስም ወዲያው ከበቅሏቸው ወርደው ድንጋይ ማንሳታቸውን ያየ ሁሉ ከበቅሉና ከፈረሱ እየወረደ ድንጋዮቹን ያነሳ ጀመር። ወዲያውንም ድንጋዮችም ሆኑ ቋጥኞች ተነስተው ጥቂት ማይሎች ርዝመት ያለው ጥሩ መንገድ ሆነ።



አይበገሬ የተባለው የመቅደላ ተራራ

በኢትዮጵያ ሥልጣኔና ዘመናዊ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ አያሌ ነገሮችን በመሥራት ግንባር ቀደምነት የያዙ ዐፄ ቴዎድሮስ ናቸው። በመገናኛ በኩል (ትራንስፖርት) እንኳን ብንመለከት መንገደኛና ዕቃ የሚያመላልስ ሠረገላ አሠርተው ነበር። ይህ ብቻ ሳይሆን በውሀ ኃይል እየዞረ ልዩ ልዩ መንኰራኵር የሚያዞር መሣሪያም ተሠርቶ ነበር።



ዐፄ ቴዎድሮስ መንገድ ለመሥሪያ ከተጠቀሙበት መሣሪያ ጋር



በዚያን ዘመን የቅጥቀጣና ልዩ ልዩ ሙያ ያላቸው ወጣቶች (ኢትዮጵያውያን) በቴክኒክ ሥራ እንዲጎለብቱ ከፍተኛ ጉጉት የነበራቸውና እሳቸው ራሳቸውም ቢሆኑ በፈጠራ ሥራ ለማገዝ ይጥሩ እንደነበረ ሄንሪ ብላንክ የሚከተለውን ምስክርነት ሰጥቷል።

> ፓድል እስቲመር (paddle steamer) ፈልስፈው ሠርተው ነበር። ዳሩ ግን ሎኮሞቲቩ ሳይሠራ ቀረ። ጀልባዋን የሚያንቀሳቅሱት ሁለቱ መንኰራኵሮች በጣም ትልቅ ስለነበሩ ወደ ውሀው ውስጥ ጠልቀው እንዲገቡ ለማድረግ በሙቀ የሚቆጣር ሰው ያስፈልግ ነበር። በዚሁ ጀልባ ሥራ መንፈሳቸው በጣም ተመስጦ ስለነበረ ጊዜያቸውን በሙሉ ለዚህ ተግባር በመዋላቸው፣ ከሠፈራቸው አራት ማይልስ ርቀት ላይ የሠፈረ ኃይለኛ ጠላት እንደ ተነሳባቸው እንኳን ሳይሰሙ እስከ መቅረት ደርሰዋል።




ሴቫስቶፖል በሰው ኃይል እየተጎተተና እየተገፋ ወደ መቅደላ ሲዘልቅ

የሚያዞር መሣሪያም ተሠርቶ ነበር።



በዒ ቴዎድሮስ መንገድ ለመሥሪያ ከተጠቀሙበት መሣሪያ ጋር

ኃይል አስቲመር (paddle steamer) ፊልሰፊው ሠርተው ነበር። ዳሩ ግን ሎኮሞቲቩ ሳይሠራ ቀረ። ጀልባዋን የሚያንቀሳቅሱት ሁለቱ መንኰራኩሮች በጣም ትልቅ ስለነበሩ ወደ ውሀው ውስጥ ጠልቀው እንዲገቡ ለማድረግ በሙቶ የሚቆጠር ሰው ያስፈልግ ነበር። በዚሁ ጀልባ ሥራ መንፈሳቸው በጣም ተመስጦ ስለነበረ ጊዜያቸውን በሙሉ ለዚህ ተግባር በመዋላቸው፣ ከሠፈራቸው አራት ማይልስ ርቀት ላይ የሠፈረ ኃይለኛ ጠላት እንደ ተነሳባቸው እንኳን ሳይሰሙ እስከ መቅረት ደርሰዋል።



ሴቫስቶፖል በሰው ኃይል እየተጎተተና እየተገፋ ወደ መቅደላ ሲዘልቅ

ራሳም በበኩሉ ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ በመርከብ ሥራ ጉዳይ እንደሚከተለው ጽፏል፡፡

> በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በሞተር የሚንቀሳቀስ ጀልባ ፲፰፻፶፰ ዓ..ም. ሲሠራ በሥራው ቴዎድሮስም ተሳትፈዋል፡፡ ፳ ጫማ ርዝማኔ ፰ ጫማ ስፋት ያላቸው ሁለት ጀልባዎች ተሠሩ፡፡ እነዚህ ሁለት ጀልባዎች እያንዳንዳቸው መቶ ሰዎች ሲጫኑ ጀልባዎቹ ወደ ባህሩ ውስጥ የዘቀጡት አራት ኢንች ያህል ነበር፡፡ ጀልባዋ በምትሞከርበት ጊዜ እኛን ይዘውን አልሄዱም፡፡ መልከተኛ ልከው «እናንተን የተውኩበት ምክንያት ምናልባት ጀልባዋ የሰመጠች እንደሆነ ውሀ ውስጥ ትገቡና ትረጥባላችሁ ብዬ ነው» አሉን፡፡ በደህና ከተመለሱ በኋላ አንድ የባህር ኃይል እንድናቋቁም ጠየቁን፡፡

ሄንሪ ብላንክና ራሳም ከዚህ ከፍ ብሎ ከጻፏቸው የምስክርነት ቃላት እንደምንገነዘበው፣ቴዎድሮስ ዘመናዊ የቴክኒክ ሙያ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባና እንዲዳብር ያደረጉት፣ብዙ ጊዜ በሚጻፈው የመድፍ ሥራ ብቻ ሳይሆን፣በየብስና በባህር የሚሽከረከሩ መንኮራኩሮች አሠርተዋል፡፡ ሥልጣኔ ወደ አገራቸው በቶሎ እንዲገባ ከነበራቸው ጽኑ ፍላጎት እና ምኞት በመነሳሳት የአውሮፓ አገሮች በተለይም የእንግሊዝ መንግሥት እንድትረዳቸው ለጻፉት ደብዳቤ መልስ ባለማግኘ ታቸው አካባቢዎቻቸው የነበሩትን ፈረንጆቹን አሰሩ፡፡ አካሄዳቸው ትክክል ነበር ማለት ተገቢ ባይሆንም፣ራዕያቸው ሲገታ፣ተስፋቸው ሲጨናገፍ የወሰዱት እርምጃ መሆኑን መገንዘብ ያሻል፡፡ "እልህ ድንጋይ ያስውጣል ይባል የለ?"

ዐፄ ቴዎድሮስ መቅደላ መመሸጋቸውን የሰማው የእንግሊዝ ጦር ወደ መቅደላ የሚጓዝበትን መንገድ እና የጦር ማረፊያ ቦታ መርጦና አዘጋጅቶ እንዲጠብቅ ሜርዌዘርን ላከው፡፡ ለዚህ ወረራ ናፒር ዘመናዊ የሆነ መሣሪያና ሰፊ ዝግጅት አድርጎ፣በኢትዮጵያ መገበያያ የነበረውን ፳፻ ሺሕ የማሪያ ቴሬዛ ጠገራ ብር በጀት አስፈቀደ፡፡ በዕቅዱ መሠረት፣በቀይ ባህር ዳርቻ ወደቦች ተደለደሉ፡፡ ታላላቅ ባውዛዎች ተተከሉ፡፡ የባህሩን የጨው ውሀ ወደ የሚጠጣ ውሀ የሚያጣራ መሣሪያ ተገዝቶ (ኮንዴንሰር) መጣ፡፡




የቴሌግራፍ ሽቦ ተዘረጋ፣የተሟላ ማቀዝቀገ እና የሕክምና ዕቃ ጭምር ተሰናዳ፡፡ ወደ መሐል ኢትዮጵያ፣ዝሆኖች፣ፈረሶች እና አጋሰሶች፣በቅሎ እና ግመሎችም ጭምር በገፍ ቀረቡ፡፡ መሣሪያዎቹን እና ፴፪ ሺሕ ሠራዊት ለጫኑ ፲፻፰፱ መርከቦች ኪራይ ፬ ሚሊዮን ፫፻፴ ሺሕ ሩፒ ተከፈለ፡፡

ከዚህ ሁሉ ዝግጅት በኋላ ዘመቻውን ስኬታማ ለማድረግ የቀረው አንድ ነገር ብቻ ነበር፡፡ የእንግሊዝ ሠራዊት ወደ መቅደላ ሲጓዝ የሌሎቹ የኢትዮጵያ ክፍል ገዥዎች አናሳልፍም በማለት ጦርነት እንዳይከፍቱ ጥንቃቄ ማድረግ ነበር፡፡ ይህን በተመለከተ ቀደም ሲል ሜርዌዘር ባደረገው ስለላ፣በርካታ መኳንንት በቴዎድሮስ ላይ መሸፈታቸውን ለእንግሊዝ መንግሥት መናገሩ ይታወሳል፡፡



የእንግሊዞቹ መሣሪያ በዝሆን፣በፈረስና በቅሎ ተጭኖ ሲጓጓዝ

እነዚህ በቴዎድሮስ ላይ ያመፁት መኳንንት ከእንግሊዝ ጋር እንዲተባበሩ በማድረግ በኩል እንዲረዳ አሁን መንገድ መሪ ሆኖ የመጣው፣ያው ራሱ ሜርዌዘር ትልቅ ሚና መጫወት ጀመረ፡፡



የእንግሊዞቹ መሣሪያ በዝሆን፣በፈረስና በቅሎ ተጭኖ ሲጓጓዝ

ጦሩን ከባህር ጠረፍ ጀምሮ ሜርዌዘር እየመራ መጣና ከደጃዝማች ካሣ (በኋላ ዐፄ ዮሐንስ ፬ኛ) ግዛት ከመግባቱ በፊት፣ደብዳቤ ጽፎ የይለፍ ፈቃድ ጠየቀ። በጀነራል ናፒር ትእዛዝ ሜርዌዘር የጻፈው ደብዳቤ "እኛ የመጣነው እስረኞች ወገኖቻችንን ከመቅደላ ለማስፈታት ነው እንጂ ሕዝቡን ለመንካት ወይም አገሪቱን ለመውረር አልመጣንም" የሚል ነበር። ደጃዝማች ካሣ (ዮሐንስ ፬ኛ) የቴዎድሮስን መውደቅ ይመኙ ስለነበረ እንግሊዞች ካሸነፉ በኋላ አገራቸውን ለቀቀው እንዲወጡ ይፈልጋሉ። ስለዚህ መርጫ ወርቄ የሚባል አሽከራቸው ይህን ሃሳብ ለእንግሊዞች እንዲያቀርብ ላኩት።

መርጫ ወርቄ ወደ እንግሊዞቹ ሰፈር ሄዶ ከሜርዌዘር ጋር በዚህ ሃሳብ ላይ በመነጋገሩ ሁለቱም ተስማምተው ተለያዩ። የእንግሊዝ ሠራዊት ከደጃዝማች ካሣ የይለፍ ፈቃድ አግኝቶ ከወጣ በኋላ የሚጓዘው በደጃዝማች ጎበዜ ግዛት አልፎ በመሆኑ፣በእሳቸው ግዛት ለማለፍ የሚያስችል መጠየቂያ ደብዳቤ ሜርዌዘር ጻፈላቸው።

ደጃዝማች ጎበዜ የቴዎድሮስን መውደቅ ይፈልጉ ነበር እና እሳቸውም ለዚህ ጉዳይ ብቻ ከሆነ የማይቃወሙ መሆናቸውን የሚገልጽ መልስ ጻፉለት። ወደ መቅደላ የሚደረገው ጉዞ ይህን በመሰለ ዝግጅት ከተጠናቀቀ በኋላ ሜርዌዘር አንድ ደብዳቤ በናፒር ስም ጽፎ ለዐፄ ቴዎድሮስ ላከ።

ለቴዎድሮስ የአበሻ ንጉሥ ፦

> በእንግሊዝ ንግሥት ትዕዛዝ፣ በእጅዎ ያለ ምክንያት የተያዙትን እስረኞች ለማስለቀቅ መጥቻለሁ እና እስረኞቹን በሙሉ ለቅቀው፣ከአረፍንበት ሰፈር ድረስ እንዲልኩ ይሁን። ግርማዊነትዎ ይህን ትእዛዝ የማይስማሙበት ቢሆን ግን፣ከግርማዊነትዎ ግዛት በኃይል እንድገባ ታዝዣለሁ። የመጣሁበትን እስክፈጽም ድረስ ምንም የሚያቆመኝ ኃይል የለም። በግዛትዎ ውስጥ የማደርገውም ሆነ የምፈልገው ነገር የለኝም። ሥልጣንዎን ልቀናቀን አልመጣሁም። ዋናው ጉዳይ የተያዙት ሰዎች እንዲለቀቁ ለማድረግ መሆኑን አሳስባለሁ።



> ግርማዊነትዎ ይህን የመጣውን አደጋ ሊመልሱት የሚችሉት እስረኞቹን ቶሎ በመልቀቅ ብቻ ይሆናል። ነገር ግን እስረኞቹ በሰላም እጄ ካልገቡ፣ቢጉላሉ ወይም አንዳንች ጉዳት ቢደርስባቸው ኃላፊነቱን የሚወስዱት ግርማዊነትዎ ብቻ ነዎት። ይህ ከሆነም ለወደፊቱ ምንም ዓይነት ወዳጅነት አይኖርም።

ከሌፍተናንት ጀነራል ሮበርት ናፒር የቦምቤይ ጦር ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ የተጻፈውን ደብዳቤ የያዘው ሰው፣ሽፍቶች መንገድ ላይ አግኝተው ሲጠይቁት፣ ለማን እንደ ተጻፈ ለመናገር ስለፈራ ለራሳም የተላከ ነው ብሎ ተናገረ። እነሱም ነገሩ እውነት መስሏቸው ደብዳቤውን ለራሳም ላኩለት። ራሳም ደብዳቤውን ከፍቶ ሲያነብ ለቴዎድሮስ የተላከ መሆኑን ቢያውቅም፣ለእሳቸው መስጠት አልፈለገም። ለዚህም ምክንያቱ፣ቴዎድሮስ ደብዳቤውን ሲያነቡ ይናደዱ እና እኛን እስረኞቹን ይገድሉናል የሚል ስጋት ስለ አደረበት ነበር። ጀነራል ናፒር ጦርነቱን ለመምራት ወደ ኢትዮጵያ ያስገባው ፴፪ ሺሕ ፺፱ የሰው ኃይል እና ፵፫ ሺሕ ፳፻፺፯ የጭነት እንስሳት ነበር።

ከእንግሊዞች ጋር የሚተባበሩ ሰዎች በማፈላለግ ግንኙነቱን እንዲያዘጋጁ ከመረጣቸው ሰዎች መሐከል፣ዋና ሰላይ እና መንገድ መሪ ሆኖ የመጣው የቀድሞው ኮለኔል፣አሁን ብርጋዴር ጀነራል ሆኖ የተሾመው ሜርዌዘር ነው። በእሱ መሪነት ከመጡት የቡድኑ አባላት መሐከል ዋናዎቹ ጀምስ ግራንት እና እስከ ዐፄ ዮሐንስ ፬ኛ ዘመን ድረስ የኢትዮጵያን መኳንንት ሲያበጣብጥ የኖረው ሙዚንጀር ናቸው። ሙዚንጀር ቀደም ሲል እንደለመደው፣አብረዋቸው የመጡትን አሥር የመልዕክተኞች ቡድን ይዞ ጥር ፲፰ ቀን ከሜጀር ጀነራል ናፒር ተልኮ ወደ ደጃዝማች ካሣ ዋና ከተማ ዓድዋ ሄደ። ደጃዝማች ካሣ በበኩላቸው፣የሰላዋውን ገዥ ኃይለ ማርያም፣የገራልታውን ሐጎስ፣የፆራውን ገብረ ሚካኤል፣የሽሬውን ገዥ ጉግሣ፣የአክሱሙን ንቡረዕድ ገብረ ውብትንና ሹም ተምቤን አኑንን፣ሹም አጋሜ ጥርሶን፣ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት መኳንንት በተጨማሪ የእንግሊዝ ተወካዮቹ የተቀበሏቸው ሌሎች መኳንንት እና ሕንድ አገር የተማረ እንግሊዝኛ በሚገባ የሚችለው አስተርጓሚ ገብሩ ወርቄም ነበረ። እንዲሁም የሰባጋዲስ ልጅ አብረዋቸው ነበሩ።

እንግሊዞቹ እንደ ደረሱ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ትልቅ ግብር ከመጋበዛቸው በስተቀር በዕለቱ ምንም ውይይት አልተደረገም:: ለደጃዝማች ካሣ ከናፒር የተላከው ደብዳቤ በማግስቱ ቀርቦ ትርጉሙ ከተነበበ በኋላ፣ደጃዝማች ካሣ ከዚህ በታች ያለውን ቃል ተናገሩ:: "አባቶቼ ከእንግሊዝ ጋር ወዳጅነት እንዳበጁ ሁሉ እኔም ወዳጅ በመሆን ክብትና እህል በማቅረብ እረዳለሁ" አሉ:: ከዚያም በመቀጠል፣ከናፒር ጋር ለመገናኘት ተስማምተው ቦታና ጊዜ ወስነው እንግሊዞቹ ወደ መጡበት ተመለሱ:: ደጃዝማች ካሣ ጥር ፳፯ ቀን ከዓድዋ ተነስተው እንግሊዞቹ ወደ አረፉበት ሠፈር ጉዞ ጀመሩ:: ከእሳቸው ጋር ሊቀ መኳስ ይልማ እና ሌሎች ወደ ስድሳ የሚሆኑ ጦርና ጠመንጃ የያዙ ወታደሮችና ጥቂት ቀሳውስት በአጃቢነት ተከትለዋቸው ሄዱ:: ደጃዝማች ካሣ፣መኳንንቶቻቸውና ሌሎቹም ተከታዮቻቸው ከእንግሊዞች ሠፈር ሲደርሱ በጀነራል ናፒር ትዕዛዝ በከፍተኛ ክብር ተቀበሏቸው:: ከዚያም የሁለቱም ወገን ቡድን ተገናኝተው ከተወያዩ በኋላ፣ደጃዝማች ካሣና ጀነራል ናፒር ሐራሞት ውስጥ ማይ አደብ ከተባለው ቦታ እንደገና ለመገናኘት ተስማሙ::

በማግስቱ መልዕክተኞቹ፣የደምብ ልብስ በለበሱ የእንግሊዝ ወታደሮች ተሸኝተው ወደ ዓድዋ ተመለሱ:: በቀጠሮው መሠረት ጀነራል ናፒር በ፬፻፶ ወታደሮች ታጅቦ የካቲት ፲፰ ቀን ማይ አደብ ደረሰ*:: ደጃዝማች ካሣ ጠመንጃና ጦር ከያዙ አራት ሺሕ ወታደሮቻቸው ጋር እዚያ ሠፍረው ነበር:: ከደጃዝማች ካሣ ሠፈር ማዶ ከትይዩ ቦታ የናፒር ተከታዮች ጓዝ አውርደው ድንኳን ተከሉ:: የእንግሊዞችን መድረስና ድንኳን ተከላ ማለቁን ሲያዩ፣አረንጓዴ፣ብጫ እና ቀይ የሆነው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከፊት ቀድሞ፣ካሣ በ፬፻ ወታደሮቻቸው ታጅበው ወደ ናፒር ሠፈር ሄዱ:: የካሣ መምጣት እንደ ታወቀ፣ቀያይ ልብስ በለበሱ ዝሆን ተቀማጮች የክብር ዘብ ታጅቦ ጀነራል ናፒር በክብር ተቀበላቸው:: ተገቢውን ሰላምታ ተለዋውጠው ለውይይት ሲቀመጡ፣ዋግሹም ጎበዜና ራስ ባሪያው መሸፈታቸው ደጃዝማች ካሣን ያስጋቸው መሆኑን አስረዱ:: ናፒር ከዚህ በፊት እንደተናገረው ሁሉ አሁንም "እኛ በአገራችሁ የውስጥ ጉዳይ አንገባም:: ነገር ግን መሣሪያ ልንሰጥዎ ዝግጁ ነን" የሚል መልስ ሰጣቸው::

* ጳውሎስ ኞኞ:- አጤ ቴዎድሮስ




ናፒር በአገራችሁ የውስጥ ጉዳይ አንገባም ያለበት ምክንያት ጉዞው በጎበዜ ግዛት በኩል አቋርጦ ሲሄድ ችግር እንዳይገጥመው ሰግቶ ነው:: በዚህ ሐሳብ ሁለቱም ተስማምተው ካሣ ወደ ሠፈራቸው ተመለሱ::

እንግሊዞቹ ወደ መቅደላ ጉዞ ከመጀመራቸው በፊት፣ካሣ ጀነራል ናፒርን እና የጦር መኮንኖቹን ወደ ሠፈራቸው ጠርተው ግብር አበሉ:: በአገሩ ባህል መሠረትም ሸለላ እና ፉከራ አሰሙት:: ከዚያም በራሱ ላይ የአንበሳ ጎፈር፣በወገቡ ላይ ሰገባው በወርቅ ያጌጠ ጎራዴ እና በእጁም ጦር እና ጋሻ በማስያዝ ሸለሙት:: ጀነራል ናፒር ለመሄድ ሲነሳ ከድንኳን ከመውጣቱ በፊት፣በወርቅ ማራሸት ያጌጠች ግራጫ በቅሎ ቀርባ ለመንገዣ እንድትሆነው የተሰጠው መሆኑን ነገሩት*:: ናፒር ወደ መቅደላ ለመሄድ ከካሣ ግዛት ከመውጣቱ በፊት የዋግሹም ጎበዜን ግዛት በሰላም ለማለፍ ፈቃድ እንዲጠይቅ ሜርዌዘርን ልኮት ነበር:: በዚያን ሰሞን ዋግሹም ጎበዜ ላስታ ውስጥ አልነበሩም:: ስለዚህ የእሳቸው ጦር ዋና አዛዥ ከሆኑት ደጃዝማች መሸሻ ጋር ለመነጋገር ተቀጣጠሩ:: በቀጠሮው ቀን በተከዜ ሸለቆ ዛጎል ዛፍ ከሚባል ስፍራ ተገናኝተው ከደጃዝማች መሸሻ ጋር ተነጋገሩ::



ካባ ለብሰው ቢተኛው ረድፍ መሐል የተቀመጡት ካሣ (ዐፄ ዮሐንስ ፬ኛ) ሲሆኑ፣ በእሳቸው በስተግራ ያሉት ፈረንጆች፣ናፒር፣ሜርዌዘር እና ሙዚንጀር ናቸው::

ደጃዝማች መሸሻ በናፒር ጥያቄ ተስማምተው የእንግሊዝን ጦር እስከ ደላንታ ድረስ ለመሸኘት ፈቃደኛ ሆኑ። መጋቢት ፳፱ ቀን ደግሞ የወሎ ንግሥት የወይዘሮ መስተዋት ልጅ፣ኢማም አህመድ፣ቴዎድሮስን ለመጣል ከእንግሊዞች ጎን ሆኖ እንደሚዋጋ አሳወቀ። ጀነራል ነፒር ከኢማም አህመድ በደረሰው ደብዳቤ ተደስቶ፣በእንግሊዞች በኩል ምንም የሚያውክ ነገር እንደሌለ እና "ቴዎድሮስ ግን አምልጠው በሌላ መንገድ እንዳይወጡ የእርስዎ ሠራዊት እንዲጠብቅ ያድርጉ" የሚል ደብዳቤ ጽፎ ለትብብሩ ምስጋና በማድረግ ጭምር ለኢማም አህመድ መልሱን ላከለት። በሥልጣን ሽኩቻ አባዜ በተጠመዱት "የጎጃሙ ራስ ደስታ አባ ቀማው፣የወሎዋ ወርቂት የላስታው ዋግ ሥዩም ጎበዜ፣የወልቃይቱ ጣሰው ጎበዜ እና የትግሬው ደጃዝማች በዝበዝ ካሣ አድመውና አብረው*" የዐፄ ቴዎድሮስ እርምጃ እንዲደናቀፍ አደረጉ። በዚህ ዓይነት ትብብርና ዝግጅት ጦሩ ደላንታ በሰላም እንደ ደረሰ፣ናፒር ስንዱ በተባለ ቦታ ሠፈረ። ናፒር ከዚህ ሠፈር ሆኖ ለዐፄ ቴዎድሮስ ደብዳቤ ጻፈ።



የጀነራል ናፒር ሠራዊት አሰላለፍ






የዐፄ ቴዎድሮስ ሠራዊት አሰላለፍ

ናፒር የጻፈው ደብዳቤ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።:

> በእንግሊዝ ንግሥት ትዕዛዝ ከጦር ሠራዊቴ ጋር መቅደላ አጠገብ ደርሻለሁ። የታዘዝኩትም በእርስዎ እጅ የሚገኙትን ራሳምን፣ ቆንሲል ካሜሮንን፣ ሐኪም ብላንክን፣ መቶ አለቃ ፕሪዲውክስን እና ሌሎቹንም አሁን በግርማዊነትዎ ኃይል በእስር ላይ ያሉትን ኤሮፓውያኖች ለማስለቀቅ መጥቻለሁ። ግርማዊነትዎን የምጠይቀው እነኝህን ሰዎች በተቻለ ፍጥነት እኔ ሰፈር ድረስ በሰላም እንዲልኩልኝ ነው።


የቴዎድሮስ መልስ እስኪመጣ ድረስ፣ናፒር ስንዴ በተባለው ቦታ እንደ ሠፈረ ከዋድላው ገዥ ከደጃዝማች ወልደ ቂርቆስ (ኪሮስ) እንዲሁም ከደላንታው ባላባት ልጅ አበጋዝ ጋር ተገናኝተው ተመመካከሩ።

ደጃዝማች መሸሻ በናፒር ጥያቄ ተስማምተው የእንግሊዝን ጦር እስከ ደላንታ ድረስ ለመሸኘት ፈቃደኛ ሆኑ። መጋቢት ፳፱ ቀን ደግሞ የወሎ ንግሥት የወይዘሮ መስተዋት ልጅ፣ኢማም አህመድ፣ቴዎድሮስን ለመጣል ከእንግሊዞች ጎን ሆኖ እንደሚዋጋ አሳወቀ። ጀነራል ነፒር ከኢማም አህመድ በደረሰው ደብዳቤ ተደስቶ፣በእንግሊዞች በኩል ምንም የሚያውክ ነገር እንደሌለ እና "ቴዎድሮስ ግን አምልጠው በሌላ መንገድ እንዳይወጡ የእርስዎ ሠራዊት እንዲጠብቅ ያድርጉ" የሚል ደብዳቤ ጽፎ ለትብብሩ ምስጋና በማድረግ ጭምር ለኢማም አህመድ መልሱን ላከለት። በሥልጣን ሽኩቻ አባዜ በተጠመዱት "የጎጃሙ ራስ ደስታ አባ ቀማው፣የወሎዋ ወርቂት የላስታው ዋግ ሥዩም ጎበዜ፣የወልቃይቱ ባሰው ጎበዜ እና የትግሬው ደጃዝማች በዝበዝ ካሣ አድመውና አብረው*" የዐፄ ቴዎድሮስ እርምጃ እንዲደናቀፍ አደረጉ። በዚህ ዓይነት ትብብርና ዝግጅት ጦሩ ደላንታ በሰላም እንደ ደረሰ፣ናፒር ስንዴ በተባለ ቦታ ሠፈረ። ናፒር ከዚህ ሠፈር ሆኖ ለዐፄ ቴዎድሮስ ደብዳቤ ጻፈ።



የጀነራል ናፒር ሠራዊት አሰላለፍ





የዐፄ ቴዎድሮስ ሠራዊት አሰላለፍ

ናፒር የጻፈው ደብዳቤ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው፡፡፡

> በእንግሊዝ ንግሥት ትዕዛዝ ከጦር ሠራዊቴ ጋር መቅደላ አጠገብ ደርሻለሁ። የታዘዝኩትም በእርስዎ እጅ የሚገኙትን ራሳምን፣ ቆንሲል ካሜሮንን፣ ሐኪም ብላንክን፣ መቶ አለቃ ፕሪዲውክስን እና ሌሎቹንም አሁን በግርማዊነትዎ ኃይል በእስር ላይ ያሉትን ኤሮፓውያኖች ለማስለቀቅ መጥቻለሁ። ግርማዊነትዎን የምጠይቀው እነኚህን ሰዎች በተቻለ ፍጥነት እኔ ሰፈር ድረስ በሰላም እንዲልኩልኝ ነው።

የቴዎድሮስ መልስ እስኪመጣ ድረስ፣ናፒር ስንዴ በተባለው ቦታ እንደ ሠፈረ ከዋድላው ገዥ ከደጃዝማች ወልደ ቂርቆስ (ኪሮስ) እንዲሁም ከደላንታው ባላባት ልጅ አበጋዝ ጋር ተገናኝተው ተመመካከሩ።

ቀጥሎም መቶ ሃምሳ ኩንታል ዱቄት፣አምስት መቶ ጀንያ ስንዴ የዋድላ፣ የደላንታ እና የዳውንት ሕዝብ አቅርቦላቸው ገዙ:: በዚህ ግዢ ቀደም ሲል ናፒር የነበረው የስንቅ ክምችት ይበልጥ ጎለበተ::

ለዐፄ ቴዎድሮስ ለተጻፈው ደብዳቤ መልስ ባለ መምጣቱ፣ቀዳሚው የእንግሊዝ ሠራዊት፣ ከመቅደላ ፹፫ ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ከሚገኘው ተከዜ ወንዝ ደረሰ:: ዐፄ ቴዎድሮስ በበኩላቸው ከመቅደላ ተራራ ግርጌ ከሚገኘው ሰላምጌ ደርሰዋል:: እስረኞች የነበሩት ሰላምጌ ስለነበረ ዋልድሜየርን ጠርተው "ከአንተ ጋር ያሉትን ሁሉ ጥራቸውና ሁላችንም አብረን ወደ መቅደላ እንሄዳለን" አሉት:: እስረኞቹ እንደመጡ ሁሉም አብረው ወደ መቅደላ አፋፍ ለመውጣት ስለተዘጋጁ፣ በሰንሰለት የታሰሩት ፈረንጆች በሙሉ ሰንሰለቱ ወለቀላቸው:: ከዚያም ከስተርን እና ከሮዘንታል በስተቀር የቀሩት ሌሎቹ በሙሉ ወደ እሳቸው እንዲመጡ አስጠሯቸው:: ፈረንጆቹ እንደመጡ ቴዎድሮስ ከድንኳናቸው ወጥተው ቀደም ሲል ከሜዳ ላይ ተነጥፈው በነበሩት ምንጣፎች ላይ ሁሉም ተቀመጡ:: ቀጥሎም በአንድነት ሆነው በሰላምና በወዳጅነት በመነጋገር ላይ እያሉ፣ዐፄ ቴዎድሮስ በንግግራቸው መሐል ጣልቃ አስገቡ እና "ስማ ራሳም፣እኔ በአንተ እተማመንብሃለሁ:: ልጄን ዓለማየሁን አደራ ሰጥቼሃለሁ፣ጠብቀው አባትም ሁነው:: እኔ እንደማስበው የመጨረሻዬ ቀኔ ቀርቧል:: ራሳዬ አጠገብ የምትቆምበትም ቀን ደርሷል"* አሉት::

ሚያዚያ ፪ ቀን ጧት በ፲፪ ሰዓት ቴዎድሮስ ዋልድሜየርን አስጠሩትና እሱ እንደ ደረሰ ቴዎድሮስ አዝነው እና ተክዘው ተቀምጠው አገኛቸው:: አጠገባቸው ቆሞ ሲጠብቅ ዐፄ ቴዎድሮስ ከተቀመጡበት ተነስተው ራሳምና ሌሎቹም እስረኞች እንዲጠሩ አዘዘው ወደ ውስጥ ገቡ:: ራሳም ተጠርቶ ሲደርስ ዐፄ ቴዎድሮስ የንጉሠ ነገሥት ማዕረግ ልብስ ለብሰው ከድንኳናቸው ወጡ:: ወዲያው ወደ ራሳም ዞር ብለው "ንሳ! ለዚያ ሰውዬ ወረቀት እንድጽፍ ትፈልጋለህ? አላደርገውም:: አንዲት ሴት ለላከችው ሰው ምንም የማደርገው ነገር የለም" አሉ:: ከዚያም እስረኞቹን ተራ በተራ አነጋገሩ:: ቴዎድሮስ እነሱን ሲያነጋግሩ በነበረት ቀን፣እንግሊዞቹ የራሳቸውን ዕቅድ እያወጡ ነበር::

* ገሪማ ታፈረ:- መይሳው ካሣ: የቋራው አንበሳ



ቢትወደድ ኃይሉ ከድተው፣የመቅደላን ምሽግ ሁኔታ እንዲሁም መድፎቹ የተጠመዱትን ቦታ መረጃ ቀደም ሲል ለእንግሊዞች ሰጥተው ነበር:: በዚህና ከሌሎች ሰላዮች ባገኙት መረጃ መሠረት ጀነራል ናፒር ሚያዚያ ፪ ቀን በበሽሎ በኩል በወርቅ ውሀ ሸለቆ፣ከፋላ ተራራ ስር፣በአሮጌና በአፍንጮ በር ሠራዊቱን ሲያደራጅ እና መመሪያ ሲያስተላልፍ ዋለ::

ዐፄ ቴዎድሮስን ከድተው የሚሸሹት ሠራዊታቸው ቁጥር እየበዛ ሄዶ በዚህ ወቅት የቀሯቸው ወደ አሥራ ሁለት ሺህ የሚሆኑ ብቻ ነበሩ:: ከዚህ ጋር በማያያዝ ቀደም ሲል፣ዐፄ ቴዎድሮስ ለሠራዊታቸው የተናገሩትን ለማስታወስ እወዳለሁ:: ንግግራቸው ታሪካዊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ለዛሬው እና ለመጪው ትውልድም ትምህርት ሰጪ ነውና እዚህ መጠቀሱ ተገቢ ነው እላለሁ::

ንግግሩ እነሆ!

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ:: በስም ሦስትነት በባህርይ አንድነት የማይለየው ልዑል እግዚአብሄር መርጦ ያነገሠውን ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ዘኢትዮጵያ በዛሬ ዕለት፣በአሁኑ ሰዓት ከጎኔ የተሰለፋችሁ ጀግኖች፣ አንድነትን የምትወዱና የምትከተሉ ተከታይ ትውልዶች ልነግራችሁ እና ላስተምራችሁ የምፈቅደው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ነው::

የእንግሊዝ መንግሥት ጦር ሠራዊት አንድነታችንን ለማፍረስ፣ ኃይላችንን ለማዳከም በቱርክ መንግሥት እየተረዳ (እየታገዘ) ወደ ኢትዮጵያ ምድር፣ባሕር ተሻግሮ ገባ:: ከዚያ በፊት ሲላላኩ "ኑ ድረሱልን" ሲሉ የነበሩት መሳፍንት ከሞት ከተረፉት ቀሪዎቹ ጋር ተገናኝተው እጅና በትር ሆነው መጡብን:: አሁን በአጠገቤ ያላችሁ ወገኖች፣የኢትዮጵያ ሠራዊት፣ለአንድነት የቆማችሁ ሆይ! ያለፈውን የመሳፍንት አመራር በማጥፋትና የቀና አስተዳደር በቦታው በመተካት የተለያዩ ወገኖችን በማግኘት፣የትኛው ጠፍቶ መልካም ሥራ እና ዘመናዊ ጥረት እንዲስፋፋ ለማድረግ ሳደረግሁት ድካሜ የኢትዮጵያ ምድር በስሜ ላይ ትመስክር::

መቼም ዕድሜያቸውን ሙሉ በወገኖቼ በኢትዮጵያ በሕዝብ ላይ ሲመኙ፣ ክፉ ሲያደርጉ የኖሩ መሳፍንት እና የነገሥታት ቅምጥል ዘሮች ደግ ሥራ መሥራት ስለማይችሉ እንዲሁም መልካም ትምህርት እና ጥበብ ማስተማር ቀርቶ በቅን ልቡና የሚሠሩትን የሚጠበቡትን ሁሉ ተከታይ ትውልድ እንዳይኖራቸው ለማድረግ ስለሚያጠፏቸው እናንተ የኢትዮጵያ ጀግኖች ለቆማችሁለት እና ለደከማችሁለት አንድነት ታማኝ ሆናችሁ እነሱን ለማደን መገኘት የአንድነት ጥሪዬ ነው።

ነገር ግን አንድነታችሁና ኃይላችሁ እንዲጠፋ ከተሰለፉባችሁ ጠላቶች ፊት መሸሽ ወይም በምን ግዴለሽነት ማለፍ ወገንን አታሉ፣ ጎሲናን በድሉ፣ ሳይሞቱ ሞቶ በውርደት መቃብር ታፍኖ መኖር ሲሆን በሌላም በኩል ደግሞ በአገሩ ላይ የመልካም ሥራና ደግ ሥራው ሐንድነቱ፣ ነጻነቱና ዓላማው በተግባር እንዲፈጸም መጣር ለትውልድ መንገድ መሪ ነው።

ማንኛውም ትውልድ በወረደ ልማድና በተበታተነ ሥርዓት ታፍኖ በክፉ ስራት ተዋርዶ ሺሕ ዘመን ተንቆ ከመኖር ለከፍተኛ አንድነት፣ለመልካም ሥራ በታማኝነት ለሀገሩ ክብር ሲል የሞተ ጀግናው ወታደር በክብር ይበልጠዋል። ለተከታዩ ትውልድም የመልካም ሥራው መስዋዕትነት መታሰቢያ ሆኖ ይኖራል። ይህ ትውልድ ቢያፍነው እንኳን ሌላ ትውልድ ይገልጠዋል። ለዚህ ታዛቢና መስካሪህ ሀገርህ የኢትዮጵያ ምድር ነው።

እነዚህ አሁን የከበቡህን የመሳፍንት ጭፍራዎች እና አጃቢዎች የውጭን ሀገር የእንግሊዝን የጦር ኃይል ይዘው ቢመጡብህ አትፍራቸው፣ ለክብርህ ብትሞት በሕይወት አለህ፣ ባትሞት ግን የሞትክና የተዋረድህ ነህ። ስለዚህ አሁን ለቀረበልህ ክብር ተነሳ! ታጠቅ! ተቀበለው። ጠላቶችህ መሳፍንት ደስ ይበላቸው፣ የዛሬ ደስታቸው የነገ ኀዘናቸውና ለቅሷቸው ነው። በየጊዜው ትውልድ ሁሉ የራሱ መብትና ምርጫ መኖሩን ያለፉት ነገሥታት ቢያውቁ ኖሮ ሕዝባቸውን በከንቱ ባልገደሉት፣ባላጠፉት ነበር። ለጊዜው ግዛታቸውና ታሪካቸው የሚኖር መስሏቸው ደክመውበት በከንቱ ጊዜያቸው አለፈ።



እኛ ግን ከእነርሱ ስንለይ የዛሬ ትውልድ ባለቤቶች ነን፣የነገው፣የነገሁም (የተነገ) ወዲያ ባለቤቶች ነን። ይኸውም መልካም ሠሪንና ሥራውን ስለምንመኝ ለአንድነትና ለተግባር ኃይል ለማቆም ስንደክም፣ስንታገል ነው እንጅ የነገው ትውልድ ባለቤት ለመሆን መልካም ሥራን እና አንድነትን ለይቶ የመምረጥ መብት የነገው ትውልድ ነው።

አሁን እናንተ ለሕዝባችሁ አንድነት ምንድን ነው የምትሠሩለት? የሕዝባችሁ አንድነትስ ለእናንተ ምን ያህል ክብር ነው የሚያስቀምጥላችሁ? አንድነት ከሌለ ሕዝብ የለም፣ሀገር ለባዕድ ይሆናል። በሕዝብ በአንድነት ከቆመ ግን ሀገር አለ። ሀገርን የሚሠራት የሕዝብ አንድነት እንጅ፣ ሀገር፣ የሕዝብ አንድነት አይሠራም፣ አያቆመውም። ነገር ግን ሀገር ታኖረዋለች፣ ታስመሰግነዋለች፣ መኖሪያና ሰፈሩ ሆና እውነተኛ ትውልድ ታስተላልፋለች።

እናንተም ሆናችሁ እኔ ለምን ደከምን? ለምን እንደምንሞትም ማወቅ የራሳችን መብት ነው። ነገር ግን መብታችን የራሳችን ሲሆን፣ ሞታችን ደግሞ በታሪክ የሚኖር ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ሕይወት ነው። ስለዚህ በሕይወታችን እንደምንኖር ቁጠሩት እንጅ ሳይሞቱ ከሞቱት ጋር ያለን እንዳይመስላችሁ። የእኛ ሞት ለተከታዩ ትውልድ ክብር ነው። ስለዚህ ሞታችን ጣፋጭ ማር እንጅ መራራ ሬት አይምሰላችሁ።

ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ለሠራዊታቸው ዐፄ ቴዎድሮስ ያደረጉትን ሌላ ንግግር ከዚህ በታች አቀርባለሁ።

> እንደ ሕጋችን ወደ ጦርነት የሚሄድ ሰው በካህናት እግዚአብሔር ይፍታህ ይባላል። ይህ እንዳይሆን ጳጳሱ አቡነ ሰላማ ዐርፈዋል። በእሳቸው ቦታ ሆኜ እኔ እፈታችኋለሁ። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ፣ የጠላትን ጦር ተቃውሞ በጦር ሜዳ ሕይወቱን ቢያጣ፣በአብ፣በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እግዚአብሔር ይፍታ።*

ዐፄ ቴዎድሮስ የተናገሩትን እነዚህን አጥንት ሰርስረው በመግባት ወኔ የሚቀሰቅሱ ቃላት ሲሰሙ ሠራዊቱ ሁሉ በእልክ ተዋጠ።

ከእሳቸው ወደ ፊት ሂድ፣ተዋጋ የሚል ትእዛዝ መጠበቅ አቅቶት ተቅበጠበጠ:: ስሜቱ ገንፍሎ ከእንግሊዝ ጦር ምሽግ ወደሚገኝበት ሰፈር ሮጦ ለመግባት ወኔው ገፋፋው:: ስሜቱ እያየለ በመሄዱ ከቀኑ ልክ ለ፲፩ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን የቴዎድሮስ ሠራዊት፣ፊታውራሪ ገብርዬን ጨምሮ ከመቅደላ አፋፍ ተንደርድሮ ወደ እንግሊዞች ሠፈር በመውረድ በእሮጌ የእሩምታ ተኩስ ከፈተ:: ሠራዊቱ በብዛት እየተመመ መምጣቱን እንግሊዞች እንዳዩ የአጸፋ ተኩስ ጀመሩ:: ከተራራው በታች ባለው ጠባብ መንገድ እየተንጋጋ የወረደው በፊታውራሪ ገብርዬ ይመራ የነበረው አምስት ሺሕ የቴዎድሮስ ጦር በብዛትና በአንድነት ሆኖ ወደ እንግሊዞች ሠፈር ሲሾጎደጎድ፣ለእንግሊዞች ተኩስ ጥሩ ዒላማ ሆኑ። ውስጥ እየገባ ተፈጀ:: የመጀመሪያው ቀን ገብርዬ እና ብዙ መኳንንቶች በጀግንነት ተሰው:: ያለቀው አልቆ የተረፈው የቴዎድሮስ ሠራዊት መሸሽ ጀመረ:: –

ቴዎድሮስ በበኩላቸው ጠቅላላ መሣሪያዎችን እና ቀሪውን ሠራዊት ይዘው መቅደላ አምባ ላይ መሽገው ነበርና ከፋላ አፋፍ ላይ ጠመንጃ እና መድፍ ያስተኩሱ ነበር:: ዐፄ ቴዎድሮስ የውጊያውን ሁኔታ ባአርስጣላብ (የሩቁን አቅርቦ በሚያሳይ መነጽር) ሲመለከቱ፣ ከሞትና ከመቁሰል የተረፈው ሠራዊታቸው ሲሸሽ አዩ:: ከዚያም ሴቫስቶፖል ብለው የሰየሙት ትልቁ መድፍ እንዲተኮስ አዘዙ:: ቀደም ሲል በመድፍ ተኩስ የሠለጠኑትን አጠገባቸው የነበሩትን መድፍ ተኳሽ ፈረንጆች አላምን ብለው፣አጠገባቸው የነበሩት ኢትዮጵያውያን ብቻ መድፉን እንዲተኩሱ ፈቀዱላቸው::

እነዚህ አዳዲስ መድፍ ተኳሾች ባለ ማወቅ በአንድ ጊዜ ሁለት ጥይቶች አጉርሰው ኖሮ መድፉ ሲተኮስ ከበስተኋላው በኩል ተሰነጠቀ:: መድፉ ተሰንጥቆ ከአገልግሎት ውጪ ሲሆን አጠገቡ ሆነው ያዩት ዐፄ ቴዎድሮስ እጅግ በጣም ተበሳጩ:: በቀሩት መድፎች ወደ እንግሊዝ ሠራዊት ሲተኮስ ምንም የረባ ውጤት ሳያስገኝ ቀረ*:: በአንፃሩ ግን እንግሊዞች የሚተኩሱት መድፍ መቅደላ አፋፍ ላይ ብዙ ጉዳት አደረሰ:: እንዲያውም እንግሊዞች ከተኮሷቸው የመድፍ ጥይቶች አንዱ ለጥቂት ቴዎድሮስን ስቶ አጠገባቸው የነበረውን ወታደር ገደለ::






በእንግሊዞች ዒላማ ስር የገባው የኢትዮጵያ ጦር ዕልቂት

ከዚህ በኋላ መልክተኛ ልከው የጦሩን ሁኔታ ቢያስጠይቁ ሹሞቻቸው በሙሉ ሞተዋል የሚል መርዶ ደረሳቸው:: ቴዎድሮስ በደረሰው ጉዳት አዝነው የመዋጊያ ቦታቸውን ከፋላ ወደ ሰላምጌ አዛወሩ:: የመኳንንቱ ዕልቂት፣የሠራዊቱ መሸሽ እና አሁን ደግሞ ይተማመኑበት የነበረው ሴቫስቶፖል የሚባለው ትልቁ መድፍ ከሸፎና ተሰንጥቆ በማየታቸው በእጅጉ ተብሰለሰሉ:: በእንግሊዞች ዝግጅት ላይ፣የኢትዮጵያ መኳንንት ክህደት እና ደባ ታክሎበት እሳቸው ወደ መሸነፍ እያዘገሙ መሆናቸውን ተረዱት:: ከዚህ የተነሳ፣ራሳም እና ዎልድሜየር አስጠርተው እሳቸው ዘንድ እንዲቀርቡ አደረጉ:: እነራሳም ከፊታቸው ሲቀርቡ “ተዘጋጁ፣ወደ ናፒር የምታደርሱት መልክት አለ:: አሁን እኔ የምጠይቃችሁ ምክር፣በእኔ እና በእንግሊዝ ጦር መሐል እርቅ ለማድረግ የሚቻልበትን ሐሳብ እንድትነግሩኝ ነው” አሉ:: ራሳም ሃሳባቸውን ደግፎ “የሰላም መልክተኞች ቢልኩ ጥሩ ነው” የሚል መልስ ሰጠ::

* ጳውሎስ ኞኞ፦ አጤ ቴዎድሮስ



በእንግሊዞች ዒላማ ስር የገባው የኢትዮጵያ ጦር ዕልቂት

ከዚህ በኋላ መልክተኛ ልከው የጦሩን ሁኔታ ቢያስጠይቁ ሹሞቻቸው በሙሉ ሞተዋል የሚል መርዶ ደረሳቸው። ቴዎድሮስ በደረሰው ጉዳት አዝነው የመዋጊያ ቦታቸውን ከፋላ ወደ ሰላምጌ አዛወሩ። የመኳንንቱ ዕልቂት፣የሠራዊቱ መሸሽ እና አሁን ደግሞ ይተማመኑበት የነበረው ሴቫስቶፖል የሚባለው ትልቁ መድፍ ከሸፎና ተሰንጥቆ በማየታቸው በእጅጉ ተብሰለሰሉ። በእንግሊዞች ዝግጅት ላይ፣የኢትዮጵያ መኳንንት ክህደት እና ደባ ታክሎበት እሳቸው ወደ መሸነፍ እያዘገሙ መሆናቸውን ተረዱት። ከዚህ የተነሳ፣ራሳም እና ዎልድሜየር አስጠርተው እሳቸው ዘንድ እንዲቀርቡ አደረጉ። እነራሳም ከፊታቸው ሲቀርቡ "ተዘጋጁ፣ወደ ናፒር የምታደርሱት መልክት አለ። አሁን እኔ የምጠይቃችሁ ምክር፣በእኔ እና በእንግሊዝ ጦር መሐል እርቅ ለማድረግ የሚቻልበትን ሐሳብ እንድትነግሩኝ ነው" አሉ። ራሳም ሃሳባቸውን ደግፎ "የሰላም መልክተኞች ቢልኩ ጥሩ ነው" የሚል መልስ ሰጠ።

* ጳውሎስ ኞኞ፡- አጤ ቴዎድሮስ

ወዲያው ደጃዝማች ዓለሜና እስረኛው ፕሪዲውክስ የሰላም መልክተኞች ሆነው ወደ እንግሊዝ ጦር እንዲላኩ ተወሰነ። ሚያዚያ ፫ ቀን መልክተኞቹ በበቅሎ ተቀምጠው እና ነጭ ባንዲራ ይዘው እንግሊዞች ወደ ሠፈሩበት አምባ ሄዱ። እዚያ ሲደርሱ በአንድ የእንግሊዝ ዘብ እየተመሩ ከናፔር ድንኳን እንደደረሱ፣የያዙትን ደብዳቤ ሰጡት። ለዚህ ደብዳቤ መልስ እስኪዘጋጅ ድረስ ደጃዝማች ዓለሜ የእንግሊዝን ጦር ሠፈር፣ዝሆኖችና ታላላቅ መድፎች እንዲጎበኙ ናፔር ትእዛዝ ሰጠ። እሱ ይህን ያደረገበት ምክንያት ደጃዝማች ዓለሜ ባዩት ተደንቀው የእንግሊዝ ሠራዊት በጦርነት የማይበገር መሆኑን ለዐፄ ቴዎድሮስ እንዲነግሩ ዐቅዶ ነው።

ደጃዝማች ዓለሜ ጉብኝቱን ከጨረሱ በኋላ በናፔር የተጻፈው ደብዳቤ ተሰጣቸው። እሳቸውም መልክቱን ይዘው ከመመለሳቸው ከአንድ ቀን በፊት በተደረገው ውጊያ በጦር ሜዳ የወደቁትን የፊታውራሪ ገብርዬን አስከሬን እንዲፈልጉ አስፈቅደው ነበር።

ሬሳቸውን ከጠላት ምሽግ አጠገብ ካለው ጉድባ ስር ወድቆ ስላገኙት፣በጎዘንና በቁጭት አንስተው እና አሸክመው መቅደላ ላይ ከቴዎድሮስ ፊት አኖሩት። ዐፄ ቴዎድሮስም ስቅስቅ ብለው ካለቀሱ በኋላ ታማኝ አሽከርና ወዳጃቸው የነበሩትን ገብርዬን በታላቅ ክብር አስቀበሩ። የቀብሩ ሥነ ሥርዓት እንደ ተፈጸመ፣ ከጀነራል ናፔር የተጻፈውን ደብዳቤ፣ደጃዝማች ዓለሜ በቆይታ ቀርበው ለዐፄ ለቴዎድሮስ ሰጧቸው። ወልድማየር ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ የተተረጎመው ደብዳቤ እንዲህ ይላል።

> ግርማዊነትዎ ትናንት እንደ አንድ ጀግና ተዋግተዋል። ግን በእኛ ጥበብ እና ኃይል ድል ሆነዋል። እንደገና ደግሞ በመሐከላችን ደም እንደማይፈስ እናምናለን። ግርማዊነትዎ የእንግሊዝን ንግሥት ከተቀበሉ በግርማዊነትዎ እጅ ያሉትን ኤውሮፓውያን እስረኞች በሙሉ በዛሬው ቀን ከእንግሊዝ ጦር ሠፈር ድረስ በሰላም ይላኳቸው። ይህ ከሆነ ለግርማዊነትዎና ለመላው ቤተሰቦችዎ የክብር አያያዝ እንደማደርግ ቃል እገባለሁ።
>
> *ጠቅላይ አዛዥ ሮበርት ናፒር*



ደብዳቤው ሲነበብ ዐፄ ቴዎድሮስ በጥሞና ካዳመጡ በኋላ "ያልገባኝ ነገር አለ። ይህ በክብር አያያዝ የሚለው ነገር ምንድነው?" ብለው ጠየቁ። ራሳቸው መልሰው "እንደ እስረኛ ተይዤ ነው የክብር አያያዝ የሚለው? ወይስ አገሪቱን ከሽፍታ ሲያጸዱልኝ ነው? ዐውቀዋለሁ በእስረኛነት እንዴት እንደሚይዘኝ ማለቱ ነው? እጄን ለጠላት ሰጥቼ የሰው (የማንም) መጫወቻና መዘባበቻ አልሆንም። የተማረከው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በመባል አይፌዝብኝም፣ የሀገሬን ክብር አላዋርድም። ለመሆኑ ይህ የእንግሊዝ ሰው ስለ መይሳውካሣ ቆራጥና ጀግና መሆኑን አልሰማም? እንዴት እኔ ስንቱን ኀይለኛ እና ጀግና እንደ ቆሎ በእፍኝ ይዤ የኖርኩ፣እንደ እኔ ያለ ጀግና ወታደር ዛሬ ምንም የመጨረሻ ቀኔ ቢሆን በሰው እጅ መያዝ ቀርቶ መጠየቁ እንኳን ንቀት ነው። እኔ ቴዎድሮስ! እኔ ነኝ እስረኛ የምሆነው? የማይሆን ነገር ነው። ከዚህ ከአጠገቤ ሂዱ"* ብለው ሲጮሁ ሁሉም ሃምሳ ሜትር ያህል ርቀዋቸው ቆሙ። አጠገባቸው ከነበሩት ሰዎች ራቅ ብለው ዐፄ ቴዎድሮስ ብቻቸውን ተቀምጠው ሲተክዙ ቆዩ።

ወዲያው ተነስው መሬቱን በግንባራቸው እያስነኩ ሦስት ጊዜ ከሰገዱ በኋላ ሦስት ጊዜ አማተቡ እና የታጠቁትን ባለሁለት አፈሙዝ ሽጉጥ እንደቆሙ መንዘዘው ራሳቸው ላይ ደገኑ። ከእሳቸው ራቅ ብለው ይመለከቱ የነበሩ ሰዎች ሮጠው ወገባቸውን ሲይዙ ግማሾቹ ደግሞ እጃቸውን ይዘው ሲታገሏቸው ሁሉም በአንድነት ወደቁ። ዐፄ ቴዎድሮስም አብረዋቸው ወድቀው ከሚታገሏቸው ሰዎች ለማምለጥ መሬት ላይ ይንከባለሉ ጀመር። በትንቅንቁ መሐል ሽጉጡ ባርቆ ጥይቱ ጆሯቸውን በመጠኑ አቆሰለው። ዐፄ ቴዎድሮስ ራሳቸውን ለመግደል ካደረጉት ሙከራ ከሞት የተረፉት እንደ አጋጣሚ ሆኖ ሽጉጡ ጎርሶ የነበረው አንድ ጥይት ብቻ ስለነበረ ወደ ግንባራቸው አዙረው ለመተኮስ ቃታውን ሲስቡ፣ደግነቱ ሽጉጡ ውስጥ ጥይት ባልነበረበት በኩል በመሆኑ ነበር።

ሁሉም ነገር መረጋጋት ሲጀምር ዐፄ ቴዎድሮስ ቤተሰቦቻቸውን ከመቅደላ ወደ ሰላምጌ አስመጥተው ከእቴጌ ጥሩ ወርቅ እና በጣም ከሚወዱት ልጃቸው ልዑል ዓለማየሁ ጋር በቆይታ ተነጋገሩ።

ከዚያ ቀጥሎ ስለታሰሩት ፈረንጆች ጉዳይ ለመመካከር፣ራስ እንግዳ፣ደጃዝማች አቦዬ፣ባሻ አብተው፣አለቃ እንግዳ ወርቅ ሌሎችም ባሉበት ዐፄ ቴዎድሮስ ስብሰባ አደረጉ። በዚህ ስብሰባ ግማሹ "ሁሉንም በአንድነት ለመያዝ የሚችል ትልቅ የእንጨት አዳራሽ ሰላሰ እዚያ አጉረን ከነሕይወታቸው እናቃጥላቸው" አለ።

ሌላው ተናጋሪ "የለም፣እጅ እና እግራቸውን እየቆራረጥን እንጣላቸው እና እንግሊዞች ሲመጡ ያንሷቸው" አለ። ባሻ አብተው ግን ከሌሎቹ ሰዎች በሃሳብ በመለየት "እነዚህ እስረኞች ቢገደሉ በአገሪቱ ላይ ከባድ መከራ ይደርሳል። ስለዚህ የሚያዋጣው ነገር እስረኞቹን በነፃ መልቀቅ ነው" አሉ። በሕዝቡ መሀል ቆመው የሹማምንቱን ፍርድ ያዳምጡ የነበሩት ፈረንጆች ደንግጠው የቴዎድሮስን የመጨረሻ ውሳኔ ይጠባበቁ ነበር። ዐፄ ቴዎድሮስ ዞር ብለው ሲመለከቱ በፍርሀት የተዋጡትን ፈረንጆች ሲያዩ "እርግጥ ሁላችሁንም እንድገድላችሁ ተመክሬ ነበር። ይሁን እንጂ በእግዚአብሄር ዘንድ እኔን ታስጠይቁኛላችሁ እና አይሏችሁ አልገድላችሁም አትፍሩ፣ቤተሰቦቻችሁን ሁሉ ይዛችሁ ወደ እንግሊዞች ሠፈር ሂዱ" ብለው አሰናበቷቸው።

በነፃ መለቀቃቸውን ከነገሯቸው በኋላ፣እስረኞቹ ሚስቶቻቸውን እና ልጆቻቸውን እንዲሁም ጓዛቸውን ይዘው ሲመጡ አዩዋቸው። ወዲያው "እባካችሁ ያን ጠላቴን ስተርንን አታሳዩኝ" አሉ። ይህን የሰማው ምልድሜየር ሮጦ ሄዶ ስተርንን እንዲደብቀው ለራሳም ነገረው። ከዚያ በኋላ ሌሎቹ እስረኞች ተሰባስበው ቴዎድሮስ ዘንድ ቀረቡ። ዐፄ ቴዎድሮስ ራሳምን ጠሩት እና አጠገባቸው ሲደርስ "ደህና ያግባህ ወዳጄ፣እኔና አንተ ዳግመኛ አንተያይም። ከእንግዲህ የምትሰማው የእኔን መሞት ነው" አሉት። እሱም እሳቸው ወደቆሙበት ቦታ ጠጋ ብሎ እጃቸውን ስሞ ሲለያዩ ሌሎቹ ፈረንጆች ትንሽ ራቅ ብለው ይጠብቁት ነበር። በዚያን ዕለት የተለቀቁት እስረኞቹ ሁሉም አይደሉም። ሆኖም በዕለቱ የተለቀቁት እስረኞች፣በደጃዝማች ዓለሜ እና በአቶ ሳሙኤል ሸኝነት ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ሲሆን ከእንግሊዞች ጦር ሠፈር ሲደርሱ በታላቅ ደስታና በጭብጨባ ተቀበሏቸው።



በማግስቱ ደግሞ የቀሩት እስረኞች፣ሚስቶቻቸውና ልጆቻቸው ሁሉ ከነጓዛቸው ጭምር እንዲሄዱ ፈቀዱላቸው። በዚያን ዕለት በጠቅላላው የተለቀቁት እስረኞችና ቤተሰቦቻቸው ጭምር ፳፯ ሰዎች ናቸው። እስረኞቹን በሙሉ ከለቀቁ በኋላ፣ዐፄ ቴዎድሮስ እንድ ትልቅ ድንጋይ ላይ ቁጭ ብለው፣ራሳቸውን በሁለት እጃቸው ይዘው ሲተክዙ ቆዩ። ከዚያም ከተቀመጡበት ብድግ ብለው ወደ መቅደላ አፋፍ ሲወጡ የተከተሏቸው አራት የጦር አለቆችና ጥቂት ወታደሮች ብቻ ነበሩ። ሆኖም የመጨረሻ ውጊያ ለማኪያሄድ አቅደው መቅደላ የተገኙትን ወታደሮቻቸውን ሲያዘጋጁ አመሹ። ሚያዚያ ፮ ቀን ጧት በ፫ ሰዓት ገደማ፣ ፀሐይዋ ዙሪያውን በጥቁር ቀለበት የተከበበች መስላ ሲያዩ "ይህ ነገር የደም መፍሰስ ምልክት ነው" ብለው ተናገሩ ይባላል።

ሰኞ የፋሲካ ዕለት፣የእንግሊዝ ጦር ወደ ፉላ እና ሰላምጌ ሲያመራ ዐፄ ቴዎድሮስ በመነፅር ተመለከቱ። ብዙም ሳይቆይ እንግሊዞቹ እየተኮሱ ወደፊት መገስገስ ጀመሩ። ቴዎድሮስ የነበራቸው ምኞት ከፈረሳቸው ደንደስ ሳይወርዱ መሞት እንጂ፣በሕይወት እያሉ እጃቸውን ለጠላት ላለ መስጠት ወስነዋል። ለዚህ ብለው፣ፈረሳቸው ላይ ተቀምጠቀውና ቦታ እየለዋወጡ ጠመንጃቸውን ወደ ጠላቶቻቸው ይተኩሱ ጀመር። ከዚያም ከፈረሳቸው ጀርባ ወርደው፣እንግሊዞች ወደ መቅደላ አምባ እንዳይገቡ የቋቲትን በር እሳቸው ራሳቸው በድንጋይ ዘጉ። ይሁን እንጂ የእንግሊዝ ጦር ብዛት ስለ ነበረው፣እያጠቃ ወደ አምባው ተጠጋ። ፀዔ ቴዎድሮስ ደግሞ ወደ አምባው መሐል አፈገፈጉ። ወዲያው ከእንግሊዞች ደጀን ተኩሱ አይሎ የመድፍ ጥይት የመቅደላን ሜዳ አረሰው (ደበደበው)። በዚህን ጊዜ አጠገባቸው የነበረው፣አቶ አማረ የሚባለው ጋሻ ዣግሬ "ጃንሆይ እጃችንን እንስጥ" ብሎ ቢያማክራቸው "የለም! በሰዎች እጅ ከመውደቅ በአንድዬ እጅ መውደቅ ይሻላል" አሉት። ይህን እየተነጋገሩ፣የእንግሊዝን ጦር ሁኔታ በመነፅር ተመለከቱ። ከመቅደላ አፋፍ አካባቢ ብዙ የተኩስ ድምፅ ባለመሰማቱ ይሁን አይሁን ባይታወቅም የእንግሊዞቹ ጦር ተበረታትቶ በሩጫ ይገሰግስ ጀመር። ቴዎድሮስ በበኩላቸው ከእርስዎ አንለይም ባሏቸው ሰዎች ታጅበው፣በወገባቸው ሽጉጥ አገንድረው የጠመንጃቸውን የመጨረሻ ጥይት አጉርሰው በሙተኮስ ላይ እያሉ አጠገባቸው ካሉት ሰዎች መሐከል በጥይት እየተመቱ ወደቁ።

ሁኔታው አስጊ በመሆኑ እንደገና ወደ መቅደላ አፋፍ መሐል ሲሄዱ እዚያ ከተመደቡት ሰዎች መሐከል የተገኙት ሰዎች ቁጥር ውስን ነበር። በዚህን ጊዜ ቀደም ሲል በወሰኑት መሠረት፣በፈረሳቸው ደንደስ ላይ እያሉ ለመሞት ቆርጠው፣ፈረሳቸውን እየጋለቡ በያዙት ጠመንጃ የመጨረሻዎቹን ጥይቶች ወደ እንግሊዞቹ ይተኩሱ ጀመር። እንግሊዞቹ በበኩላቸው ጠመንጃና መትረየስ ይተኩሱ ነበር። ሆኖም እንግሊዞቹ ከተኮሱት አንዱም ጥይት ዐፄ ቴዎድሮስን ሳይነካቸው ቀረ። "እንግሊዞች ዐፄ ቴዎድሮስን በሕይወት እያሉ ለመማረክ ስለ ፈለጉ ወደ እሳቸው አነጣጥረው አይተኩሱም ነበር" በማለት አንዳንድ የታሪክ ደራሲያን ጽፈዋል።

ቴዎድሮስ እጄን አልሰጥም በሚል ወኔ፣ፈረሳቸው እስኪደክም ድረስ በመመላለስ እና ቀጥሎም ከፈረሳቸው ወርደው፣ወደ ቋቲት በር ተጠግተው በሳንቃ ቀዳዳ እያሾለኩ ተኮሱ። ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ መቅደላ አምባ መሐል ከመውጣቸው በፊት ወልደ ጋብር የሚባለውን ታማኝ አሽከር ወደ ኋላ አስቀርተው ሌሎቹን "ቃል ከገባችሁልኝ መሀላ እግዜር ይፍታ ብያለሁና ሽሹ። እኔ ግን በጠላቴ እጅ አልወድቅም" ሲሏቸው፣ወታደሮቹ እያለቀሱ ተለይተዋቸው ሄዱ። እሳቸው ደግሞ ወደ መቅደላ ከፍተኛ ቦታ ከወጡ በኋላ፣ወደ ወልደ ጋብር ዞር ብለው "በእንግሊዞች እጅ ከመያዝ ራሴን እገድላለሁ" አሉ እና ሽጉጣቸውን አፋቸው ውስጥ ከትተው ተኮሱ። ጥይቷ በአፋቸው ገብታ በላንቃቸው በኩል አልፋ በማጅራታቸው ወጣች።

አንዲት ኢትዮጵያን ለመመሥረት፣ለማልማትና ሕዝቧን ለማሠልጠን በቆራጥነት የተነሱት አባ ታጠቅ ካሣ፣የኋላው ዐፄ ቴዎድሮስ በተወለዱ በሃምሳኛ ዓመታቸው በንገሡ በ፲፫ኛው ዓመት፣ሚያዚያ ፮ ቀን ፲፰፻፷ ዓ.ም. መቅደላ አምባ ላይ በራሳቸው ሽጉጥ ራሳቸውን ገደሉ። እንግሊዞች በበኩላቸው ወደ መቅደላ አፋፍ ለመግባት የቋቲትን በር በመድፍ ጥይት በረገዱት። ጥቂት ወታደሮች የጥይት ድምፅ ወደ ሰሙበት ስፍራ ሮጠው ሲደርሱ አንድ ሰው በጀርባው መሬት ላይ ተንጋሎ አዩ። እነኛ ሁለት ወታደሮች የሰውዬውን የአንገት ሀብልና የጣት ቀለበት አውልቀው ወሰዱ። እግር እየጎተቱ ካንገላቱ በኋላ ሸሚዙን በመቀስ አጨዱ። ይህን መሰል ፍዳ የደረሰው በቴዎድሮስ ላይ ነበር።





" ጀግናው ዐፄ ቴዎድሮስ የሽጉጣቸውን ጥይት እንደ ብራንዲ ሲጠጡ[1]።"

[1] ገሪማ ታፈረ ፡- አባ ታጠቅ ካሣ፡ የቋራው አንበሳ



" ጀግናው ዐፄ ቴዎድሮስ የሽጉጣቸውን ጥይት እንደ ብራንዲ ሲጠጡ[1]።"

[1] ገሪማ ታፈረ ፦ አባ ታጠቅ ካሣ፡ የቋራው አንቦሳ



ዐፄ ቴዎድሮስ ሕይወታቸው ባለፈችበት ወቅት የእንግሊዝ ወታደሮች እንደደረሱ።

የዐፄ ቴዎድሮስ አስከሬን መሆኑ የታወቀው ሚስተር ራሳም ከተናገረ በኋላ ነበር። ጀነራል ናፒር እንደተመኘው ዐፄ ቴዎድሮስን በሕይወት እያሉ ለመማረክ ስለ አልቻለ በእጅጉ ተቆጨ።

ዐፄ ቴዎድሮስ መሞታቸው ሲታወቅ ከተሰሙት እንጉርጉሮዎች አንደንዶቹ የሚከተሉት ናቸው።

ገደልን እንዳይሉ ሞተው አገኟቸው
ማረክን እንዳይሉ ሰው የለ በእጃቸው
ምን ይሉ እንግሊዞች ሲገቡ አገራቸው

ገሪማ ታፈረ በዚህ ርእስ የጻፉት ግጥም የቴዎድሮስን አሟሟት ገላጭ ስለሆነ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል።



የመቅደላን ጋራ መርጦ ቴዎድሮስ
ሰይፉን ልብስ አድርጎ ጦሩንም ትራስ
ቢርበው ሽጉጡን አየነው ሲጎርስ
አርባ ጹሞ ጹሞ ፋሲካ ሲደርስ
በአፈር ገደፈ አሉ የአበሻ ንጉሥ

የናፖሊዎን እና የቴዎድሮስ ታሪክ ተመሳሳይነት አለው ቢባልም፣የሁለቱ ነገሥታት የግዛት ፍጻሜ ሲፈተሽ ደግሞ፣ናፖሊዮን ተማርኮ በመጀመሪያ ከእስር ቤት ቢያመልጥም ለሁለተኛ ጊዜ ተማርኮና በእስር ማቅቆ በመሞቱ ክብሩን ዝቅ እንዳደረገው ታሪክ ጸሐፊዎች አትተዋል።

በአንጻሩ ዐፄ ቴዎድሮስ በወሰዱት ከመማረክ ይልቅ በራሳቸው ሽጉጥ ሕይወታቸውን በመሰዋታቸው ተማርኮ ከመንገላታት እና ከውርደት ከመዳናቸው በላይ፤ ለራሳቸው እና ለሀገራቸው አኩሪ ታሪክ ትተው በማለፋቸው የማያደንቃቸው ሰው የለም ቢባል ከዕውነት የራቀ አይደለም። የዐፄ ቴዎድሮስ አልማረክም ብለው የወሰዱትን ውሳኔ አድናቆታቸውን የገለጡ ታሪክ ጸሐፊዎች ብዙዎች ናቸው። ይህን በተመለከተ ሌሎች ገጣሚዎች የጻፉትን ግጥም ቀንጫጭቤ እና የራሴንም አክዬበት በማቀነባበር አቀርባለሁ።

በሰልፍ በውጊያ በአስተጣጠቃቸው
መቶ ሺሕ ሰው የሚከተላቸው
እንደ ናፖሊዎን ዓለም ያወቃቸው
የኢትዮጵያ ንጉሥ ቴዎድሮስ ናቸው።
ንጉሥ ናፖሊዮን መማረኩን ሰምተው
አባ ታጠቅ ሞቱ ጥይትን ጠጥተው
ደረስጌ ያበራው የቋራው ፀሐይ
ተኝቷል መቅደላ ጠላት እንዳያይ
የቋራ ባላባት የመቅደላ አንበሳ
ሰርክ ዕለት አዲስ ነው ታሪኩ ሲወሳ



ዐፄ ቴዎድሮስ ሕይወታቸው ባለፈችበት ወቅት የእንግሊዝ ወታደሮች እንደደረሱ።

ከዐፄ ቴዎድሮስ ሞት በኋላ ባለቤታቸውን እቴጌ ጥሩ ወርቅን፣ልጃቸውን ልዑል ዓለማየሁንና የሦስት ዓመት ዕድሜ ያለውን ሌላ ሕፃን ልጅ፣እንዲሁም የዘረፏትን ንብረቶች ይዘው ወደ እንግሊዝ ጦር ሰፈር ወረዱ:: በማግስቱ ማክሰኞ ዕለት የንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ የቀብር ሥነ ሥርዓት በመቅደላ መድኀኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ተፈጸመ::

ዐፄ ቴዎድሮስ የውጭ አገር ሰዎችን ዓላማ በሚገባ የተገነዘቡ ሰው መሆናቸውን በአንድ ወቅት ሲገልጡ "ነጭ አህያ ቆዳው ፈነጣ፣ልቡ አይነጣም" ማለታቸው ይነገራል:: ይህን እምነታቸውን በማጠናከር፣ ለአንድ የፈረንሳይ ቆንሲል እንዲህ ብለው ነግረውታል::

> ማንም መንግሥት በኢትዮጵያ ምድር ቆንሲሎን እንዲያኖር አንፈቅድም:: ሚስተር ፕላውዴንም ቢሆን በአገራችን የሚታወቀው እንደ አንድ ተጓዥ ሰው ነው:: እዚህ በሚቆይበት ጊዜም፣ተሳስቶ የቆንሲልነትን ሥራ ሲሠራ ቢገኝ የሃያ አራት ሰዓት ዕድሜ አይኖረውም:: የአውሮፓውያን አሳብ ለእኛ ስውር አይደለም:: አገር ለመያዝ ሲፈልጉ መጀመሪያ ወንጌላዊ ተብሎ ሰላይ ይላካል:: ሰላዩን ለመርዳት ቆንሲል ይሾማል:: ከዚያም የሰላይ ዘር ይበዛል:: ቆንሲሉንና ዝርያውን የሚጠብቅ ጦር ይታከላል:: እንዲህ ያለ ነገር በሀገሬ እንዲካሄድ እኔ አልፈቅድም:: እኔ የሂንዱስታን ራጃ አይደለሁም:: ቆንሲል ከሚላክብኝ ይልቅ ጦር ቢላክብኝ እመርጣለሁ::

እሳቸው እንዳሉትም እንግሊዝ በመጀመሪያ ሚሲዮናዊያን ላከች:: ቀጥሎም ቆንሲል ላከች:: እነዚህን ነጮች ሲያስሩ ደግሞ ዜጎቼን አስለቅቃለሁ በሚል ሰበብ ጦር ላከች:: ጀግናው ዐፄ ቴዎድሮስ ስለ አገራቸው ፍቅርና ክብር በቆራጥነት ከተዋጉ በኋላ ራሳቸውን የገደሉት በዚህ ምክንያት ነው:: እሳቸው የኢትዮጵያን ነጻነት ለመጠበቅ፣የዘመኑን ሥልጣኔ ወደ አገራችን ለማስገባትና በውጭ አገር ሰዎች ታፍራ እና ተከብራ እንድትኖር ያደረጉት ጥረት እንዲሁም የከፈሉት መስዋዕትነት በቀላሉ ተነግሮና ተጽፎ የሚያልቅ አይደለም:: ዐፄ ቴዎድሮስ አስረውት የነበረው ዶክተር ብላንክ "የእስራት ዘመን በአበሻ አገር" በሚለው መጽሐፍ ውስጥ ስለ ንጉሠ ነገሥቱ አሟሟት ሲጽፍ እንዲህ ብሏል::



> መቅደላ በእኛ ወታደሮች እንደ ተያዘች ወዲያው ስለደረስኩ፣መጀመሪያ የተመለከትኩት የዐፄ ቴዎድሮስን ሬሳ ነበር:: የቴዎድሮስ ሬሳ ፈገግ ብሎ ይታያል:: የዚህ ዓይነት ደስታና ፈገግታ ዐፄ ቴዎድሮስ በቅርቡ ጊዜ በሕይወታቸው ሳሉ አይታይባቸውም ነበር:: ይህም ሁኔታ ፀጥታ የተመላው ብዙ አስደናቂ ሥራዎች ያከናወኑ፣ጨካኝነታቸውና ታላቅነት በታሪክ ውስጥ ተወዳዳሪ የሌለውን የሰው ቅርጽ የያዘ፣ ሕይወታቸው ማለፊያ (መጨረሻ) ጊዜ የወጣትነታቸውን ዘመን፣በጀግንነት ያደረጉትን ውጊያዎችና አሁንም ራሳቸውን በራሳቸው መግደላቸውን አስታውቀው በዚህም መደሰታቸውን ያሳያል::

የዐፄ ቴዎድሮስ ፍላጎት አገራቸው በዘመናዊ አስተዳደር የተመራች ቶሎ ወደ ሥልጣኔ እንድትገሰግስ ነበር:: ይሁን እንጂ በሰበብ አስባቡ እሳቸው የገነቡትን በጎን የሚያፈርሱ ጠላቶች ከየአቅጣጫው እንደ አሸን ይፈሉ ነበር:: ያም ሆኖ መይሳው ካሣ ቆርጠው ተነስተው ነበርና እክሉቸን ሰበብ አድርገው አርፈው ከመቀመጥ ይልቅ ያሰቡትን ከፍጻሜ ለማድረስ ሌት ተቀን ይደክሙ ነበር:: ዐፄ ቴዎድሮስ በተግባር የፈጸሟቸውን ሌሎች ውሳኔዎች የሚከተሉት ናቸው::

- ➢ የመሳፍንትን አገዛዝ ገርስሰው ሥርዓተ መንግሥት አቋቋሙ
- ➢ የባሪያ ንግድ በአዋጅ አስከለከሉ
- ➢ ትምህርትና የቴክኒክ ሙያ እንዲስፋፋ መሠረቱን ጣሉ
- ➢ የቅኝ ግዛት ሰላዮች ዓላማ እንይሳካ አደረጉ
- ➢ ወታደር በዘመናዊ መንገድ ተደራጅቶ በደሞዝ እንዲስተዳደር አደረጉ
- ➢ ለወታደር የሹመት ስያሜ አወጡ
- ➢ መሬት ለገበሬው አከፋፈሉ

የኢትዮጵያን ታሪክ ከሚጽፉት አንዱ የሆኑት ደራሲ ገሪማ ታፈረ "አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ" በሚባለው መጽሐፍ ውስጥ የቴዎድሮስን ማንነትና አሟሟት ሲተርኩ እንዲህ ብለዋል::

> አባ ታጠቅ ካሣ የትግሬን፣የጎንደርን፣የጎጃምን፣የወሎንና የሸዋን ባላባቶች ሁሉ ከእግሩ በታች አንበረከካቸው:: በአገሩ ባላባቶች ነን እያሉ በመንግሥቱ ላይ የተነሱትን አማፅያን በጦርነት እያስገደደ፣ እጅ እግራቸውን ቆራረጠ፣ አንዳንዶቹንም ዓይናቸው እያየ ወደ ገደል ወረወራቸው::

በመጨረሻም ከመጣበት የውጭ አገር ጠላት ጋር በተቻለ መጠን ከተከላከለ በኋላ ለሁዓሊዎች፣ ወይም ለደራሲያን እና ለቱሪስት እንዲመች፣ ተቀመጥ፣ተነሳ እየተባልኩ ትኩስ ዳቦ አልሆንም:: እጄን ለጠላት አልሰጥም:: አገሬን አላስደፍርም፣ክብሬንም ለመኖር ስል አልለውጠውም::

በመቀጠልም ገሪማ ሲጽፉ "የራሱን ሽጉጥ ጥይት በገዛ እጁ እንደ ብራንዲ ጠጥቶ ከዚህ ዓለም በሞት ዐለፈና እንደ አባቶቹ በክብር አንቀላፋ" ብለዋል::

ዐፄ ቴዎድሮስ ያለ ጊዜያቸው የተነሱ ከፍተኛ የሀገር ፍቅር የነበራቸው ታላቅ የአገር መሪ ነበሩ:: ይሁን እንጂ አንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች በጣም አጋንነው የሚጽፉት የተቀናቃኞቻቸውን እግርና እጅ እየቆረጡ ወደ ገደል መወርወራቸውን ብቻ ነው:: ይህን መሰል ተግባር ትክክል አለመሆኑ ባይካድም ታሪክ ጸሐፊዎች ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ ማቅረብ አለባቸው ባይ ነኝ:: ለዚህ መጽሐፍ መደምደሚያውን ዐረፍተ ነገር ከማስፈሬ በፊት፣ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ ስብእና አንዳንድ መረጃዎች ማቅረቡ ተገቢ ይመስለኛል:: ዐፄ ቴዎድሮስ፣የቀድሞው ካሣ ኃይሉ በጣም ጀግና፣እጅግ ደግ እና ባህል አክባሪ ሰው እንደ ነበሩ ከሚቀጥሉት ትረካዎች መረዳት ይቻላል::

<u>ሰውነት እና ስብዕና</u>

ዐፄ ቴዎድሮስ ጥቋቁርና ጎድጎድ ያሉ ዓይኖች፣ ስስ ከንፈሮችና ደፍጣጣ አፍንጫ ያላቸው ሰው ናቸው:: በተቆጡ ጊዜ ዓይናቸው ደም ስለሚለብስ ሲያፈጡ እጅግ ያስፈራሉ:: ቁመታቸው ልከኛ ቢሆንም ፈርጣማ ክንዳቸው ሰፋ ያለ ደረታቸው ለጦርነት ስኬታቸው ረድቷቸዋል:: ጥቁር እና ረጅም ፀጉራቸውን በቅባት አረስርሰው፣ በሹሩባ አሠራር ተጎንጉኖ፣ ከአንገታቸው አልፎ ትከሻቸው ላይ ሲያርፍ ግርማ ሞገስ ይሰጣቸዋል:: ልብሳቸው በአብዛኛው በአገር ውስጥ የተሠራ ሱሪ፣ ቀሚስ (እጀጠባብ) እና ገንባሌ ሲሆን ጋሻና ጣምራ ጦር ከእጃቸው፣ ድግ እና ሽጉጥ ከወገባቸው አይለያቸውም ነበር ይባላል::

ከቄስ ትምህርት ቤት የቀሰሙትን ልማድ በመከተል እህል ውሀ ሳይቀምሱ የዕለት ፀሎታቸውን ያደርሱ ነበር:: ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ካላጋጠማቸው በስተቀር ፀሎታቸውን አያስተጓጉሉም ነበር:: በአገር ባህል ረገድም ቤተ ክርስቲያን ሲያዩ በትምህርተ መስቀል አማትበው አቡነ ዘበሰማያት ደግመው ይሄዳሉ:: በሠርግና በኀዘንም ጊዜ ወግና ሥርዓት ተከትለው ተገቢውን ተግባር ይፈፅሙ ነበር::



<u>ደግነት</u>

ዐፄ ቴዎድሮስ በሰሜን ግዛት የነበሩትን ተቀናቃኞቻቸውን ሁሉ ካሸነፉ በኋላ ፊታቸውን ወደ ሸዋ አዞሩ:: ለውጊያ ተዘጋጅተው ፍልሚያ ከመጀመሩ በፊት የሸዋው ንጉሥ ኃይለ መለኮት ድንገት ታመው ስለዐረፉ ያለ አንዳች እንከን ድሉ የቴዎድሮስ ሆነ:: በዚህ ምክንያት የሸዋን መንግሥት አልጋ ይወርሳሉ ተብሎ የተተነበየላቸው ምኒልክ ተማረኩ:: የ፲፩ ዓመቱ ወጣት ምኒልክ እጃቸው በሰንሰለት ሲታሰር ስቅስቅ ብለው አለቀሱ:: ዐፄ ቴዎድሮስ ወጣቱ በፍርሀት ተውጠው ማልቀሳቸውን ሲያዩ አዘኑላቸውና ሰንሰለቱ እንዲወልቅላቸው አዘዙ:: ከዚያን ቀን ጀምሮ ከዐፄ ቴዎድሮስ ግቢ በቆዩበት ፲፩ ዓመታት ውስጥ እንኳን መታሰር አንድም ቀን ቁጣ ደርሶባቸው አያውቅም::

እንዲያውም ዐፄ ቴዎድሮስ በርኅራኄና በፍቅር ይንከባከቧቸው ነበር:: ይህንንም የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የልጅ ልጅ የሆኑት አቤቶ ምኒልክ በኋላ ሲናገሩ «ዐፄ ቴዎድሮስ እንደ ሁለተኛ አባት ሆነው፣ በዘመኑ እንደ ትልቅ ትምህርት የሚቆጠረውን የመንግሥት አስተዳደርና የውትድርና ሙያ እንዳውቅ የቤተ መንግሥታቸው ታዳጊ ልጅ አድርገው አሳድገውኛል» ብለዋል:: እሳቸው እንዳሉትም ዐፄ ቴዎድሮስ ለወጣቱ ምኒልክ ከነበራቸው መልካም አስተያየት የተነሳ ተንከባክበው ከማሳደጋቸው በተጨማሪ የራሳቸውን ሴት ልጅ እመቤት አልጣሽን ድረውላቸዋል:: በዚህ መሐል አቤቶ ምኒልክ በድንገት ፈንጣጣ ይይዛቸዋል:: በዚያን ዘመን ፈንጣጣ እጅግ አስፈሪ በሽታ ስለነበረ ዐፄ ቴዎድሮስ ወጣቱ እንዳይጎዱ ሰግተው ሐኪም ማፈላለግ ጀመሩ:: አንድ ሚሲዮናዊ ሐኪም ተገኝና አክሚቸው ጠባሳው እፊታቸው ላይ ቢቀርም ምኒልክ ዓይናቸው ከመጥፋት በስተቀር ከሞት አፋፍ አመለጡ:: ከዚያም አንድ ሰው ወደ ዐፄ ቴዎድሮስ ጠጋ ብሎ «እርስዎ የሚገባ ሥራ አልሠሩም»ብሎ ተናገረ::

ዐፄ ቴዎድሮስ ደግሞ ሰውዬውን «ለምን እንዲህ አልክ?» አሉት:: እሱም ሲመልስላቸው «ይህ ልጅ እኮ ከእርስዎ በኋላ ይነግሳል የሚባለው ልጅ ነው:: ቢሞትስ ምን ቸገረዎት እና ነው እሱን አሳክመው ያዳኑት» አላቸው:: ዐፄ ቴዎድሮስ የሰውዬውን ዓይን ትኩር አድርገው እያዩ «አይ ክፉ አትሁን:: አሁን ማን ይሙት እሱን ሕክምና ከልክዬ እንዳይነግሥ ለማድረግ እችላለሁን? ወይስ አሳክሜ ስላዳንኩት ነው የሚነግሠው?» በማለት መካሪውን ሰው አሳፈሩት ይባላል::

የሸዋ ባላባት የሆኑት ገርማሜ ወልደ ሐዋርያት ለዐፄ ቴዎድሮስ የቅርብ ሰው በመሆናቸው በግል ግብር እስከ ማብላት ነጻነት ነበራቸው። ንጉሠ ነገሥቱ የሰጧቸውን አመኔታ በመጠቀም አንድ ቀን ድግስ ደግሰው የግቢ ዘበኞቹን ግብር ሲያበሉና ሲያጠቁ አመሹ። አሳባቸው ተሳክቶ ዘበኞቹ ሁሉ ሰክረው ነፍሳቸውን መሳታቸውን ሲያዩ፣ መሸሻ ከሚባሉት ከዐፄ ቴዎድሮስ ልጅ ጋር ተመሳጥረው አቤቶ ምኒልክን ይዘው ወደ ሸዋ አምልጠው ሄዱ። የምኒልክን ከቁም እስር ማምለጥ ቴዎድሮስ ሲሰሙ፣ «የቆጨኝ የእሱ ከእስር ማምለጡ ሳይሆን፣ ሚስቱን አልጣሽን ይዟት አለመሄዱ ነው» ማለታቸው ለደግነታቸው ሌላው ማስረጃ ነው*። ቀደም ሲል ዐፄ ቴዎድሮስ ገለል አድርገዋቸው የነበሩት ልጃቸው ደጃዝማች መሸሻ አሁን ደግሞ አቤቶ ምኒልክ ከቁም እስር እንዲያመልጡ በማድረጋቸው ከአባታቸው ጋር ይበልጥ መቃቃራቸው ይነገራል።

<u>ጎብዝና እና ጎበዝ መውደድ</u>

አንድ ቁመቱ ዘለግ፣ሰውነቱ ደንደን ያለ ሰው "ከሸዋ ወደ እርስዎ ዘንድ የመጣሁት ለእርስዎ አሽከርነት ለማደር ነው" አላቸው። እሳቸው የሰውዬውን ዓይንና ቁመና ትኩር አድርገው አዩና "ጎበዝ ትመስላለህና በል ከዛሬ ጀምረህ ጋሻጃግሬዬ ትሆናለህ" ብለው መንገድ ሲሄዱ ከፊት ሆኖ እንዲያጅባቸው ፈቀዱለት። እሱም በዚህ አዲስ ሥራው ከፊት፣ከፊት በመሄድ ሲያገለግላቸው ቆየ። አንድ ቀን ባልታወቀ ምክንያት ዐፄ ቴዎድሮስ ጦራቸውን ወደ እሱ ቢወረውሩት በጆሮ ግንዱ በኩል አልፎ አጠገቡ መሬት ላይ ተተከለ። በዚህ ሁናቴ ሰው ሁሉ ሲደነግጥ፣ እሱ ግን በትንሹ ሰግጠጥ ከማለት ውጪ የመደንገጥ ስሜት አላሳየም። የሰዎቹን መደንገጥና የእሱን ሰግጠጥ ማለት በማገናዘብ "አይዞህ፣አይዞህ" ብለው አጽናኑት። እሱ ደግሞ "እፊት፣እፊት ከምሄድ ጋሻጃግሬነቱ ቢቀርብኝ ይሻለኛል" አላቸው። ንጉሡም "ጋሻጃግሬነትህ አይቀርም፣ባይሆን ከፊት መሄድህ ቀርቶ ከኋላ ታጅበኛለህ" አሉትና ከዚያን ቀን ጀምሮ ከኋላቸው ይከተል ጀመር። ወዲያው አንድ ሰው መጥቶ "እንዴ! ይህን ሰው ከኋላ አስከትለው ሲሄዱ ከዚህ በፊት ሊገድሉኝ ነበር ብሎ ቂሙን ለመወጣት አስቦ አንድ ቀን ቢገድልዎትስ?" አላቸው።

* Chris Prouty:- Empress Taytu and Menilek II



ዐፄ ቴዎድሮስም ሲመልሱለት "ጎበዝ ሰው፣ሌላውን ጎበዝ ከኋላው
አይገድለውም" አሉ። ያ ጎበዝ ሰው ለብዙ ጊዜ ከኋላቸው በመከተል
ጋሻጃግሬያቸው ሆኖ ሥራውን ቀጠለ።

አንድ ቀን ደግሞ፣እጅና እግሩ የታሰረ ሰው ከፊታቸው ይቀርባል። የምን ሰው
ነው፣ምን አደረገ?" ብለው ጠየቁ። "ጌታዬ! ሌባና ሽፍታ እያደናችሁ
አምጡልኝ ባሉት መሠረት፣እነሆ ይህን አገር ያሸበረ ሽፍታ አድነን ስለያዝነው
ከፊትዎ አቅርበነዋል" ብሎ የዘብ አለቃው ተናገረ። እሳቸውም "አዬ! ይኽን
የመሰለ ቁመናና የሰውነት አወጣጥ ያለው ሆኖ ምን አሸፈተው? የማይረባ
ነው። ታዲያ ምን ይደረግ? ግደሉታ" አሉ። ሽፍታው ትእዛዛቸውን ሲሰማ
"እንዴት እኔን የመሰለ ሰው ይገደላል?" ብሎ ሲያጉተመትም ሰሙትና "ታዲያ
ምን ይሁን ትላለህ?" አሉት። እሱም ሲመልስ "እኔ ጀግና፣ጎበዝ ሰው ነኝ።
ዛሬ ግን ዕድል ሸሽቶኝ፣ቀን ጥሎኝ ተያዝኩ፣እንዴት እኔ እገደላለሁ? በማለት
በቁጭት ተናገረ። ሰውዬው የተናገረውን ሁሉ በጥሞና አዳምጠው ነበርና "እኮ
ታዲያ ምን ይሁን ትላለህ?" ብለው መልሰው ጠየቁት።

እሱም "እኔ ጎበዝ፣ጀግና ሰው ነኝ፣ማንም ሰው በተኩስ፣በሩጫ፣በት
አይስተካከለኝም፣ እንዴት እኔ እገደላለሁ?" እያለ በቁጭት ተናገረ።
ቴዎድሮስም ሰውዬው ያለውን በፀጥታ አዳምጠው እንዴት፣እንዴት ይናገራ
በል አሁን እንግዲህ ጉብዝናህን እናያለን" አሉና ጎራዴያቸውን ከወገባቸው ፈ
ከዚያ ጦራቸውን ጨምረው ለአጋፋሪያቸው ሰጡ። ሕዝቡ ቆሞ ምን ሊያደ
ነው ብሎ ሲጠብቅ፣ወደ ሜዳው መሐል ገብተው "አንተ የሽፍቶች አለቃ
እንታገል" አሉት።

ዙሪያውን የነበሩት መኳንንት ሁሉ "እንዴ! ለምን እንዲህ ያደርጋሉ?" እያሉ
ጮሁ። ዐፄ ቴዎድሮስ ደግሞ "ቆይ የዚህን ፎካሪ ሰው ጉብዝና እናያለን። እሱን
መሬት ላይ ካላንደባለልኩ እኔ ሞቼያለሁ" ብለው ትግል ገጠሙት። የሽፍቶቹም
አለቃ የዋዛ ሰው አልነበረምና ግብግብ ሲጋጠሙ ለብዙ ደቂቃዎች
ተቋቋማቸው። በመጨረሻ ግን ዐፄ ቴዎድሮስ ታግለው ከጣሉት
በኋላ፣ከውንጀላው ነጻ አደረጉትና እሳቸው በአሽከርነት ቀጠሩት።

<u>የባህል አክብሮት</u>

ዐፄ ቴዎድሮስ ለባህል ያላቸው አክብሮት በቀላሉ የሚታይ አልነበረም:: አንድ ቀን በሁለት መኳንንት ግራና ቀኝ ታጅበው፣ፈረስ ላይ ተቀምጠው ወደ ዳር አገር ሲሄዱ በሩቁ ሰዎች እየጨፈሩ ሲመጡ አዩ:: ወዲያው ሠርገኞች ይሆኑ እንዴ?" ብለው ጠየቁ:: ጥቂት እንደሄዱ እነዚያ በሩቁ ያይዋቸው ሰዎች አሳቸው አጠገብ ሲደርሱ ሠርገኞች መሆናቸውን አረጋገጡ:: ሙሽራው በፈረስ፣ ሙሽራይቱ በበቅሎ ተቀምጠው ሲመጡ፣ ሠርገኞቹን ሰላምታ ለመስጠት ከፈረሳቸው ለመውረድ ዳዳቸው::

አብረዋቸው የሚያጅቧቸው መኮንኖች አንዲት ቃል ሳይተነፍሱ ሠርገኞቹ ከፊታቸው ደረሱ:: በዚህን ጊዜ ቴዎድሮስ ከፈረሳቸው ላይ ወርደው "የአብርሃምና የሣራ ጋብቻ ያድርግላችሁ" ብለው የገንዘብ ስጦታ አድርገውላቸው እሳቸው ከቆሙበት እስኪርቁ ድረስ ጠብቀው ሙሽሮቹ ራቅ ሲሉ እንደገና ፈረሳቸው ላይ ተቀምጠው ጉዟቸውን ቀጠሉ:: አጠገባቸው ከነበሩት መኳንንት አንዱ "ጌታዬ በጣም አጥፍተዋል:: እንዴት እርስዎን የሚያህል ታላቅ ንጉሥ፣የሀገር ባህል ነው ብለው ከፈረስዎ ይወርዳሉ? ይህን የመሰለ የሀገር ባህል መተው ነው" በማለት በቁጭት ነገራቸው:: ዐፄ ቴዎድሮስ ለመከራቸው ሰው የተናገሩት ቃል "አንተ ምንም አትረባም! እኛ ዘወትር የምናገኘውን ደስታ፣ለእነዚህ ወጣት ሙሽሮች ለአንዲት ደቂቃ እንኳን እንዳይደሰቱ ትከለክላቸዋለህ?" አሉት ይባላል::

ዛሬ በዓለም አቀፍ ደረጃ በትልቅ ዝግጅት የሚታየውን የቁንጅና ውድድር ዐፄ ቴዎድሮስ የዛሬ ፩፻፶ ዓመት ገደማ በታላቅ ድምቀት እንዲታይ ያደርጉ ነበር ቢባል ሐሰት የሚመስለው ሰው ይኖራል:: ለማንኛውም የተካሄደው የቁንጅና ውድድር ሥርዓት እነሆ::



ትረካውን ያዘጋጀሁት ከጳውሎስ ኞኞ:- አጤ ቴዎድሮስ እና ከገሪማ ታፈረ:- መይሳው ካሣ: የቋራው አንበሳ በሚባሉት መጽሐፎች ውስጥ ከመዘገቡት ቆንጠር አድርጌ ነው:: መስቀል በተከበረ በ፪ኛው ቀን በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. የተካሄደው የቁንጅና ውድድር ሥርዓት እንደሚከተለው አቀርባለሁ::

ከጧቱ ፫ ሰዓት ሲሆን በዓሉ ወደሚከበርበት ሜዳ የገጠሩና የከተማው ሕዝብ ይጎርፍ ጀመር:: ፬ ሰዓት ሲሆን ምርጥ መሣሪያ የያዙ ወታደሮችና አጋፋሪዎች ሰልፈኛውን ለማስተናበርና ፀጥታውን ለማስከበር በበዓሉ ሜዳ ተሰማሩ:: ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ፊታውራሪ ገብርዬ በሠራዊቱ ታጅቦ ሰንደቅ ዓላማ እያውለበለበ አጤ ሰቀላ ከረብታ ደረሰና የዙፋኑን አቀማመጥ ተመለከተ:: እንዲሁም ንጉሠ ነገሥቱ በፈረሶች በሚሳብ ሠረገላ ላይ ተቀምጠው ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ቤል ባሠለጠናቸው ወታደሮች እየታጀቡ መጥተው በዙፋናቸው ላይ ተቀመጡ:: እምቢልታና መለከቱ ተብላላ፣ ነጋሪት አጅብር፣ አጆብር፣ውጋው፣ውጋው እያለ ይጎሰም ጀመር:: ዘፋኞች ይዘፍናሉ አዝማሪዎች ይዘምራሉ፣ወታደሮች ይጨፍራሉ:: በዚህ ዓይነት ይዞታ ተድላ ደስታ ሆኖ ሲደባለቅ በመካከሉ ለውድድሩ የታጩት ወይዛዝርት ጥልፍ ቀሚሳቸውን እያንሰረተቱ ተቀብተው፣ተኩለው ወደተዘጋጀላቸው ቦታ ያልፋሉ::

ቀጥሎም ምርጫው በሚፈፀምበት ጎል እየገቡ፣ውበታቸው እና ደምግባታቸው፣የላሕየ ገጻቸው አወራረድ፣ የፀጉራቸው ሥሬት፣የቁንድላቸው እርዝመት፣ ሽንጣቸው፣ዳሌና ተረከዛቸው እየተመረመረ የምርጫው ሥነ ሥርዓት ይጀምራል:: በመካከሉ ከበሰቀልት ወረዳ ከመቋማ ማርያም የመጣችው ትውልዷ ከመቄት አዝማች ወገን የሆነ የደጃዝማች ይልማ አሰፋ ልጅ፣ ጣይቱ ይልማ አንደኛ ሆናለች:: ከጎንደር አዲስ ዓለም የመጣችው፣ የመሐመድ ኩርማን ሚስት የሸኽ መሐመድ ጌታ ልጅ ተዋበ፡ የተባለች እስላሚቷ በጠጉሯ ማማር፣ በቁንዳላዋ አወራረድና መርዘም ሁለተኛነት አግኝታለች::

ከዚህ በኋላ ዮሐንስ ቤልና ፊታውራሪ ገብርዬ የምርጫውን ውጤት ለንጉሠ ነገሥቱ ለመንገር ወደ ዙፋኑ ቀረቡ:: ወዲያው ጣይቱ ይልማ አንደኛ፣ተዋበች መሐመድ ጌታ ሁለተኛ መሆናቸውን ከገለጹ በኋላ ተመራጮች ከዙፋኑ ፊት በመቅረብ እጅ እየነሱ ሽልማታቸውን ተቀብለው፣ ለመኳንንት ለሊቃውንት እና ለካህናት የምሳ ግብዣ ተደረገ::

ዐፄ ቴዎድሮስ ለእንስሳት በተለይም ለአንበሳ ልዩ ፍቅር ነበራቸው። ብዙ ሥዕሎች ላይ እንደሚታየው በአደባባይ ከጎናቸው የማይለዩ አንበሶች ነበሯቸው። ስለ አንበሳ ከተነሳ አንድ ጊዜ የሆነውን መጥፎ አጋጣሚ ገሪማ ታፈረ በጻፉት መይሳው ካሣ፡ የቋራው አንበሳ በሚባለው መጽሐፍ ውስጥ ያለውን ታሪክ ላንሳ። ዐፄ ቴዎድሮስ ለመዝናናት ሲፈልጉ በግንባር ቀደምነት ከልጃቸው ከልዑል ዓለማየሁ ጋር መጫወት ያዘወትሩ ነበር። ከዚያ ቀጥሎ የሚያስደስታቸው ከለማዳ አንበሶቻቸው ጋር መዝናናት ነው። አንበሶቻቸውን ብዙ ዘዴ እንዲሠሩ አሰልጥነዋቸዋል። ታዲያ ለመዝናናት ሲፈልጉ እገሌን ጥራ ይላሉ። የተጠራው ሰው መጥቶ እጅ በሚነሳበት ጊዜ፣ከአጠገባቸው የተኛውን ገራም አንበሳ በልዩ ዘዴያቸው ይጠቁሙታል። አንበሳው በሠለጠነው መሠረት ትእዛዛቸውን ተቀብሎ በሁለት እግሩ በመቆም ያዝኩህ እያለ ሲያጉረጠርጥ ከአንበሳው ግርማና ክብደት የተነሳ እኩሉ ሰው ሲሸሽ፣ሌላው ደግሞ ሲወድቅ እየተሖለከቱ አጥብቀው ይደሰቱና ይስቁ ነበር ይባላል።

ዐፄ ቴዎድሮስ የዓለምን ሁኔታ ጠይቀው የተገነዘቡ፣ዐረብኛ ቋንቋ ተናገሪ እና ግዕዝና አማርኛ ጥልቅ ዕውቀት የነበራቸው ሰው ነበሩ። ግጥም ገጣሚ፣በገና ደርዳሪም እንደነበሩ ይነገራል። በአጠቃላይ በሰው ልጅ ላይ ሊኖር የሚችለው ጠባይ ሁሉ አላቸው ማለቱ ይቀላል። አስተዋይነት፣ርኅሩኅነት፣ቁጡኛነትና ችኩልነት ታይቶባቸዋል። ለአገራቸው የነበራቸው ፍቅርና ቀናተኛነት ወደር የለውም። ይህንን ጽኑ የአገር ፍቅራቸውን ይበልጥ የሚገልጠው፣ደራሲ ዶክተር ከበደ ሚካኤል መኩሪያ "የዕውቀት ብልጭታ" በሚባለው መጽሐፍ ውስጥ፣ በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. የጻፉት ግጥም ነው።

<u>ዐፄ ቴዎድሮስ እና ሁለት የውጭ አገር ሰዎች</u>

በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት
ሁለት ፈረንጆች መጥተው በአንድነት
በኢትዮጵያ መሬት እውሬ እንዲያድኑ
ዐፄ ቴዎድሮስን ፈቃድ ቢለምኑ
እሺ አሉዋቸውና እያመሰገኑ
ለማደን ሲሄዱ ፈቃዱን አግኝተው
በረገጡት አገር ሁሉን ተመልክተው
ለይተው ለማወቅ እያንዳንዱን ቦታ
ጽፈው እያነሱ የመንገዱን ካርታ



ሲሠሩ ከረሙ የስለላ ሥራ
አብሯቸው የሚዞር መንገድ እየመራ
የማይለያቸው አንድ ሰው ነበረ
ከእነሱ ጋር ቆየና አብሮ እየዞረ
ሁለቱ ፈረንጆች አደኑን ጨርሰው
ከተማ ሲገቡ ኋላ ተመልሰው
መሰለላቸውን ካርታም እንዳነሱ
የሠሩትን ሥራ ነግሮ ለንጉሡ
ሁሉን አስረዳቸው ለአፄ ገለጠና
ተግቶ ሲጠባበቅ ጥንቱን ታዟልና።
የመጡበት አሳብ ሌላ በመሆኑ
ነገሩን ሲሰሙ ንጉሡ አዘኑ።
ከዚያም ፈረንጆቹ ፈጥነው ሊመለሱ
ሊሄዱ አገራቸው አስበው ሲነሱ
ቀጠሮ ጠየቁ ፈቅደው መሰናበት
ዐፄ ቴዎድሮስም ወዳያው በደግነት
ምሳ ጋበዙና በመልካም አብልተው
አክብረው በብዙ ደስም አሰኝተው
ጥሩ ወርቅና ብር እንዲሁም ሉል ጭምር
ሰጥተው ሲሸኟቸው ጠርተው አንዱን አሽከር
እስከ መርከብ ድረስ ተለይቶ ሳይቀር
ከሸኘ በኋላ ሲገቡ ከመርከብ
የእግራቸውን ጫሞች አውልቆ እንዲያጥብ
አዘዙት ንጉሡ እሱም እሺ ብሎ
ሁለቱን ፈረንጆች ሄደ ተከትሎ።
የታዘዘውን ቃል ገልጦ እያሳወቀ
መርከብ ሲሳፈሩ ጫሞችን ጠየቀ።
ሁለቱ ፈረንጆች ይህንን ሲሰሙ
በንጉሡ ትዛዝ እጅግ ተገረሙ።

ምክንያቱን ማወቅ ስለናፈቃቸው
እንዲወርድ አድርገው ከመርከብ ዕቃቸው
ጠይቀው ለማግኘት ነገሩን ከንጉሡ
ፈጥነው ካሽከሩ ጋር አብረው ተመለሱ።
ዐፄ ዘንድ ሲደርሱ ነገሩን አውርተው
መደነቃቸውን ለንጉሡ አመልክተው
የዚህን ምክንያት ሳይሄዱ እንዲያውቁ
እንዲገልጡላቸው ለምነው ጠየቁ።
ንጉሡም መለሱ አገሬ ገብታችሁ
የኢትዮጵያን አፈር በዓይናችሁ አይታችሁ
ከሁሉም መብለጡን ስለተረዳችሁ
እኔም አገራችን ብትሉ እንመለስ
ከወርቅም ከሉልም ለጠሁ በመለገስ።
የኢትዮጵያ አፈር ግን በጣም የነጠረ
ከወርቅም ከሉልም ይበልጥ የከበረ
ውድ በመሆኑ አልችልም ለመስጠት
አሁንም እነሆ በዚሁ መሰረት
እናንት አገራችሁ ከዚህ ስትሄዱ
ካገሬ ውብ አፈር ከጠራው ከውዱ
ጫማ ያነሳውን እንኳን እንዳትወስዱ
በጣም ነፍጌ ነው በሄዳችሁ ጊዜ
ይህን እንዲፈጽም አሽከሬን ማዘዜ።



**ዐፄ ቴዎድሮስ በጠላቶቻቸው መፈራትንና መጠላትን፣ለሀገሩ አንድነትና ክብር ከቆመው ወገን ደግሞ ፍቅር እና ክብርን አትርፈዋል። ይህን ታሪካዊ ተግባር መፈጸማቸውን ምክንያት በማድረግ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ ለአገራቸው ክብር ሕይወታቸውን የሰዉበትን መቶኛ ዓመት ለማክበር የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር የተጫወቾውን ሚና ከዚህ ቀጥሎ በአጭሩ አቀርባለሁ።**

በዘመኑ የማስታወቂያ ምኒስትር የነበሩት ደጃዝማች ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት የጻፉትን "ቴዎድሮስ" የሚባለውን ቴአትር በማሳየት የሚገኘውን ገቢ ለኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር መቋቋሚያ እንዲሆን ፈቀዱ። ቴአትሩ ተጽፎ ከታየ ከአሥራ ዘጠኝ ዓመት በኋላ፣አሁን ቴአትሩ እንደገና እንዲታይ መፈቀዱን ታሪካዊ አጋጣሚ ለመጠቀም፣ የቴአትሩ መክፈቻ ቀን፣የዐፄ ቴዎድሮስን መቶኛ ሙት ዓመት መታሰቢያ እንዲከበር የደራሲያን ማኅበሩ አባላት ሐሳብ አቀረቡ።

የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር ሊቀ መንበርና የቴአትሩ ደራሲ ደጃዝማች ግርማቸውም ተክለ ሐዋርያት እና የማኅበሩ ዐቃቤ ንዋይ የሆኑት ደራሲ ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ፣ በዚያን ጊዜ የአዲስ አበባ ከንቲባ ለነበሩት ቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወት ዕቅዱን ነገሯቸው። ከዚያ በኋላ ሦስቱም ሰዎች፣ይህ ተገቢ እና የተቀደሰ ሐሳብ በመሆኑ ከስምምነት ላይ ደረሱና አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ ጀመሩ። ቀጥሎም ዐፄ ቴዎድሮስ ለተሰዉበት መቶኛ ዓመት መታሰቢያ ዕለት ቴአትሩ እንዲታይ ከስምምነት ላይ ደረሱ። ከንቲባ ዘውዴ ገብረ ሕይወት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቴአትሩን እንዲያዩ ጋበዟቸው። እግረ መንገዳቸውንም ቴአትሩ በሚታይበት ቀን ለዐፄ ቴዎድሮስ አደባባይ እንዲሰየምላቸው እና የመታሰቢያ ሐውልት እንዲቆምላቸው ጠየቁ። ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ ሁለቱንም ሐሳቦች ተቀብለው ወዲያውኑ የይሁንታ ፈቃድ ሰጧቸው*።

ለዚህም ነው ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በ፲፱፻፷ ዓ.ም. ለዐፄ ቴዎድሮስ መንገድና አደባባይ የሰየሙላቸው። ቦታው ዛሬ ሴቫስቶፖል የሚባለውን የመድፍ ቅርፅ እንዲመስል ተደርጎ የተሠራው "ሐውልት ነው" ተብሎ አሁን በተቀመጠበት ቦታ ላይ (ቴዎድሮስ አደባባይ) የዐፄ ቴዎድሮስን ክብርና ሞገስ የሚያሳይ ሐውልት ለመትከየ ቦታው ተዘጋጅቶ ግርማዊ ቀደማዊ ኃይለ ሥላሴ የሐውልቱን የመሠረት ድንጋይ ሲያስቀምጡ የተናገሩት ቃል እነሆ።

"ዐፄ ቴዎድሮስ ከባለታሪኮች አንዱ በመሆናቸው፣ታሪካቸውን ለመጪው ትውልድ የሚያወርስ መታሰቢያ እንዲቆምላቸው አዝዘን የእኝህን ታላቅ ሰው ሐውልት የመሠረት ድንጋይ በዚህ ቦታ ስናኖር፣ ጀግንነታቸውን እና ቆራጥነታቸውን፣ ለአገራችንም አንድነት ብዙ ሥርዓቶችን በማከናወን ለአለንበት ዘመን ተቀዳሚ ሆነው የሠሩትን ታሪኮች በመገንዘብ፣ በውጭ አገር ያሉ ጸሐፊዎች የተውትን መጻሕፍት አንብበናል።

በአገራችንም ሰዎች ሲያያዝ የመጣውን ታሪክ ተመልክተን ይህን ሁሉ በማሰብ የዚህን ሐውልት መሠረት እናኖራለን"።

ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ለማቆም ያሰቡት የሐውልቱ ንድፍ እያለ፣በቅርቡም አንድ ወጣት ቀራፂ አርቲስት በራሱ ወጪ ሐውልቱን ልሥራ እያለ ሲወተውት፣ ታሪክ ተሻሚዎች እውነተኛነት የሚጎድለውን አንድ የሴቫስቶፖል መድፍ ቅርፅ ብቻ ማስቀመጡ እውን የጀግናውን ዐፄ ቴዎድሮስ ማንነት በማክበር ነውን? የብረት አለሎውስ የሳቸውን ማንነት ይገልጣልን? በዚህ ሂደት የተሳተፉት የሚሉን፤ "በገንዘብ እጥረት ምክንያት ለጊዜው ይህን አድርገናል ነው። "ታዲያ ምን አስቸኮላችሁ? በገዛ ፈቃዱና ገንዘቡ ሊሠራ ያሰበውን ሰው ለምን እንዳይሠራ አሳገዳችሁት? ብሎ መጠየቅ አግባብ ያለው ይመስለኛል።

ምስጋና ለእግዚአብሄር ይድረሰውና እነሆ በአማራ ክልል ኃላፊነት የዐፄ ቴዎድሮስን እና የልጃቸውን የልዑል ዓለማየሁ ሐውልት ለመሥራት ጎንደር ከተማ ውስጥ የመሠረት ድንጋይ ተቀምጧል። የዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያው ህትመት ሽያጭ ገቢ በሙሉ ለሐውልቱን ማሠሪያ እንዲውል ያበረከትኩ መሆኔን በመግለጥ፣ የዐፄ ቴዎድሮስን የሕይወት ታሪክ በዚህ አባባል እደመድማለሁ።

* ክቡር ፕሬዚደንት ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ (በ፲፱፻፺ ዓ.ም. የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር ዐቃቤ ነዋይ) ከነገሩኝ የተቀነጨበ



## ምዕራፍ ፱

### ልዑል ዓለማየሁ ቴዎድሮስ



ሐምሌ ፳፫ ቀን ፲፰፻፷ ዓ.ም.

እቴጌ ጥሩወርቅ ከዐፄ ቴዎድሮስ ጋር የተጋቡት ገና የ፲፪ ዓመት ኮረዳ ሆነው ነው። ዐፄ ቴዎድሮስ የሚስታቸውን አባት ደጃዝማች ውቤን፣ ሁለቱን ወንድሞቻቸውን ካሣ ውቤን እና ጓንጉል ውቤን አስረውባቸው ስለነበረ፣እቴጌ ጥሩ ወርቅ በጋብቻው ደስተኛ አልነበሩም። በዚህም የተነሳ ምኞታቸው ለመመንኮስ ስለ ነበረ ከባለቤታቸው ጋር በአብዛኛው አይግባቡም ነበር። ዐፄ ቴዎድሮስ በበኩላቸው በሞት የተለይዋቸው የቀድሞ ባለቤታቸው እቴጊ ተዋበች ይሰጧቸው የነበረውን ክብር እና ፍቅር ከአዲሷ ባለቤታቸው ከእቴጌ ጥሩ ወርቅ ባለማግኘታቸው ብዙ ጊዜ በትዳራቸው ይበሳጩ ነበር።

## ምዕራፍ ፪

# ልዑል ዓለማየሁ ቴዎድሮስ



ሐምሌ ፳፫ ቀን ፲፰፻፷ ዓ.ም.

መቼም "እግዚአብሄር ሳይደግስ አይጣላም" እንደሚባለው ሆነና እቴጌ ጥሩ ወርቅ ሚያዚያ ፳ ቀን ፲፰፻፶፫ አንድ ወንድ ልጅ በማፍራታቸው ዐፄ ቴዎድሮስ በጣም ተደስተው ለረጅም ጊዜ ጠመንጃና መድፍ አስተኮሱ። አምስት መቶ ያህል እስረኞችም በዕለቱ በምህረት እንዲለቀቁ አዘዙ። እቤታቸው ሲገቡ ከፍቅር እና እንክብካቤ ባለማግኘታቸው ይበሳጩ የነበሩት ዐፄ ቴዎድሮስ፣የሕፃኑን ስም ዓለማየሁ አሉት። በትርጓሜው "እስከ አሁን ተከፍቼ ነበር እና አሁን ግን ተደሰትኩ" ለማለት አስበው ያወጡት ስም ይመስላል። ልጃቸውን በጣም ይወዷቸውና ይሳሱላቸው ስለነበረ ወደቤት ሲገቡ በመጀመሪያ የሚሄዱት ዓለማየሁ ወዳለበት ቦታ ነበር። ሲገናኙ ልጃቸውን ይስሙና ጭንቅላቱን እና ሰውነቱን እያሻሹ ለጥቂት ደቂቃ እንዳቀፉት ይቆያሉ። ከዚያም ጉንጩን እየሳሙ ከራስ እስከ እግሩ ሰውነቱን ይዳስሱና ጠረኑን ያሸታሉ። ይህ ትግባር ቴዎድሮስ ከውጭ መጥተው ወደ ግቢያቸው ሲገቡ የሚፈጽሙት የሁልጊዜ አካሄድ ነበር። አልፎ አልፎ ብስጭት ሲገጥማቸው ከዓለማየሁ ጋር ሲጫወቱ ሁሉንም ነገር እርግፍ አድርገው ይተዉ ነበር ይባላል። በአንድ ወቅት ወዳጆቻቸውን ሰብስበው "በዓለም ላይ ካለው ነገር ሁሉ እስቲ ሽታው እጅግ ደስ የሚልና ልብ የሚመስጥ ምንድን ነው?" ብለው ጠየቁ። መኳንንቱ ሁሉ ልዩ ልዩ ጠረን ያላቸውን የአበቦችና የሽቶዎች ስም እየጠሩ እንዳፈቀታቸው ተናገሩ። እሳቸው ግን የሰሙትን መልስ ሁሉ ወደ ጎን ትተው "ከሁሉም ነገር የሚመስጠው የሕፃን ልጅ ጠረን ነው" አሉ ይባላል*። ለዓለማየሁ የነበራቸው ፍቅር እስከዚህ ድረስ የጠለቀ ነበር።

የልዑል ዓለማየሁ የግል አልባሻቸው ገብረ መድህን፣ልብሶችንና ጌጣጌጦችን እየመረጠ አዘጋጅቶ ያለብሳቸው ነበር። ስለዚህ ልዑል ዓለማየሁ ሁልጊዜ ጥሩ ልብስ ለብሰው የደስ ደስ ያላቸው እና ሳቂታ ልጅ ሆነው ይታዩ ነበር። ዐፄ ቴዎድሮስ በዚህም ደስተኛ ስለ ነበሩ ወደ ሌላ ቦታ ካልሄዱ ወይም የመንግሥት ጉዳይ ካልያዙ በስተቀር በትርፍ ጊዜያቸው ከዓለማየሁ ጎን አይለዩም ነበር። እዚህ ላይ፣ዐፄ ቴዎድሮስ ለልጃቸው ልዑል ዓለማየሁ ይህን የመሰለ ለየት ያለ ከፍተኛ ፍቅር ያደረባቸው ለምን ይሆን ብሎ ለሚጠይቅ መልሱ እንደሚከተለው ነው።



አንደኛ በጣም ከሚወዷቸውና ከሚያስቡላቸው ባለቤታቸው ከእቴጌ ተዋበች ልጅ ባለማፍራታቸው በእጅጉ ያዝኑ እና ይቆጩ የነበሩ መሆናቸው ነው። ሁለተኛ ምክንያት ከወይዘሮ ገሰሰች እንግዳ ተጋብተው መሸሻ እና አልጣሽ የሚባሉት ሁለቱ ልጆች ከተወለዱ በኋላ፣ካሣ በተለያዩ የጦር አውድማዎች በመዋላቸው ከልጆቻቸው ጋር የሚገናኙበት ጊዜ ውስን መሆኑ ነው። ከዚያም አልፎ፣ቀደም ሲል እንደተገለጠው፣በእቴጌ መነን ግፊት ወይዘሮ ገሰሰችን ፈትተው እቴጌ ጥሩ ወርቅን ማግባታቸው ከልጆቻቸው ጋር ስለ አራራቃቸው ነው። ይህ ከልጆቻቸው ጋር መራራቅ የተከሰተው፤ከጋብቻ ውጭ ከተወለዱት ኃይሉ እና ይማም ቴዎድሮስም ጭምር ነው። እግረ መንገዳችንን፣ ወይዘሮ አልጣሽን በዚያን ዘመን የቴዎድሮስ ምርኮኛ ለነበሩት ለደጃዝማች ምኒልክ (በኋላ ዐፄ ምኒልክ) ድረውላቸው ነበር።

ሕፃኑ ልዑል አራት ዓመት ሲሞላቸው፣በአገሩ ወግ መሠረት፣አለቃ ገብረዓት የሚባሉ ቄስ በአስተማሪነት ቀጠሩላቸው። እኚህ መምህር ዓለማየሁን እዚያው አባታቸው ግቢ ውስጥ ማስተማር ጀመሩ። ልዑል ዓለማየሁ ፊደል ቆጥረው፣አቡጊዳን ዘልቀው ዳዊት መድገም ሲጀምሩ፣እንግሊዞች በዐፄ ቴዎድሮስ የታሰሩትን ፈረንጆች ለማስፈታት ድንበር ተሻግረው ወደ መቅደላ ዘመቱ። ጦርነቱ ሲጀመር እናታቸው እቴጌ ጥሩ ወርቅ እና ልዑል ዓለማየሁ መቅደላ አፋፍ ላይ ነበሩ። ጦርነቱ እየበረታ እና እየተፋፋመ ሲሄድ፣እቴጌ ጥሩ ወርቅና ልዑል ዓለማየሁ ተጠርተው ከዐፄ ቴዎድሮስ ጋር ሲጨዋወቱ ቆዩ። በዚህ ዓይነት የመሰነባበቻ ውሎ ባደረጉ በሁለተኛው ቀን ሚያዚያ ፮ ቀን ፲፰፻፷ ዓ.ም. "አባ ታጠቅ ካሣ፣ የቋራው አንበሳ" ጀግናው ዐፄ ቴዎድሮስ በገዛ ሽጉጣቸው ራሳቸውን ዐጠፉ። ጀነራል ናፔር እንደተመኘው አባ ታጠቅ ካሣን (ቴዎድሮስን) መያዝ ባይችልም እቴጌ ጥሩ ወርቅን እና ገና ስምንት ዓመት ያልሞላቸውን ልዑል ዓለማየሁን ወታደሮቹ በአንድ ቤት ውስጥ ሲያገኟቸው ተደሰተ።

ከዚያም ከቤት አስወጥቶ ከሜዳ ላይ አስቀመጣቸው እያለ አንድ ትንሽ ልጅ ሲያለቅስ ሰሙ። ወታደሮቹ ድምፅ ወደሰሙበት አቅጣጫ ሲሄዱ፣ሦስት ዓመት እንኳን ያልሞላው ሌላ ሕፃን ልጅ ከግድግዳ ጥግ ቁሞ ሲያለቅስ አዩ። የሕፃኑ ማንነት ባይታወቅም፣እቴጌ ጥሩ ወርቅና ልዑል ዓለማየሁ ወደ ነበሩበት ቦታ ወሰዱት። (ሲያለቅስ የነበረው ሕፃን በኋላ ወርቅነህ እሸቱ መሆኑ ታውቋል)።

ተጨማሪ አሰሳ ሲደረግ፣የዓለማየሁ መምህር አለቃ ገብረዓትና አልባሽ ገብረ መድኅን እዚያው አካባቢ ስለተገኙ ከቤት ወጥተው ከእቴጌ ጥሩ ወርቅ ጎን እንዲቆሙ ተደረገ። በዚህ ግርግር መካከል፣የእንግሊዝ ወታደሮች የቴዎድሮስን ልብስ በጫጭቀው ለመታሰቢያነት ወሰዱ። ቀጥሎም ግቢው ውስጥ የነበረውን በርካታ ንብረት ዘርፈው፣ ቤቶችን አቃጥለው እና የንጉሡን ቤተሰቦችና ሌሎችንም በስፍራው የተገኙትን ሰዎች ወደ አገራቸው ለመውሰድ የመጡበትን መንገድ ይዘው ወደ ባህር ጠረፍ አመሩ። ከመቅደላ እስከ ትግራይ ግዛት እንደ ተጓዙ እቴጌ ጥሩ ወርቅ በጠና ታመሙ። እሳቸው በሞት አፋፍ ላይ እያሉ፣ ካፒቴን ስፒዲን አስጠርተው እጁን ያዙ እና "ልጄ አባት የለውም። እኔም እናቱ መሞቴ ነውና አንተ አባት ሁነው። ስለዚህ ይህን ያልኩህን ሁሉ እንደምትፈፅም በእግዚአብሄር ስም ማልልኝ" አሉት። ስፒዲ በኋላ እንደጻፈው "ከሞት አፋፍ ላይ ለነበሩት ለእቴጌ ጥሩ ወርቅ "የጠየቁኝን ለዓለማየሁ እፈጽማለሁ ብዬ ማልኩላቸው" ብሏል። በዚያን ጊዜ የሦስት ዓመት ዕድሜ የነበራቸው ሕፃን ልጅ፣ከልዑል ዓለማየሁ ጋር መቅደላ ላይ ተይዘው ወደ ሕንድ አገር ስለተወሰዱ፣እዚያ አድገው፣በሕክምና ሙያ ከተመረቁ በኋላ በሥራ ዓለም ላይ እያሉ ባልታተመ የሕይወት ታሪካቸው መጽሐፍ ውስጥ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ጽፈዋል።

> ጀነራል ናፒር የስቅለት ዕለት ፲፰፻፷ ዓ.ም. ወደ መቅደላ ምሽግ ሲዘልቅ፣አካባቢው ጭር ብሎ እና ፀጥ ቴዎድሮስ ሙተው አየ። ከእቴጌ ጥሩ ወርቅ እና ከልዑል ዓለማየሁ ጋር እኔን ትንሹን ልጅ ማርኮ ከአፋፉ ይዞን ወደ ጦሩ ሰፈር ወረደ። ከዚያም ጉዞ ተደርጎ ጦሩ በሙሉ ወደ ባህር ወደብ እንደ ደረሰ እቴጌ ጥሩ ወርቅንና ዓለማየሁን (ልዑል) ወደ እንግሊዝ አገር ይዞ በመሄድ ላይ እንዳለ፣እቴጌ በጉዞው ላይ ስለ ዐረፉ ባህር ውስጥ ተቀበሩ።

ስለ እቴጌ ጥሩ ወርቅ ዕረፍትና ቀብር፣ጳውሎስ ኞኞ አጤ ቴዎድሮስ በሚለው መጽሐፉ ውስጥ የሚከተለውን ጽፏል።

> እቴጌ ጥሩ ወርቅ ውቤ፣ልጃቸውን ዓለማየሁን ተከትለው ከእንግሊዞች ጦር ጋር ጉዟቸውን ቀጠሉ። መቅደላን ከለቀቁ ጀምሮ ጤነኛ አልነበሩም። ህንጣሎ አጠገብ ሐይቅ ሐላጥ ከሚባል ስፍራ ሲደርሱ፣መከረኛዪቱ እቴጌ ጥሩ ወርቅ ሞቱ። ሬሳቸውም ጨለቆት ባለው ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ከታላቁ ከራስ ወልደ ሥላሴ መቃብር አጠገብ ተቀበሩ።



ስለ እቴጌ ጥሩ ወርቅ አሟሟት እና ቀብር፣ከዚህ በላይ በተጻፉት ሁለት ዓይነት ትረካ በብዙ መጽሐፎች ውስጥ ተጽፏል። ለማንኛውም ሰኔ ፱ ቀን ፲፰፻፷ ዓ.ም. ወጣቱ ልዑል ዓለማየሁ፣ የሦስት ዓመቱ ሕፃን፣ ካፒቴን ስፒዲ፣አለቃ ገብረዓት፣ አልባሽ ገብረ መድኅን፣ ዘማቾቹ የእንግሊዝ ጦር አባላት እና ከእስር ቤት የተፈቱት ፈረንጆች በሙሉ ከነቤተሰቦቻቸው ከቀይ ባህር ወደብ ደርሰው ፌሬዝ በምትባል መርከብ ላይ መሳፈራቸው ግን እርግጥ ነው*። ልዑል ዓለማየሁ እና ስፒዲ በመርከቧ ውስጥ ለብቻቸው አንድ ክፍል ተሰጣቸው። የልዑል ዓለማየሁ መምህር እና አልባሻቸውም አብረው ነበሩ።

ስፒዲ የአማርኛ ቋንቋ ያውቅ ስለ ነበረ ከልዑሉ ጋር ከፍተኛ መግባባት ነበረው። በጉዞው ወቅት በመርከቡ ላይ አብረው በመዝናናት ጥሩ ጊዜ ያሳልፉ እንደ ነበረ ገልጦ ሰኔ ፳ ቀን ስለደረሰው ሁኔታ እንዲህ ብሎ ጽፏል። "በአራት ሰዓት ገደማ የእኔን እርዳታ የሚፈልግ የድረሱልኝ ጩኸት በአማርኛ ሰማሁ። አጯጯሁ እና ድምፁ አማርኛ ስለሆነብኝ ዓለማየሁ ይሆናል ብዬ ደነገጥሁ። ዓለማየሁ ከእኔ ተለይቶ መርከቧ ሜዳ ላይ ይጫወት ነበር። ወደ ልጁ እየሮጥሁ ስሄድ ከናፒር የተላከ መልዕክተኛ ወደ እኔ እየሮጠ ሲመጣ አጋጠመኝ እና "ቶሎ ና ትባላለህ" አለኝ። እኔ ስደርስ ዓለማየሁን ናፒር ታቅፎታል። ወጣቱ ልዑል ይወራጫል። እናት እና አባቱ የሞቱበትን ያን ሕፃን ከአዛዦችን ከጀነራል ናፒር እጅ ስቀበል፣ አለቃ ገብረዓት "ልጁ የሚጮኸው ቡዳ በልቶት ነው" አሉን።

ልዑል ዓለማየሁን ከጀነራል ናፒር ተቀብሎ ስፒዲ ሲያቅፋቸው ወዲያውኑ መጮህ አቁመው ከብብቱ ስር ሽጉጥ አሉ። ልዑሉ ወጣት፣እንዲህ የጮኹበት ምክንያት ግልጽ አልነበረም። ችግሩ የተከሰተው ኢትዮጵያዊ አስተማሪያቸው የሚያስፈራራ ነገር ነግረዋቸው ይሆናል ብለው ያሰቡ ሰዎችም አልጠፉም። ጥርጣሬውን ያጠናከረው፣ዓለማየሁ መምህራቸውን እና ሞግዚታቸውን ሲያዩ ምርር ብለው ማልቀሳቸው ነበር። ሌላው ምክንያት ደግሞ ልዑል ዓለማየሁ ከዚያን ቀን በኋላ መምህራቸውን ለማየት ፈጽሞ ፈቃደኛ ሳይሆኑ መቅረታቸው ነው።



ስፒዲ ልዑሉን እንደታቀፈ ከአልባሻቸው ጋር። "እንቅልፍ እስኪወስደው ድረስም ራሱን ከክንዴ ላይ አላነሳም " ስፒዲ

ከዚያ ቀጥሎ የሆነውን ስፒዲ ሲገልጥ "ናፒር ጠራኝ እና በልጁ ላይ ያለውን ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ አንተ ያዝ። ከሀበሾቹ ይልቅ ልጁ አንተን ወዶሃል። ሀበሾቹን ሲያይ የሚያወራጨውና የሚያበሳጨው ነገር ስላለ፣ እነሱ ስዌዝ ስንደርስ ወደ አገራቸው ይመለሳሉ" አለኝ። በዚህም ምክንያት መርከቡ ስዌዝ ሲደርስ፣የልዑሉ መምህርና እንዲሁም አልባሻቸው ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ ተወሰነ። ይሁን እንጂ ወደ አዱሊስ የሚሄድ መርከብ እስኪገኝ ድረስ፣ ሁለቱ ሰዎች ማዳጋስካር ብዙ ወራት እንዲቆዩ ተደርጎ በመጨረሻ ወደ አገራቸው መመለሳቸው ይነገራል።



ሩት ሰዎች በመርከብ በተጓዙባቸው ወራት ሁሉ ልዑል ዓለማየሁ የስፒዲ ንድ እየተንተራሱ ይተኙ ነበር። አሁንም ስፒዲ ስለ ሁኔታው ሲገልጽ "ዓለማየሁ ኔ በስተቀር ከሌላ ሰው ጋር አልለምድ አለ። እኔንም ቢሆን አስቸገረኝ። ሲተኛ ኳን ክንዴን ካላንቆራስኩት እና እብብቴ ውስጥ ሽጉጥ ካላለ እንቅልፍ ወስደውም። የሀበሻ ሞግዚቶቹ ስለ አባቱ እና ስለ እናቱ አሟሟት የነገሩት ሚያስፈራራ ነገር ከአእምሮው አልወጣ አለ። ተኝቶ ይባንንና ይነቃል። ምን ሆንክ ው፣ፈራሁ ይለኛል። ሽጉጥ አድርጌ እብብቴ ስር እይዘውና አይዞህ አትፍራ፣ተኛ ው ምስኪኑ ልጅ መልሶ እንቅልፍ ያሸልበዋል። እንቅልፍ ድብን አድርጎ ኪወስደው ድረስም ራሱን ከክንዴ ላይ አያነሳም ነበር" ብሏል።

ዑል ዓለማየሁ ቀን፣ቀን ከስፒዲ ጋር አብረው ይውሉ ስለ ነበረ ከሰቀቀን ቀቀው ጤናማ ልጅ ሆኑ። አልፎ አልፎ ከእንቅልፋቸው ባንነው ከነቁ፣እንገደና ቅልፍ እስኪወስዳቸው ድረስ እንዲጠብቃቸው ስፒዲን ይለምኑት ነበር።

ርከቡ ጉዞውን አገባድዶ እንግሊዝ አገር ሲደርስ፣ልዑል ዓለማየሁን ይዘው ጀነራል ር እና ካፒቴን ስፒዲ ወደ ቤተ መንግሥት ወስደው ከንግሥት ቪክቶሪያ ጋር ተዋወቋቸው። ንግሥቲቱም ከወጣቱ ልዑል ጋር እንደተገናኙ በጣም ደ ፏቸው። ስለዚህ ለወጣቱ ልዑል እንክብካቤ እንዲደረግላቸው አዝዘው ልዩ ልዩ ታ አበረከቱላቸው። ከንግሥቲቱ ጋር የተደረገው ትውውቅ እንዳለቀ ከቤተ ንግሥቱ ወጥተው ኋይት ደሴት ከሚባል ቦታ ወደሚገኘው የካፒቴን ስፒዲ ቤት ። ከዚያም ልዑል ዓለማየሁ እና ስፒዲ አብረው መኖር ጀመሩ። የእንግሊዝኛ ቋ ትምህርት ስፒዲ አስጀመራቸው። በአባትና እናታቸውን ሞት ነጥቋቸው ጅ አልባ የሆኑት ልዑል ዓለማየሁ፣ኀዘንና ፀፀታቸውን ረስተው ዘና ብለው ሳቅና መጫወት ጀመሩ። ሕፃን ልዑል ዓለማየሁ የባህር ነፋስ ስለሚያስደስታቸው ባህር ውስጥ መታጠብ ስላዘወተሩ ጤናቸው ተሻሽሎ የጨው ውሀ ጥላቻቸው ቀው። ስፒዲ ስለ ልዑሉ ወቅታዊ ሁኔታ ሲጽፍ "የአካል አቋማቸውም ጥሩ እ የተስተካከለ ውበት ያለው ሲሆን በፊት የነበረው አፋራምነት ወደ ልዝብ አስተያየ ተለውጦ ተናፋቂ ሁኗል።



ስፒዲ ልዑሉን እንደታቀፈ ከአልባሻቸው ጋር።
"እንቅልፍ እስኪወስደው ድረስም ራሱን ከክንዴ ላይ አላነሳም"
ስፒዲ.

በዚህ ዕድሜው ያለው የተፈጥሮ ዕውቀት ሰብአዊ ኀሊናን ይማርካል፣ይህንኑም ባሳየው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥናት ሊያስመሰክር ችሏል" ብሏል።

ንግሥት ቪክቶሪያ የዓለማየሁን ሁኔታ ይከታተሉ ስለነበረ ስፒዲ በየጊዜው ወደ ቤተ መንግሥት ወስዶ ከንግሥቲቷ ጋር ያገናኛቸው ነበር። ስለ ሕፃኑ ልዑል ዓለማየሁ ሐምሌ ፳፫ ቀን ንግሥት ቪክቶሪያ ሲጽፉ "የሀበሻው ንጉሥ የቴዎድሮስ ልጅ፣አሳዛኙ ዓለማየሁ የሀበሻ ልብሱን ለብሶና የአገሩን ጌጥ አድርጎ ከስፒዲ ጋር መጥቶ ነበር" ብለዋል። ስፒዲ ሲጽፍ "ለተወዳጁ ልዑል ሕፃን ዓለማየሁ የኪስ ሰዓት እና የጌጥ ሰንሰለት ሰጡት" ብሏል።

በአንድ ወቅት ደግሞ "ዓለማየሁ ጨዋና ውብ ልጅ ነው። የሰጠሁትን ኬኮች ደስ እያለው እየተቀበለኝ በላ። ዓለማየሁ ኬክ መብላት ይወዳል" ብለው ንግሥት ቪክቶሪያ ማስታወሻ ደብተራቸው ውስጥ ጽፈዋል። ልዑል ዓለማየሁ በክብርና በጥሩ እንክብካቤ እንዲያድጉ ለዚህ እናት ለሌለው ሕፃን እናቱ እኔ ነኝን የሚሉት ንግሥት ቪክቶሪያ ዓለማየሁ ጥሩ አስተዳደግ እንዲኖረው ስለፈለጉ፣አማርኛ የሚያውቀው ካፒቴን ስፒዲ በቂ ዝግጅት ተሰጥቶት ሞግዚት እንዲሆናቸው አዘዙ። በዚህ ትዕዛዝ መሠረት የእንግሊዝ መንግሥት የገንዘብ ምኒስቴር ለካፒቴን ስፒዲ በዓመት ሦስት (፫፻) መቶ፣ለሞግዚትነታቸው እና ለልዩ ልዩ ወጪ ደግሞ አራት መቶ (፬፻)፣በድምሩ ሰባት መቶ (፯፻) ፓውንድ እንዲሰጠው ወሰነ። በዚህም ስፒዲ ለሚቀጥለው ሁለት ዓመታት ልዑል ዓለማየሁን እንዲያሳድግ ተፈቀደለት። በተጨማሪ ያለበት ኃላፊነት፣የልዑሉን ሁኔታ በየጊዜው እንዲያቀርብ ነው። በ፲፰፻፷፩ ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ካፒቴን ስፒዲ ዑደህ በምትገኘው ሱታፑር ለምትባል ቀበሌ የፖሊስ ኮሚሽነር ሆኖ ተሾመ። ካፒቴን ስፒዲ በዚህን ጊዜ ትዳር አልመሠረተም ነበር። ስለዚህ ወደ ሹመት አገሩ ከመሄዱ በፊት ሚስት ማግባት አስፈለገው። ለሚስትነት ያጨው ወይዘሮ ኮርኔሊያ ኮተም የምትባል ጨዋ እመቤት ስለበረች ወዲያውኑ የጋብቻ ሥርዓት ፈፀሙ።

ሰኔ ፳፯ ቀን ባለቤቱን ወይዘሮ ኮተምን እና ልዑል ዓለማየሁን ይዞ ስፒዲ ወደተመደበበት የሥራ ቦታ ሄዱ። ልዑል ዓለማየሁ ሕንድ አገር በነበሩበት ጊዜ ስፒዲ ያቀረበው የመጀመሪያ ሪፖርት "ዓለማየሁ ደስ የሚል አንደበት ያለው ልጅ ሆኗል። ከትምህርቱ ሌላ የውጭ ስፖርት መሥራት ስለሚወድ፣የፈረስ ግልቢያ፣የእግር ኳስ ጨዋታና የውሀ ዋና ችሎታ አዳብሯል።



በተጨማሪም የአእምሮና የሥራ ቅልጥፍና ከጥሩ ሥነ ምግባር ጋር ያዋሃደ ልጅ ሆኗል። አንዳንድ ጊዜ የአእምሮ ሕመሙ ይነሳበታል። ዓለማየሁ ለሚጠይቀኝ ሁሉ ሳልደብቅ እውነተኛውን ነገር እነግረዋለሁ" ብሏል። በዚህን ጊዜ ነበር "አሁን በመማር ላይ ያለውን ትምህርት ትቶ በምትኩ ከኤውሮፓውያን ኦፊሰሮች ጋር የፈረሰኛነት ትምህርት ቢማር ይሻላል" የሚል ሃሳብ በግምጃ ቤቱ ኃላፊ የተወጠነጠነው። ካፒቴን ስፒዲ በበኩሉ "ዓለማየሁ በቀጣዩ ሚያዚያ ወር ፲ ዓመት ይሞላዋል። በስፖርት ጨዋታ የሚያሳየው ቅልጥፍና፣ ጉብዝናው እና ፍርሃትን ለመቋቋም ያለው ድፍረት በገሃድ ይታያል። በቀለም ትምህርት እምብዛም ጉጉ አይደለም። ግን በትምህርት ቤቱ ውስጥ ካሉት ጓደኞቹ ሁሉ ብሌላ ተግባሩ እጅግ የተመሰገነ ወጣት እርሱ ነው" በማለት ጽፏል። ስፒዲ በመቀጠልም ጽፎ በተወው በሌላ ሰነድ ውስጥ ተጽፎ የተገኘው መረጃ ደግሞ እንዲህ ይላል።

> የዚህ ሕፃን ፍቅር እንደ ሐረግ በልባችን ውስጥ ተወሳስቧል። የእኔና የእሱ መገናኘት በእግዚአብሔር ፈቃድ የተወሰነ ይመስላል። እኔ ሕንድ አገር አመቺ ትምህርት ቤት ስለ አሳገኘሁለት ሁኔታው ለዓለማየሁ ጥሩ አልነበረም። ተማሪ ቤት ከገባ በኋላ እርሱ ያለበት ቦታ ራቅ ያለ ስለሆነ ወደ ትምህርት ቤቱ የሄድኩ ዕለት እሱ እዚያ አልነበረም።

ስፒዲ ከዚህ ከፍ ብሎ የሰጠውን መረጃ ምክንያት በማድረግ፣ዐለቆቹ እና የእንግሊዝ መንግሥት ባለ ሥልጣኖች ልዑል ዓለማየሁ ወደ እንግሊዝ አገር መመለስ አለበት ብለው ወሰኑ። ይህ ብቻ ሳይሆን ትምህርት ቤቱ ከኢንግላንድ ወጣ ያለ መሆን የለበትም የሚል አቋምም ያዙ። በዚህም ላይ ስፒዲ እና ሚስቱ በ፲፰፻፷፩ ዓ.ም. በፈረሙት ስምምነት መሠረት የልዑል ዓለማየሁ ሞግዚትነታቸው የሚያበቃበት ጊዜ ተቃርቦ ነበር። ስፒዲ እና ባለቤቱ ግን፣ ከልጁ ጋር ሊለዩ ከፍተኛ ኀዘንና ሰቀቀን እንደሚደርስባቸው አልሸሸጉም። ይህንኑ የሚገልጥ ደብዳቤ በወይዘሮ ኮተም ተጽፎ ለንግሥቲቱ ባለሟል፣ ለሰር ጆን ካሚል ተላከ። የደብዳቤው ዓላማ ውሳኔው ይለወጣል በሚል ተስፋ ሳይሆን፣ ልዑል ዓለማየሁ ከእነርሱ ተነጥለው ከሌላ ሰው ጋር እንዲኖሩ ቢደረግ ኀዘንና ትካዜ የሚሰማቸው መሆኑን ጭምር ለመግለጥ ነበር።

በመቀጠልም ወይዘሮ ኮተም ለዓለማየሁ የግል መምህር አፈላልገው ከኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ በቅርቡ ዲግሪውን የተቀበለ ዶክተር ይግቦይ የሚባል ሰው አገኙ። ካፒቴን ስፒዲ ይህን ሐሳብ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሠራተኛ ለሆኑት ለሊንገን ሲጽፉ፡ "ለዓለማየሁ የግል መምህር ስለተገኘ ከእርሱ የዕድሜ እኩያ የሆኑ ተማሪዎች አብረውት እንዲኖሩ የማድረግ ዕቅድ አለን" በማለት አሳወቁ። ከዚህም ጋር በመያያዝ ስፒዲ ወደ እንግሊዝ አገር እንዲመለስ ቢፈቀድለት እና ሌላ ሥራ ቢሰጠው፣የዓለማየሁን ሞግዚትነት በመቀጠል የበለጠ አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን አብራርቶ ጻፈ።

በአንፃሩ የገንዘብ ሚኒስትሩ ቻንስለር፣ ስፒዲና ወይዘሮ ኮተም የሚሉትን በማጣጣል እንዲህ አለ። "በሕንድ ውስጥ ወላጆች ልጆቻቸውን በፈቃዳቸው እንደሚያሳድጉ ሁሉ ዓለማየሁ በወታደር ምሽግ ቢያድግ ብቻኛ ስለሚሆን ምናልባት በተሸሸገ ቦታ እንዳደጉ ሕፃናት አንጎሉ የማይዳብርና አእምሮው የላሸቀ ይሆናል። ይህ ልጅ ለብዙ ጊዜ ሕንድ አገር ብቻውን እንደተተወ አምናለሁ። ስለዚህ እዚያ አገር መቆየቱ ጥቅሙ አይታየኝም። ካፒቴን ስፒዲና ባለቤቱ ለሚሉት ሁሉ ቁምነገር አልሰጠውም። ምክንያቱም እነሱ ለሚያበረክቱት አገልግሎት ከሚገባ በላይ ጥቅም ስለሚያገኙ፣ እንዲህ የሚወተውቱት ለጥቅም ብለው ነው። እኔ ከቸልተንሃም ኮሌጅ የበላይ ተጠባባቂ ከሚስተር ጃክስ ብሌክ ጋር ተነጋግሬ ባዘጋጀሁት መሠረት ወደ እነሱ ዘንድ እንዲሄድ እኔ ተስማምቻለሁ። ሚስተር ጃክስ ብሌክ ብዙ ቤተሰብ ስለ አላቸው ልጁ ብቸኝነት አይሰማውም። ምናልባት አጋጣሚ ሆኖ ልጁ አንድ ቀን የሀበሻ አገር ኑሮ ተካፋይ ይሆናል እና አነስተኛ የመሻሻል ዕድል አግኝቶ የአውሮፓን የኑሮ ይዞታ ሳናላትፈው ብንቀር ይቅርታ የሚነፍገን እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል" በማለት ንግግሩን ደመደመ።

ንግሥት ቪክቶሪያ ዓለማየሁ ከስፒዲ ቤተሰብ እንዲነጠል የተመከረውን በሰሙ ጊዜ በጠቅላላው ይዘት አልተስማሙም ነበር። በኋላ ላይ ግን ሁለት ነገር መጨመር አለባችሁ በማለት ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል ተናገሩ።

አንደኛ፡- ልጁ ከለመዳቸው አሳዳጊዎቹ በሚነጠልበት ጊዜ ጠባዩ እንዳይለወጥ፣የሕክምና ጠበብት እንዲከታተሉ

ሁለተኛ፡- ከሚመረጡት ሐኪሞች አንዱ ሰር ደብሊው ጂኒር እንዲሆን



ከዚህ ትእዛዝ በኋላ ካፒቴን ስፒዲ ልዑል ዓለማየሁን ከሕንድ አገር አጅቦ ነሐሴ ፴ ቀን ሳውዝ ሃምፕተን ከሚባለው ወደብ ደረሰ። ያን ዕለት ባለቤቱን ለማግኘት፣ ፍሬሽ ወተር ወደሚገኘው ቤቱ ከልዑል ዓለማየሁ ጋር ሄዱ። ቀደም ሲል የገንዘብ ሚኒስትሩ እንደተናገረው፣የተከበሩ ጃክስ ብሌክ በራሳቸው ስም የሚጠራ የግል ኮሌጅ ቸልተንሃም በሚባል ቦታ ነበራቸው። እሳቸው ተማሪ ቤት ልዑል ዓለማየሁን በአዳሪነት ይቀበሉት እንደሆነ ተጠይቀው ፈቃደኛነታቸውን ቀደም ሲል ገልጠዋል። ሆኖም ልዑል ዓለማየሁ ለጃክስ ብሌክ እንዲሰጡ የተጻፈው መመሪያ ለስፒዲ አልደረሰውም ነበር። ስፒዲና ልዑሉ እንደ አባትና ልጅ ሆነው ብዙ ጥሩ ደስታ የተሞላበት ጊዜ አሳልፈዋል። ልዑል ዓለማየሁም ብቸኝነት ሳይሰማቸው፣ስፒዲን እንደ አባት አድርገው በመቁጠር አብረው ኖረዋል። በዚህ ምክንያት ስፒዲ ስለ እሳቸው ትምህርት ጉዳይ ያለውን ሐሳብና የጉዳዩን ሁናቴ ገልጦ የሚከተለውን መራር ደብዳቤ ጻፈ።

> ኀዘኔንና ድንጋጤዬን ከመግለጽ የሚገታኝና የማያግደኝ አንዳችም ነገር አልተፈጠረም። ይህም የምወደውን አበባውን የሕይወት ጓደኛዬን ዓለማየሁን ከማጣቴ የተነሳ በመንፈሴ ውስጥ ትካዜ ተመላለሰ። ለልጁም ደግ አሳዳጊዎች ነበርን እንጂ በክፋት አላሳቀቅነውም ነበር። በወቅቱም ስለ ኑሮ ይዞታው ሳይገለጽልኝ በመቅረቱ፣የማስብለት ሁሉ ከንቱ በመቅረቱ ነው። ስለ አእምሮውም ሆነ ስለ ሰብአዊ ኑሮው ከእነብሌክ የሚያገኘውና የሚጠባበቀውም ነገር የለም። በአሁኑ የአእምሮ ይዞታው ዓለማየሁ ለከፍተኛ ትምህርት ቤት ብቁ አይደለም።



ልዑል ዓለማየሁ ከስፒዲ ቤት መኖር ሲጀምሩ የተነሱት

ከሕፃንነቱ እስከ አሁን ከአገሩ ከኢትዮጵያ እስከ እንግሊዝ አገር ከዚያም እስከ ሕንድ አገር ድረስ ሆን ብዬ ያጠናሁትን መግለጥ የእኔ የመንፈስ አባቱ ፈንታ ስለሆነ በዚች ደብዳቤ ላይ ሳላሰፍረው አላልፍም። የመጨረሻው ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በቃል እንድንነጋገር በትህትና እጠይቃለሁ።



ይህ በታላላቅ ሰዎች መካከል የተፈጠረው የአስተሳሰብ መጋጨት የወጣቱን ልዑል ዓለማየሁ ኑሮ አባባ። ክርክሩ የመንግሥት ሹሞችን እና ስፒዲን ብቻ የሚመለከት አልሆነም። ጉዳዩ ወደ እንግሊዝ ምክር ቤት ደርሶ የካቲት ፳፱ ቀን የልዑል ዓለማየሁ ጉዳይ ተነሳ። የምክር ቤቱ አባል የሆኑት ስታፎርድ ኖርዝኮት ልዑል ዓለማየሁ ከካፒቴን ስፒዲ ለምን እንዲለይ እንደተፈለገ ጠየቁ። በዚህ ጉዳይ ሎዊ የሚባሉ ባለሥልጣን ሲመልሱ "ልጁ አሁን ፲፩ ዓመቱ ነው። በዚህ ዕድሜው መሠረታዊ ዕውቀት እንኳን አልቀሰመም። የመኳንንት ልጆች ትምህርት ቤት ገብቶ ከእኩዮቹ ጋር ሊማር የቻለ አይመስለኝም። መጻፍና ማንበብ መቻሉን እጠራጠራለሁ" አሉ።

ከዚህ የፓርላማ ጥያቄና መልስ በኋላ ልዑል ዓለማየሁን ወደ ብሪንግቶን ወስዶ ለተከበሩ ብሌክ ጃክሰን ለማስረከብ የተሰጠውን ትዕዛዝ ስፒዲ አልተቀበለውም። ተመሳሳይ ትዕዛዝ በተደጋጋሚ ቢደርሰውም አሁንም ካፒቴን ስፒዲ አልበገር አለ።

በመጨረሻ ጥር ፲፪ ቀን "ልዑሉን ወደ ዊንድሰር ቤተ መንግሥት እንዲያመጡ ይፈለጋሉ" የሚል ቴሌግራም ደረሰው። ደብዳቤው የተጻፈለት ቀደም ሲል ስፒዲ በጠየቀው መሠረት ሲሆን ሁለቱን ሰዎች ለማወያየት፣ ወደ አልቤር ሆቴል እንዲሄድ ለመጠየቅ ምክንያት ነበር። ስፒዲ በቀጠሮው ቀን ሄዶ ከተነጋገረ በኋላ፣ ለልዑሉ የሚስማማ ቦታ ምክክር ተደርጎ እስኪመረጥ ድረስ፣ ከስፒዲ ጋር እንዲቆይ መወሰኑን ተቀበለ። ወዲያው ካፒቴን ስፒዲ ባለበት፣ ልዑል ዓለማየሁ የጤና ምርመራ ተደረገላቸው። ዶክተር ጄኔር የሰጠው ሪፖርት "ዓለማየሁ በሞቃት ቦታ ቢቆይ ይሻላል፣ ይህም ሲሆን በደቡባዊ ኢንግላንድ ምቾት ባለው ቤት ውስጥ ቢቀመጥ አየሩን ሊላመድ ይችላል" የሚል ሃሳብ አቀረበ።

ከፍ ብሎ በተገለጠው በዚህ ሪፖርት መሠረት ልዑል ዓለማየሁ ለጤናቸው ተስማሚ ሊሆን ይችላል በሚል ሰበብ አመቺ ነው ወደ ተባለ የሕዝብ ትምህርት ቤት እንዲላኩ የሚል ሃሳብ ቀረበ። ስፒዲ እና ዶክተር ኩየን ግን፣ ልዑልዓለማየሁ ወደ ሕዝብም ሆነ ወደ የግል አዳሪ ትምህርት ቤት መላካቸውን ተቃወሙ።



ልዑል ዓለማየሁ ከስፒዲ ቤት መኖር ሲጀምሩ የተነሱት

ከሕፃንነቱ እስከ አሁን ከአገሩ ከኢትዮጵያ እስከ እንግሊዝ አገር ከዚያም እስከ ሕንድ አገር ድረስ ሆን ብዬ ያጠናሁትን መግለጥ የእኔ የመንፈስ አባቱ ፈንታ ስለሆነ በዚች ደብዳቤ ላይ ሳላሰፍረው አላልፍም። የመጨረሻው ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በቃል እንድንነጋገር በትህትና እጠይቃለሁ።

እንደ አማራጭ "ከሁለትና ከሦስት ያልበለጡ ተማሪዎች ያሉበት የግል ትምህርት ቤት ተፈልጎለት ካፒቴን ስፒዲ እንደሞግዚት እየተቆጣጠረ እና የእረፍት ጊዜ እየተቀበለ ቢወስደው እጅግ በጣም የተሻለ ነው" በማለት ተብራርቶ ተጻፈ:: ይህንን ሃሳብ ንግሥቲቷ አጥብቀው ደገፉት:: ሮዶልፍ ግን በበኩሉ፣ የንግሥቲቱ አባባል ልዑል ዓለማየሁ ዶክተር ብሌክ ትምህርት ቤት መግባቱን የሚቃወም አስመስሉ ጻፈ::

ከዚህ መሰል ኸወኸው በኋላ ስፒዲ ለአንድ ዓመት እንግሊዝ አገር እንዲቆይ ተደርጎ፣ ልዑሉ ወደ ጃክስ ብሌክ ትምህርት ቤት ቺልተንሃም እንዲሄዱ ተስማሙ:: በዚህ ስምምነት መሠረት፣ ልዑል ዓለማየሁ በፈለጉ ጊዜ ከስፒዲ ጋር እንዲገናኙ እና ደብዳቤም በሚጸጻፉ ጊዜ፣ ሌላ ማንም ሰው ሳያነቡና ሳያየው እንዲላላኩ ፈቃድ ተሰጥቶ ልዑሉ የሚደሰቱ ሆኖ ከተገኘ ከጃክስ ብሌክ ጋር እንዲኖሩ ወሰኑ:: ጃክስ ብሌክ ቤት ከገቡ በኋላ ወጣቱ ልዑል ዓለማየሁ ደስተኛ አልሆኑም:: ለብስጭታቸው ምክንያት የሆነው፣ የጃክስ ብሌክ ልጆች ሴቶች ብቻ ስለሆኑና እነሱም የሚጫወቱት፣ የሚያወሩት እና እርስ በእርሳቸው የሚያደርጉት ሁሉ የሴታሴቶች ጨዋታ በመሆኑ ብቸኝነት ስለሚሰማቸው ነበር:: ይህንም ከዚህ ቀጥሎ ባለው አነጋገር ገልጠውታል::

"አብረውኝ የሚጫወቱ ልጆች እፈልጋለሁ:: ከማንም ሰው ጋር የምነጋገረው ቅዳሜ እና እሁድ ብቻ ነው:: እኔን ሊያጫውቱኝ የሚመጡት ሁለት ልጆች ብቻ ናቸው:: ሌላ ማንም የለም" እያሉ በየጊዜው ችግራቸውን ከማሳወቅ እና ከማሳሰብ አልተቆጠቡም ነበር:: የብቸኝነት ስሜት ዓለማየሁን ስለ አብሰለሰላቸው በሽተኛ ለመሆን በቁ:: በዚህ ምክንያት ደማቸው አልቆ፣ መጣጣና ቀጭን ሆኑ:: ጠባያቸው እና መንፈሳቸውም ተለወጠ::

ወይዘሮ ኩተም የልዑሉን የጤና እና አእምሮ መታወክ ሲሰሙ ወሬው ትክክል መሆኑን ለማጣራት ፈልገው፣ልዑል ዓለማየሁን ለማየት ቢጠይቁ፣ ሚስስ ጃክስ ብሌክ ጥያቄውን ሳይቀበሉ ቀሩ:: ልዑሉ ጓደኛ ስላልነበራቸውና በጣም የሚወዱትን ስፖርት ከዚህም አልፎ ከልጆች ጋር ለመጫወት ባለመቻላቸው የዝምተኛነት ጠባይ አመጡ:: ይህ ሁኔታ እስጊ መሆኑ እየታወቀ፣ ሚስስ ጃክስ ብሌክ ግን ልጁን በደህና ሁኔታ ይዘውት እንደሚገኙ ሲናገሩ ነበር:: በዚህ መሐል ጃክስ ብሌክ ፲፱፻፳፮ ዓ.ም የራግባ አስተዳዳሪ ሆኑ::



በዚህ ጊዜ በተደረገ ውይይት ልዑል ዓለማየሁ ወደራጉባ አብረው እንዲሄዱ ተወሰነ:: ሆኖም ከጃክስ ብሌክ ቤት ሳይገቡ ከሚስተር ሊዎርነር ቤት እንዲኖሩ ተደረገ:: በዚህ ትምህርት ቤት ሲማሩ ምንም ማሻሻል ሳያሳዩ በመቅረታቸው በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. በሚያዚያ ወር ወደ ብሮክስበርን አዳሪ ትምህርት ቤት እንዲገቡ ተደረገ:: ልዑል ዓለማየሁ በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ ከአሥር ተማሪዎች ጋር ሲማሩ በነበሩበት ጊዜ፣ጃክስ ብሌክ የሚከተለውን ሪፖርት ለቡድሉፍ አቀረቡ::

> ዓለማየሁ በትምህርት ጥናቱ የእኛን ፍላጎት ያህል ባይጣደፍም ንቁ እና ትጉህ ነው:: በሰብአዊ ይዞታው ደግ ነው:: እኔ እንደማስበው ከሆነ በሕይወት ውስጥ ካለው ኑሮ መስክ ሁሉ በተለይ ወታደርነት ሥራ ይስማማዋል ብዬ አምናለሁ:: በጨዋታዎች ሁሉ እጅግ በጣም ጥሩ ሲሆን ከተለይም በእግር ኳስ ጨዋታ እንደ እርሱ ያለ ልጅ የለም:: በጠባዩ ረገድም ሲቆጣ አይቼው አላውቅም::

ከዚያ በማያያዝ በሚቀጥለው ጊዜ ጃክስ ብሌክ ልዑል ዓለማየሁን ራንሳም ለሚባለው የግል መምህር ሰጡ:: እዚያ በነበሩበት ጊዜ ጃክስ ብሌክ አንድ አዲስ ወሬ ደረሰው:: ይህም፣ ልዑል ዓለማየሁ በመስከረም ወር ያለፈተና ወደ ሳንድኸርስት የጦር ትምህርት ቤት ሊገቡ ይችላሉ የሚል ነበር::

ወደ ሳንድኸርስት ትምህርት ቤት እንዲገቡ ከተፈቀደ በመጀመራቸው የዓለም ኤግዚቢሽንን ለማየት ከራንሳም ጋር ወደ ፓሪስ እንዲሄዱ ተወሰነ:: ፓሪስ ሄደው ኤግዚቢሽኑን ከማየት በተጨማሪ፣ የሉቭር ሙዚየምን፣ የኤሊሴ ቤተ መንግሥትን፣ የአይፈል ማማን (Eifel Towen) እና ሌሎችንም ታሪካዊ ቦታዎች ከጎበኙ በኋላ ወደ እንግሊዝ አገር ተመለሱ::

በመስከረም ወር ሳንድኸርስት በካዴትነት ገቡ። ሳንድኸርስት ብዙም ሳይቆዩ የካዴት ትምህርት ቤቱ ባለሥልጣኖች፣ እዚህ ተቋም  ውስጥ መቆየቱ ምንም ጥቅም የለውም ከሚል ድምዳሜ ደረሱ። ስለዚህ ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ቢገባ ይሻላል የሚል ሃሳብም አቀረቡ። በዚህ ወቅት እንደ አጋጣሚ ሆኖ እጅግ የሚወዱት እና ከፍተኛ እንክብካቤ ያደርግላቸው የነበረው ሻምበል ስፒዲ ወደ አገሩ ተመልሶ መጥቶ ነበር። ስለዚህ ዓለማየሁን ወደ ስኮትላንድ ለአንድ ወር ወስዶ በማንሸራሸር፣ የአእምሮ ጭንቀታቸው እንደሚቃለል ተስፋ ያላቸው መሆኑን እና ከዚያም ሕንድ ውስጥ በሚገኝ ተቀዳሚ ሬጂመንት ውስጥ ቢቀጠሩ እንደሚሻል ሎርድ ናፒር ሐሳብ አቀረቡ። በቀጣይም ይህ ሐሳብ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረና፣ ግሉሴስተር ሻየር ወደሚገኝ አንድ ትምህርት ቤት እንዲሄዱ ተደረገ።

ሁኔታው በዚህ ላይ እንዳለ በግንቦት ወር ፲፰፻፷፪ ዓ.ም. በአማርኛ የተጻፈ ደብዳቤ ለልዑል ዓለማየሁ መጣ። ደብዳቤውን የላኩት ወይዘሮ ላቂያዬ የሚባሉት የልዑል ዓለማየሁ ሴት አያት፣የእቴጌ ጥሩ ወርቅ እናት ናቸው። ከኢትዮጵያ የተላከላቸውን ደብዳቤው የሚያነብላቸው ሰው በመታጣቱ የደብዳቤውን ይዘት ሳያውቁ ብዙ ቀን አለፈ። ከወራት በኋላ ቴዎፍሎስ ዎልድሜየር የሚባሉ ሰው ተገኙ እና ደብዳቤዳው ወደ እንግሊዝኛ ተተረጎመ። ደብዳቤው የሚለውን እንዲህ ነው።

ይድረስ ለደጃዝማች ዓለማየሁ፡-

ከልጄ ከወዳጄ እጅጉን እንዴት አለህ? ከተለያየን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ምነው ወረቀት አትሰድልኝ? በኀዘን፣ በለቅሶ ከመሞት በስተቀር ሌላ ልጅ ሌላ ተስፋ የለኝም። አሁንም ቶሎ ወረቀት ስደድልኝ። መልክህን በሥዕል አድርገህ ዘወትር እንዳየው። ክርስቶስ ለመገናኘት ያብቃን፣ ከነገሥታቱ ሁሉ ወዳጅ ሁን፣ ወረቀት ላክ። የሀበሻ ሰው ሁሉ አንተን ይጠብቃል ይመኛል። ለሀበሻ ሰው ዓይን አውጣለት፣ ዕውር ሁኗል፣ ጥበብ አውጣለት፣ እንዲህ ዕውር ሆኖ አይቅር።



ከዚህ በተጨማሪ ወይዘሮ ላቂያዬ ለንግሥት ቪክቶሪያም ሌላ ደብዳቤ ጽፈውላቸዋል። የደብዳቤውን ይዘት እነሆ፡-

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፣
ከወይዘሮ ለቂያዬ የእቴጌ ጥሩ ወርቅ እናት፣
የደጃዝማች ዓለማየሁ አሚታ የተላከ።

ይድረስ ለእንግሊዝ አንባቢው፣* እጅ ንሣልኝ። መድኀኒዓለም ጤና ይስጥልኝ። መንግሥትዎ ይስፋ፣ጠላትዎን ያጥፋ። ሦስት ደጃዝማቾች፣ አራተኛ እቴጌ ሙተውብኝ የቀረኝ ደጃዝማች* ዓለማየሁ ብቻ ነው። አደራዎን ይጠብቁልኝ። እግዚአብሄር አባቱን እና እናቱን ቢነሣው እርስዎን ሰጥቶታል። እኔም ካላየሁት ከሞቱት ቁጥር ነኝ። እርስዎን እናቴ ይላል* እንጂ እኔን እናቴ አይለኝም። እኔ አላሳደግሁትም እና እርስዎ ያሳድጉት፣ ስለ እግዚአብሄር ብለው።

ለንግሥት ቪክቶሪያ የተጻፈው ደብዳቤው ትርጉም ለሚስተር ሎው ከላኩ በኋላ ምንም መልስ ሳይሰጥ ቀረ። ከዚያም ጥቂት ቆየት ብሎ፣ ሰር ባርትል ፍሬየር የሚባሉ ሰው "የሀበሻ ንጉሥ እንዲሆን ለምን አይደረግም" የሚል ምክር ሰጡ። እኝህ ሰው ሐሳቡን ያቀረቡት በ፲፰፻፷፱ ዓ.ም. ነው። ቡድሎፍ በበኩሉ ለንግሥት ቪክቶሪያ መግለጫ ሲሰጥ "ዓለማየሁ ወደ ሀበሻ አገር የመመለስ ፍላጎት የለውም" አለ።

ለዚህ አባባሉ የሰጠው መግለጫ ወይም አጥጋቢ ምክንያት ግን አልነበረም። በአንፃሩ ልዑል ዓለማየሁ "አገሬ ሁለት አክስቶቼና የእናቴ ወንድም በሕይወት አሉ። እኔ ወደዚያ (ወደ አገሬ) መሄድ እፈልጋለሁ" እያሉ ይናገሩ ነበር።

የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ጥቅምት ፰ ቀን የልዑል ዓለማየሁን ሃሳብ ለሌዲ ቡድሎፍ ሲጽፍ "ወደ አገሩ የመሄዱ ጉዳይ ከጥያቄ ውጪ መሆኑን ስነግረው እሱም መልሶ በእንግሊዝ አገር ውስጥ ማንም እንደ ሚስተር ስፒዲ ጥሩ ያደረገልኝ ሰው የለም" አለኝ ብሏል። ከዚህ አባባላቸው የምንረዳው፣ ልዑል ዓለማየሁ ከስፒዲ በመለየታቸው እና አለኝ የሚሉት ሰው በማጣታቸው ክፉኛ ያሳዘናቸው መሆኑን ነው።

---

* ንግሥት ቪክቶሪያ ናስሕዋ እናት እሆናለሁ ያሉትን በመጥቀስ ነው ፡

ልዑል ዓለማየሁ በዚህ ዓይነት አተካራ ውስጥ በመግባታቸው በጥቅምት ወር ራንሳም ቤት እያሉ በሽታው አገረሸባቸው። በወቅቱ ኖርዝኮት ስለ ልዑል ዓለማየሁ ሕመም እንዲህ ብሎ ጽፏል። እኔ የሚገባኝን መግለጽ ስላለብኝ፣ ዓለማየሁ በእንዴት ባለ አደገኛ ሕመም እንደ ተጠመደ ልገልጽ እወዳለሁ። ከመጀመሪያው ጊዜ አሁን ስለ ተሻለው ይድናል የሚል ትንሽ ተስፋ አለ። ነገር ግን በአጠራጣሪ፣ በአወላዋይ እና በአስጊ ሁኔታ ላይ ነው ያለው። በደረት ውጋት በመሰቃየት ላይ ስለሆነ፣ ሁለት ጊዜ ደረቱን ታግሟል። በሽታው ብርቱ ስለ ሆነ ሰውነቱ በአሳዛኝ ሁኔታ ከመቀነሱም በላይ ማንኛውንም ዓይነት ምግብ እና መድኀኒት መውሰድ አቅቶታል። አሁን በአለበት ሁኔታ የሚታዘዘውን መፈጸም ተስኖታል። ዶክተር ካልፎርድ አልበርትን፣ ሰር ዊሊያም ጎልን እና ሰርጄምስ ፐጀትን ለውይይት ጠርቻቸው ነበር። እነሱ ያላቸው አስተያየት፣ እኔ እንዳሰብኩት ሁሉ፣ ልዑል ዓለማየሁ ለሕይወቱ አስጊ በሆነ ሕመም የተለከፈ መሆኑን ነው።

ንግሥት ቪክቶሪያ ስለ ዓለማየሁ መታመም በሰሙበት ኅዳር ፬ ቀን ሄንሪ ፔንሰባይን ተቀብለው ከአነጋገሩ በኋላ ሌዲ ቡዶልፍ ልዑሉ ወደ አሉበት ቦታ ሂደው እንዲያይዋቸውና ሁኔታቸውን እንዲገልጹላቸው በስልክ አዘዟቸው። እሳቸውም ሰር ጆን ፓልን ጠርተው አብረው ሂደው ልዑል ዓለማየሁን ሲያይዋቸው በስቃይ ላይ ነበሩ።

ይህንኑ ሌዲ ቡዶልፍ ለንግሥቲቷ ነገሩ። ንግሥት ቪክቶሪያም እግዚአብሔር ይማርህ የሚል የማጽናኛ ደብዳቤ ጽፈው ለልዑል ዓለማየሁ ላኩላቸው። ከንግሥት (ቪክቶሪያ) የተላከላቸው ደብዳቤ እንደ ደረሳቸው በከፍተኛ ናፍቆትና ፈገግታ አንቦልጭን ከፍተው ጥቂት መስመሮች ካነበቡ በኋላ በሃሳብ ተውጠው አጠገባቸው ወዳለው ሰው ዞር ብለው ደብዳቤውን እንዲያስቀምጥላቸው ሰጡት። ደብዳቤው እስከ ዕለተ ሞታቸው ቀን ድረስ የተቀመጠው እሳቸው እንደፈለጉ ሊያዩት ከሚችሉበት ቦታ ነበር።



ዐፄ ቴዎድሮስ ከልብ የሚወዱት እና የሚሳሱላቸው ልጃቸው ልዑል ዓለማየሁ እ.አ.አ. ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፰፻፸፩ ዓ.ም. ከጧቱ በሦስት ሰዓት ላይ በተወለዱ በ፲፱ ዓመታቸው እንግሊዝ አገር ሎንዶን ከተማ ዐረፉ።

የልዑል ዓለማየሁ ቴዎድሮስ የቀብር ሥነ ሥርዓት በንግሥት ቪክቶሪያ ፍላጎትና ፈቃድ ዊንድሶር በሚገኘው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ፣ ከቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት ተፈጸመ።

በቀብሩ ሥነ ሥርዓት ላይ ራሳቸው ንግሥት ቪክቶሪያ እና ልዕልት ቢትሪስ የአበባ ጉንጉን ላኩ። በዚያ የበረዶ ዶፍ በቀብሩ ሥነ ሥርዓት ብዙ ሰዎችና ጋዜጠኞች ተገኝተዋል።

በቀብር ሥነ ሥርዓቱ ላይ ሌዲ ቡዶልፍ እና ሌዲ ፐንሰቤይ፣ሚስተርና ሚስስ ጃክ ብሌክ፣ ካፒቴን ስፒዲ፣ ሁለቱ የገንዘብ ሚኒስቴር ቻንስለሮች፣ ሚስተር ኖርዝኮት፣ሚስተር ሎው እና ሌሎችም ታላላቅ ሰዎች ተገኝተዋል። የቀብሩ ዕለት አየሩ በጣም ቀዝቃዛ ከመሆኑም በላይ በረዶም ይጥል ነበር። ስለ ልዑል ዓለማየሁ አሟሟት ንግሥት ቪክቶሪያ ኅዳር ፲፬ ቀን የሚከተለውን በዕለት ማስታወሻቸው ውስጥ ጽፈውታል።

> "በዛሬው ጧት ጥሩው ወዳጃችን ዓለማየሁ ከዚህ ዓለም በሞት መለየቱን በተረዳን ጊዜ የተሰማን ጥልቅ ኀዘን አሰቃቂ እና የሚያንገፈግፍ ነበር።"

በመቀጠልም ንግሥት ቪክቶሪያ ስለ ልዑል ዓለማየሁ አማሟት ከጻፉት ጥቂቱን ከዚህ በታች አቀርባለሁ።

የልዑል ዓለማየሁ አሟሟት በእርግጥ አሳዛኝ ነው። ምክንያቱም እስከዚህ ዕድሜው ድረስ በሰው አገር ኑሮ በብቸኝነት ዘመኑን ስለ አሳለፈ እና ወገኑ የሆነ ዘመድ ወይም ጓደኛ ሳይኖረው፣ የሀገሩን ሽታ እንደ ናፈቀ መሞቱን እና ደግና ጥሩ ወጣት እንደነበረ ትዝ ሲለንም ሆነ ስናስታውስ ያጋጠመውን ሰንካላ ዕድል እንደ እርሱ ለመቋቋም የሚችል የለም። ሕይወቱ በሙሉ የደስታ አልነበረም። ማንኛውም ዓይነት ችግር እና ስቃይ ያጋጥመው ነበር። በዚህም ላይ አስተዋይነትና ብልህነት የታደለ ወጣት ነበር። ስለሆነም ብቀለሙ ልዩነት ሕዝቡ አተኩሮ ሲመለከተው ደስታ ሳይሰማው ኑሯል፣ የሚል ስጋት አድሮብኝ ነበር። ስለዚህ በሁሉም ነገር ከፍተኛ ኀዘን እንደተሰማው ዐለፈና በክርስ መቃብር ተኛ።

ወጣቱ ልዑል ዓለማየሁ ቴዎድሮስ ባባዕድ አገር ሳይመቻቸውና ሁልጊዜ አገራቸው እንደናፈቃቸው ለሞት የዳረጋቸው ብቸኝነት መሆኑን ንግሥቲቱ ተገንዝበውታል። ንግሥት ቪክቶሪያ ልዑል ዓለማየሁን የተቻላቸውን ያህል ሊያቀርቧቸው እና ሊያግዟቸው ቢፈልጉም፣ በዙሪያቸው የነበሩ ሹማምንት በፈጠሩት ሴራ ሳይሳካ ቀርቷል። ለዚህም ማስረጃ፣ የሚሆነው ካፒቴን ስፒዲ ከኢትዮጵያ ሲወጣ፣ ከልዑል ዓለማየሁ እናት እቴጌ ጥሩ ወርቅ የተቀበለውን አደራ በሚገባ እየፈጸመ መሆኑ እየታወቀ፣ ከእሱ እንዲለዩ መደረጉ ነው።

ከዚህ ከፍ ብሎ በንግሥት ቪክቶሪያ ጽሑፍ ከተጻፈው እንደምንገነዘበው የልዑል ዓለማየሁ ዋናው ችግር ሆኖ ያስረከረካቸው ባይተዋር እና ብቸኛ መሆናቸው ነበር። ሌላው ነገር ቢቀር እንኳን በአንድ ቀን አብረዋቸው ከመቅደላ የወጣው ትንሹ የአገራቸው ልጅ (ሕፃን ወርቅነህ) አጠገባቸው ቢኖሩ ኖሮ ሁለቱም እንደ ታላቅ እና ታናሽ ወንድማማቾች ሁነው ባደጉም ነበር።

ይህ ተደርጎ ቢሆን ኖሮ እሳቸውን ያሳዝናቸው እና ያብከነክናቸው የነበረው የጓደኛ እጦት ባላጋጠማቸውና በመጨረሻ ሕይወታቸውን ለቀጠፈው አደጋ ባልተጋለጡም ነበር።



ልዑል ዓለማየሁ በባዕድ አገር በሞት አፋፍ ላይ እያሉ ቢናዘዙ ኖሮ ምናልባት የሚከተለውን ስንኝ ዓይነት ሳይቋጥሩ አይቀሩም ነበር።

*ምንድነው አባባ የምትለው ነገር*
*ከአንተ ከተለየሁ ይሰማኛል ችግር*
*በሕፃንነቴ ጉልበቴ ሳይጠና*
*ሩቅ ምሥራቅ አገር መጥቻለሁና*
*ይወጣል ይወርዳል ልቤ እንደ ደመና*
*ዐውቀዋለሁ እኔ አለመታደሌን*
*የሰቀቀን እንባ ይቀዳዋል ዓይኔን*
*ከእንግዲህ በኋላ ተውኩት ሰው መሆኔን።*

ከወልደ ገብርኤል አሥጌ

ምስኪኑ ኢትዮጵያዊ፣ የጀግናው ዐፄ ቴዎድሮስ ልጅ፣ ልዑል ዓለማየሁ በዐረፉ በማግስቱ በርካታ የእንግሊዝ ጋዜጣዎች ታላቅ ዜና አድርገውት ነበር። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በዘመኑ በሎንዶን ውስጥ በርካታ አንባቢ ደምበኞች ካሏቸው ሁለት ጋዜጦች መጥቀሱ በቂ ይመስለኛል። ስለዚህ በታይምስ እና በዴሊ ቴሌግራፍ ውስጥ ከተጻፈው እጠቅሳለሁ።

"ማለፊያ ዛላ የነበረው፣ ቁመቱ ፮ ጫማ የሆነው
ልዑል ዓለማየሁ በዛሬው ዕለት ተቀበረ"

ታይምስ ጋዜጣ።

"የእናት አገሩ ነፋሻ አየር፣ ሞቃት ፀሐይ፣
ውብ አትክልቶችና አበቦች እንደናፈቁት፣ከባቢ
አየሩ በሚቆፈንን የባዕድ አገር የወጣቱ ልዑል
ዓለማየሁ ሕይወት ተቀጨ"

ዴሊ ቴሌግራፍ።

ከላይ በተጠቀሱት ሁለት ጋዜጦች ዘገባ የልዑል ዓላማየሁን አጭር የሕይወት ታሪክ ከመደምደሜ በፊት፣አያታቸው (አሚት) ወይዘሮ ላቂያዬ በደብዳቤያቸው ውስጥ ስለ ጻፏቸው ሁለት ቃል እና ሐረግ ጥቂት ልበል።

የልዑል ዓለማየሁ ቴዎድሮስን አጭር የሕይወት ታሪክ ለመደምደሚያ እንዲሆን አያታቸው በጻፉት ደብዳቤ ውስጥ ስላሉት ሁለት ቃላት ወይም ሐረግ መግለጫ መስጠ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁና እነሆ።

1. "ለእንግሊዝ አንባቢው እጅ ንሳልኝ" ስለሚለው፡-
   በዚያን ዘመን የኢትዮጵያ ነገሥታት ደብዳቤ ሲደርሳቸው ብሊቀ መኳሶች ያስነብቡ ስለነበረ፣ወይዘሮ ላቂያዬ የእንግሊዝ አገር ደንብ እንደ ራሳቸው አገር መስሏቸው ነው ይህን ሐረግ የጻፉት።

2. ደብዳቤው ላይ "ደጃዝማች" በሚል ማዕረግ ስለጻፉት፡-
   ይህም በዚያን ዘመን በኢትዮጵያ ከመሳፍንት ወገን ለሚወለዱ ልጆች በጨቅላ ዕድሜያቸው ይሰጥ የነበረ ማዕረግ "አቤቶ"፣"ደጃዝማች" ወዘተ የሚል ነበር። ወይዘሮ ላቂያዬ ደጃዝማች ብለው የጻፉት በአገራቸው ሥርዓት መሠረት ነው። እንግሊዝ አገር ደግሞ የነገሥታት ቀጥተኛ ልጆች ከሕፃንነታቸው ጀምሮ "ልዑላን" ይባላሉ። እኔም በመጽሐፉ ውስጥ የጻፍኩት ካነበብኳቸው በእንግሊዝኛ ከተጻፉ ዋቢ ጽሑፎች ያገኘሁትን የማዕረግ ስም ነው።

አባቱ ዐፄ ቴዎድሮስ የልዑል ዓለማየሁን ነፍስና ሥጋ ይቅርና ጠረኑን ያፈቅሩ የነበረው ልጃቸው እንዲህ በሰው ናፍቆት ተብሰክስከው እና ተሰቃይተው መሞታቸውን ለማወቅ ቢችሉ ኖሮ ምን ያህል ያዝኑ ነበር?

ከእቴጌ ጥሩ ወርቅ የተቀበለውን አደራ ጠብቆ፣ስፒዲ የራሱ ልጅ ስለሌለው፣ ልዑል ዓለማየሁን የንብረቱ ሕጋዊ ወራሽ መሆናቸውን በኑዛዜ ካስጸደቀ በኋላ፣ በመጀመሪያ ሞግዚትነቱን ቀጥሎም የዓይኑ ብሌን የሆነውን ወጣት፣ሞት የሚባል ደበኛ ሲነጥቃቸው ካፒቴን ስፒዲ እና ለባለቤቱ የደረሰባቸውን ሰቆቃ መገመት አያዳግትም።



ዐፄ ቴዎድሮስ በሕጋዊ ጋብቻ የወለዱት ብቸኛ ልጃቸው አስከሬን ባረፈበት የዊንድሰር የፀሎት ቤት በነሐስ ሰሌዳ ላይ በተቀረፀው የሸንኮላ ቃል ለዚህ ለልዑል ዓለማየሁ አጭር የሕይወት ታሪክ ምዝገባ መቋጫ አድርጌዋለሁ።

"እንግዳ ሆኜ መጣሁ፣ተቀበላችሁኝ"



ልዑል ዓለማየሁ በ[illegible] ትምህርት ቤት የደንብ ልብስ

ዐፄ ቴዎድሮስ በሕጋዊ ጋብቻ የወለዱት ብቸኛ ልጃቸው አስከሬን ባረፈበት የዊንድሰር የፀሎት ቤት በነሐስ ሰሌዳ ላይ በተቀረፀው የሽንገላ ቃል ለዚህ ለልዑል ዓለማየሁ አጭር የሕይወት ታሪክ ምዝገባ መቋጫ አድርጌዋለሁ።

"እንግዳ ሆኜ መጣሁ፣ ተቀበላችሁኝ"



ልዑል ዓለማየሁ በግሎሴስተር ትምህርት ቤት የደንብ ልብስ

<u>ዋቢ ጽሑፎች</u>

፩. ገሪማ ታፈረ:- አባ ታጠቅ ካሣ: የቋራው አንበሳ
፪. ጳውሎስ ኞኞ:- አጤ ቴዎድሮስ
፫. ሄንሪ ብላንክ:- የእስራት ዘመን በአበሻ አገር (ትርጉም)
፬. ወልደ ገብርዔል አሠጌ:- ልዑል ዓለማየሁ: መስፍኑ ምርኮኛ
፭. ከበደ ሚካኤል:- የዕውቀት ብልጭታ (ግጥም)
፮. ዘውዴ ገብረ ሕይወት:- የሕይወት ውጣ ውረድ
፯. ታደሰ ብጡል ክብረት:- መጽሐፈ ውይይት

Bibliography

1. Charles Martin:- My memoirs (Type-written)
2. John Camedon Hoten:- Abyssinia and Its People
3. Allan Moorhead:- The Blue Nile
4. Captain Speedy:- Type-written letters
5. Sven Rubinsen:- King of Kings : Theodros of Ethiopia


## ከዚህ በፊት ደራሲው ያሳተማቸው መጽሐፎች

እንቃወማለን:- ስቶክሆልም 1956 ዓ.ም.
ኀብረት:- ስቶክሆልም 1966 ዓ.ም.
Kan Du Hjälpa Etiopien:- Stockholm 1969 ዓ.ም.
ማራዠት (ቅጽ 1):- አዲስ አበባ 1987 ዓ.ም.
ሮማ ያሉ የግብፅ እና የኢትዮጵያ ሀውልቶች:- በኮምፒውተር የታተመ 1987 ዓ.ም
ውልታ፤ከበደ ሚካኤል ከልጅነት እስከ ዕውቀት/ አዲስ አበባ 1989 ዓ.ም.
መጽሐፈ ውይይት (ቅጽ 1) አዲስ አበባ 1991 ዓ.ም.
The Origin of Humankind:- Hannover 2000 G.C.
የከበደ ሚካኤል ምርጥ ድርሰቶች:- በኮምፒውተር የታተመ 1994 ዓ.ም.
ሦስትዮሽ እና ሌሎች ግጥሞች:- አዲስ አበባ 1997 ዓ.ም.
ዐፄ ቴዎድሮስ እና ልዑል ዓለማየሁ ቴዎድሮስ 2000 ዓ.ም.

## ከደራሲው ለህትመት የተዘጋጁ

አዛዥ ወርቅነህ እሸቱ
የአክሱም ሐውልት መመለስ ታሪክ
ባለውለታ ኢትዮጵያውያን
የማይታመን ታሪክ (ታሪካዊ ልብወለድ)
ማራዠት (ቅጽ 2)
መጽሐፈ ውይይት (ቅጽ 2 እስከ 5)
ልብሲቱ መኮንን (የብቸኛ እናት ታሪክ)
ስምን መልዓክ ያወጣዋል (የራሴን በራሴ)